ስለዚህ ጌታ ሆይ ይቅርታና ከኛ ጋር ይሁን ለዘለዓለም(2)
ጥቅስ፡ ሉቃ21÷1

መዝሙር
አቤት የዚያን ጊዜ
አቤት የዚያን ጊዜ ክርስቶስ ሲመጣ(2)
ትንሹም ትልቁም(3) መድረሻውን ሲያጣ
ከምሥራቅ ከምዕራብ ከሰሜን ከደቡብ(2)
ነፋሳት ሲሳኩ(3) መዓትህን ለማዝነብ
ሠማይና ምድር ባንድ ሲዋሐዱ(2)
የት ይሆን መድረሻው(3) የት ይሆን መንገዱ
አቤት የዚያን.....
ፃድቃን በቀኝ በኩል ሃጥአን በግራ(2)
ሲነፋ መለከት(3) ሲደለቅ አምቢልታ
ምድር ቀውጢ ስትሆን አጽም ሲሰበሰብ(2)
ህፍረት ይዋዘዋል(3) ሰው ለፍርድ ሱቀርብ
አቤት የዚያን.....
ጩኸት ሲበረታ የማይጠቅም ለቅሶ(2)
ነዶ ቁረ ጠቁሮ(3) ጽለመትን ተሳብሶ
ገነትን ሲያገኙ ጻድቃን በሥራቸው(2)
ኃጥአን ወደ ሲኦል(3) ተፈረደባቸው
አቤት የዚያን.....
ጥቅስ ማቴ 24÷32

መዝሙር
አምላክ ሆይ ወደ አኛ
አምላክ ሆይ ወደአኛ ባትመጣ ስብሰህ የማርያምን ሥጋ(2)
ባክኖ የነበረው የአዳም ዘር ውጤቱ ነበር የሚያሰጋ(2)
በዚያ ዓመት በዚያ ወር በዚያች ቀን ድኀነትን ለሰው ልጅ ስትሰጥ(2)
ምን የበዛ ነበር ትህትና ትእግስትህ የማይለወጥ(2)
የሾህ አክሊል ደፍተው በራስህ ጐንህን ሲወጉት በጦር(2)
አንተ ግን ለእነርሱ ካለባትህ ምሕረትን ትለምን ነበር(2)
ግን መቼ አወቁ እነርሱ በሀጢአት ደንድኖ ልባቸው(2)
መድኃኒታቸውን ገረፋህ ሰቀሉህ አንተም ሞትክላቸው(2)
ዳግም ስትመጣ ለፍርድ ከዓለም ፍፃሜ በኋላ(2)
አረ እንዴት እድለኞች ናቸው በፊትህ የሚያገኙ ተድላ(2)
በዚያች በደብረ ዘይት ቦታ ደስታና ለቅሶ ሲፈልቅ(2)
አረ ከየት ይሆን አጣዩ ያን ጊዜ የኔ አወዳደቅ(2)
የፀፀት እሮሮ እንዳያቃጥለኝ እኔን(2)
እርዳኝ ፈጣሪዬ ካሁኑ አድሰው የዛገው ልቤን(2)
ጥቅስ: ሉቃ23÷32-49 መዝ50÷1

(የሆሣዕና መዝሙራት)

መዝሙር
ሰላምሽ ዛሬ ነው
ሰላምሽ ዛሬ ነው ኢየሩስ ዓሌም
ወደ አንቺ መጥቷልና አመላክ ዘለዓለም(2)
ሆሳእና በአርአያም አያሉ ዘመሩ
ሕፃናት በኢየሩሳሌም
አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ
የሕዝቦችሽ ብርሃን መጣልሽ በግርማ(2)
ሆሳእና.....
ሆሳእና አያሉ አመሰገኑት
በኢየሩስዓሌም አእሩግ ሕፃናት
ሆሳእና.....
ኪሩቤል መንበሩን የሚሸከሙት
መስቀል ተሸክሞ ሆነ መድኃኒት(2)
ሆሳእና.....
የኢየሱስን ሕማም ደናግልም አይተው
አያስቀሱስት ሔዱ ተከትለው(2)
ሆሳእና.....
ጥቅስ: ዘካ9÷9-10 ሉቃ 19÷42

መዝሙር
ሠላም ሠላም ብለን
ሠላም (2)ብለን እንዘምር ስሙን
ተአጋሽ ነውና የዓለም መድህን(2)
ሠማይን በብርሃን አስጊጦ ሰርቷት
ምድርን በውኃ ላይ አጽንቶ ፈጥሯት(2)
በገዛ ገንዘቡ ውሃ ጥም ይዞት
ተጠማሁ ቢሳቸው ሐሞት አጠጡት(2)
የሕይወት ምንጫችን እንዳልሆነ ሁሉ
ውሃ ስጡኝ ብሎ ለመነ በቃሉ(2)
እጅግ ያስደንቃል የሱ ትዕግስት
ቃልም አልመለሰ እንዲያ ሲገርፋት(2)
ዘጠና ዘጠኙን መላዕክትን ትቶ
ቆሟል ቀራንዮ እንጨት ተጠግቶ(2)
እጅግ ደሃ መሳይ የንጉስ ልጅ ንጉስ
በአህያ ተቀምጦ ገባ ከመቅደስ(2)
ጥቅስ: መዝ135÷6 ማቴ27÷48 ማቴ18÷12

መዝሙር
የአምላካችን ክብሩ ይስፋ
የአምላካችን ክብሩ ይስፋ
ምስጋናውም ይንሰራፋ
ሰይልናልና ታላቅ ተስፋ
ወገኖቹ እንዳንጠፋ
የምሥራች ልል በሉ
ችግረኞች ይሆች ሁሉ
የምሥራች አልል በሉ
ተሰናዱ በውል ሁኑ
እንድንዘምር ለሕፃኑ
ወርዶ መጥቷል ከዙፋኑ
ቤዛ ሊሆን ለወገኑ
የምሥራች.....
አምላካችን ደጉ አባት
ባለ ብዙ ቸርነት
ወገኖቹ እንዳንሞት
ሰደደልን መድኃኒት
የምሥራች.....
የዳዊት ልጅ ሆሳዕና
ይገባዋል ክብር ምስጋና
ለእርሱ ችግር ለኛ ጤና
ከዙፋኑ ወርዷልና
የምሥራች.....
ባጐደሉት ሰዎቻችን
አስሮን ነበር ጠላታችን
ከፋይ ሰዶ ለእዳችን
ባሮች ሆንን ለአምላካችን
የምሥራች.....
ጥቅስ:

መዝሙር
ሆሳዕና በአርያም
ሆሳእና (3) በአርአያም ሆሣዕና
ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም
ምስጋናሽ ብዙ ነው በመላው ዓለም
በአህያ ላይ ሆኖ ወደ አንቺ የገባው
ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ነው
ሆሳዕና.....
ኃይልና ሥልጣን በአንድ ላይ ሳለው
ጠላቶቹ አፈሩ ሕዝብሽም ደስ አለው
ሆሳዕና.....
ሰውማ ቢዘምር ምን ያስገርመናል
ሆሣዕና ሰው ቀርቶ ድንጋይ ያናግራል
ሆሳዕና.....
ጥቅስ: ማቴ21÷1-11

መዝሙር
እመ አፈ ደቂቅ
እም አፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳድሎከ ስብሐት(2)
በእንተ ፀላኢ(3) ከመትንስቶ ለፀላኢ ከመገፋኢ(2)

ትርጉም፡ ከሕፃናት አንደበት ምስጋናን አዘጋጀህ
የጠላት ዲያብሎስ ምክሩን ታፈርስበት
ዘንድ
ጥቅስ፡ መዝ8 ÷ 2

መዝሙር
ሆሳእና አምርት
ሆሣዕና አምርት አንተ አቡነ ዳዊት(2)
ቡሩክት አንተ ትመጽዕ መንግሥት
ትርጉም፡ በጌታስም የምትመጣ አባታችን የዳዊት
መንግሥት የተባረከች ናት የታወቀ
ሆሣዕና በአርያም ይሁን
ጥቅስ፡ መዝ117 ÷ 26

መዝሙር
ሆሳዕና በአርያም
ሆሳእና በአርያም
ሃሌ ሃሌ ሉያ(2)
መድኃኒት መጣልን ለሁላችንም
ሃሌ ሃሌ ሉያ(2)
ምሥጋና ይደረሰው ለአምላክ በመላው ዓለም
ሆሳእና (2) በአርያም
ብሩክ ነው የመጣው በእግዚአብሔር ሥም
ሃሌ ሃሌ ሉያ(2)
አናከብረዋለን ከልባችን ለዘለዓለም
ሆሳእና (2) በአርያም
ጥቅስ፡

(የስቅለት መዝሙራት)

መዝሙር
ወሪዶ እመስቀሉ
ወሪዶ እመስቀሉ(2)
አመስቀሉ አብርሃ ለኩሉ(2)
ትርጉም፡ ከመስቀሉ ወርዶ አበራ ለሁሉ::
ጥቅስ፡

መዝሙር
በጌቴ ሴማኒ
በጌቴ ሴማኒ በአትክልቱ ቦታ(2)
ለኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ(2)
አዳምና ሔዋን ባጠፋት ጥፋት(2)
ለእኛም ነበረብን የዘለዓለም ሞት(2)
መስቀል ተሸክሞ ሲወጣ ተራራ(2)
ደገርፋት ነበረ ሁሉም በየተራ(2)
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ(2)
እያየች በመስቀል ልጇ ሲንገላታ(2)
በአምላክነቱ ሳይፈርድባቸው(2)
እንዲህ ሲል ፀለየ አባት ሆይ ማራቸው(2)
በረቂቅ ሥልጣኑ ሁሉን የፈጠረ(2)
በሰዎች ተገርፎ ሞተ ተቀበረ(2)

ጥቅስ፡ ማር14 ÷ 32-72 ዮሐ19

መዝሙር
አዳምን ሲያወጣው
አዳምን ሲያወጣው ከገሃነም ቀንበር(2)
በጌቴ ሴማኒ ፀሎት አርጉ ነበር(2)
ኢየሱስ በዚያ መስቀል ሳይ በቀራንዩ
ምሕረት ለመነ ለጠላቶቹ እንዲህ እያለ
የማያውቁትን በማድረጋቸው
አባት ሆይ አንተ ይቅር በሳቸው(2)
ይቺ ጽዋ ትለፈ አባት ሆይ ቢቻልህ
ደግሞም ባይቻልህ(2) ያንተው ፈቃድ ትድረስ
ኢየሱስ.....
ለኛ ወገኖችህ ሀጢአት ሳደክመን(2)
የመስቀልህ ጥላ (2)ማረፊያ ትሁነን(2)
ኢየሱስ.....
ጥቅስ፡ ማቴ 26 ÷ 36-46 ሉቃ22 ÷ 40-46

መዝሙር
በስመ አብ ወወልድ
በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ(2)
ምስጋና ይደረሰው ለሰዳኝ ክርስቶስ(2)
በሥም ቅዱስ ሲሆን በንፁህ ሕሊና(2)
በዙሪያ መቅደሱ አንገኛለንና(2)
ልደት ቤተልሔም ጥምቀት የርዳኖስ(2)
መሠረት ተዋሕዶ ድኅነት ሥጋ ነፍስ(2)
ቤዛ ኩሉ ዓለም መሥዋዕተ ነፍሳችን(2)
ክርስቶስ ቃለ አምላክ በግዐ ፋሲካችን(2)
ልዑል ጌታ ክርስቶስ ፈጣሪ(2)
ምስጋና ይደረስህ በሰማይ በምድር(2)
ወሀቤ ሕይወት ፀጋ ዘእም ፀጋ(2)
አሜን ሃሌ ሉያ አልፋ ወዖሜጋ(2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
ፍቅር ሰሀቦ
ፍቅር ሰሀቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ(2)
ወአብጽሖ(4) እስከ ለሞት(2)
ትርጉም፡ ፍቅር ወልድን ከልዑል መንበሩ ሳበው እስከ
ሞትም አደረሰው
ጥቅስ፡ ዮሐ3 ÷ 16 ሐኖዮሐ4 ÷ 7-12

መዝሙር
አቤቱ ማረን
አቤቱ ማረን ይቅር በለን(2)
ያለአንተ መድኃኒት የለን(2)
ሥጋዬን ብሱና ደሜን ጠጥታችሁ(2)
ዘለዓለማዊ ሕይወት ይኑራችሁ(2)
አቤተማረን..ሩ.....
ብሎ ነበር አርሱ የሚሰማው ጠፋ
ሁሉም በየድርሻው ምኞቱን ሲያስፋፋ
አቤተማረን..ሩ.....
በሕይወት ለመኖር ትዕዛዙን ጠብቀን
ምኞት ሳናበዛ አናስብ ሰሙን(2)
አቤተማረን..ሩ.....
በሥጋው ቀድሶ ሲያድነን በደሙ
ምን ውስታ ሰራን ለአምላክ በስሙ(2)
አቤተማረን..ሩ.....

ደህን ቅዱስ ሥጋ ደህን ክቡር ደም
አንዴት ልጆች ብቻ በልተውት ደፈጸም
አቤተማረን.ሓ.....
ብዙ ሰው ስግብግ ተጠርቶ ነበረ
ጊዜን በማሳለፍ ከዚያው ከደጅ ቀረ
አቤተማረን.ሓ.....
ሌሎቹ በጥበብ ስማዳን ሲደክሙ
ሕይወት የተገኘው በሥጋው ወደሙ(2)
አቤተማረን.ሓ.....
ጥቅስ፡ኢሳ43 ÷ ዮሐ6 ÷ 53

መዝሙር
የንጉሶች ንጉሥ
የንጉሶች ንጉሥ ፈጣሪ ሲሆን
ዙሪያውን አስቀምጦ ተማሪዎቹን
እራሱን አዋርዶ አጥቦ አግራቸውን
አንደ እናት አንደ አባት ሆነ መምሕራችን
ምሳሌ አንዲሆኑ ለወንድሞቻቸው
ምሳሌ በመሆን ጌታ አስተማራቸው
አኔ ልሙትልህ አኔ ልንገላታ
በተንገላታህው በተከዝከው ፈንታ
አንዲያ ሲያንገላቱህ ሲመቱህ በእጃቸው
የምሕረት ሸማ አጐናፀአካቸው
ቢያውቁትማ ሰውነታቸውን
በሀጢአት ሸማ መተብተባቸውን
መቼ ይሰቅሱት ነበር መድኃኒታቸውን
ጥቅስ፡ ዮሐ13 ÷ 4-17

መዝሙር
ክርስቶስ ያንተ ሞት
ክርስቶስ ያንተ ሞት ሕይወት ባይሆን
የሥቃይን ነገር አንደምን በቆጨን
ራስህን መውደድ ካለ አዋቂ ነኝ ማለት
አንድ ሰው አይችልም ለመኖር በሕይወት
ብናስታውሳቸው የአይሁድ ካህናትን
በምቀኝነት ነው ጌታን የሰቀሉት
ክርስቶስ ያንተ ሞት.....
በሰው እጅ መውደቅ ምንኛ ጭንቅ ነው
ባለመብት ሆኖ አርሙን ቢለምነው
የዝናሙን ጌታ ውሃ ከለከለው
ሀሞትና ከርቤ መራራን አጠጣው
ክርስቶስ ያንተ ሞት.....
አርሱ ግን ይህ ሁሉ በላዩ ላይ ሲደርስ
የተናገረው ቃል ኪዳኑን ሳይጥስ
ሰዎች አፈዙበት ፍርድን ተቀበለ
ከወንበዴዎች ጋር አብሮ ተሰቀለ
ክርስቶስ ያንተ ሞት.....
ከፈጠርከው ፍጥረት ታላቁ ሰው ሲሆን
ቢሰራም ስህተት የማይገባውን
ኃጢአቱን ሳትቆጥረው ሳትገነዘበው
ከንቱ ሆኖ አንዳይቀር አንተው ይቅር በለው
ክርስቶስ ያንተ ሞት.....

ጥቅስ፡ ማቴ 27 ÷ 15-25 ማር 15 ÷

መዝሙር
ሥጋውና ደሙ
ሥጋውና ደሙን አምኖ የሚቀበል(2)
የዘለዓለም ሕይወት አግኝቶ ይኖራል(2)
የአቤልን መስዋዕት የተቀበልክ አምላክ(2)
ለእኛም ለምዕመናን መንፈስ ቅዱስን ላክ(2)
ሥጋውን የበላ ደሙንም የጠጣ(2)
ከኃጢአት ደዌ የሚፈውሳቸው(2)
ሥጋውና ደሙ ከዚህ አለላችሁ(2)
ከነልጅ ልጆቹ አዳምን ለማዳን(2)
መስዋዕተ መድኃኒት ሆነ የዓለም ብርሃን(2)
በቀልን ሳይተው መቀበል በድፍረት(2)
እያዩ መግባት ነው ከሚያቃጥለ አሳት
ይህን የወንጌል ቃል አሁን የሰማችሁ(2)
ቂምና በቀልን ተው አባካችሁ(2)
ጥቅስ፡ ዮሐ6 ÷ 54 1ኛቆሮ11 ÷ 24-26

መዝሙር
የአብርሃም አምላክ
የአብርሃም አምላክ የይስሃቅን ቤዛ(2)
ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ(2)
የሀሰት ምስክር አቁመው ከሰሱት(2)
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት(2)
ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አሰሮ(2)
ከሮማዊው መንግሥት እንዲኖር ተፋቅሮ(2)
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ(2)
እያዩት በመስቀል ልጇ ሲንገላታ(2)
በብርሃን ዙፋን ላይ የቆሙት አግሮቹ(2)
በችንካር ላይ ቆመው ምንም አልሰለቹ(2)
የብርሃን አክሊልን ለሰማእት ያደለ(2)
የሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ(2)
ጥቀስ፡ መር15 ÷ 33 ርማ1 ÷ 21

መዝሙር
አምላክ ለኛ ብሎ
አምላክ ለእኛ ብሎ ቢያፈሰው ደሙን
ለምን ከለከለች ፀሐይ ብርሃኗን
የከበረው ሥጋ የከበረው ደም
በመስቀል ላይ ዋለ ኢየሩስዓሌም
እዩት ኢየሱስን መስቀሉ ማማረ
ስተመራመረው ብዙ ነው ምስጢሩ
ቢመቱት ቢሰቅሉት ቢያሳግጡበት
ምንም አላገኙ ከእርሱ ዘንድ ስህተት
ፍጣሪ መሆኑ ምስጢሩ ገብቷት
ጌታን አልይዝም አለች ግውዟ መሬት
እዩት ኢየሱስን.....
ይህ ታላቅ ንጉሥ ሲገለጽ በሠማይ
የናቁት የወጉት ይሉስታል ዋይ ዋይ
ምድርና ሰማዩ ከፊቱ ሲሸሹ
ወዴት ልግባ ይላል ትልቁ ትንሹ
እዩት ኢየሱስን.....
ወደ ሰማይ ያረገው የከበረው ስጋ
ዳግመኛ መምጣቱን ሁላችን እንዘንጋ
በሰማይ ለሚኖር ቅዱስ አባታችን
ምስጋና ይደረሰው ከኛ ከሁላችን
እዩት ኢየሱስን.....

ጥቅስ፡ ማር15÷1-39 ዮሐ1÷1-11
ማቴ24÷29-51

መዝሙር
ከመቶ በግ አንዱ
ከመቶ በግ አንዱ ቢጠፋው አዳም
ሲፈልገው መጣ መድኃኔዓለም
ባገኘውም ጊዜ በጣሙን ደስ ስሎት
ወደ ቀድሞው ቦታ ሔደ ተከትሎት
ቸሩ አረኛችን ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ
በቶሉ ፈልገን ወዳንተ አንድንመለስ
ጥቅስ፡ ማቴ18÷11-14

መዝሙር
ምድረ ቀራንዮ ከጧት እስከበርክ
ምድረ ቀራንዮ ከጧት እስከ ሰርክ(2)
የሾህ አክሊል ደፍተህ በመስቀል ላይ ዋልክ
በቀራንዮ ጐልጐታ
ገላህ በመስቀል ተመታ
ስላለም ቤዛ ብለህ
ራስክን ለሞት ሰጠህ
ምድረ ቀራንዮ.....
እንደ ወንበዴ ታስረህ
ሲችነክሩህ አጅና አግርህ
ስጠላቶችህ ክፋ አላሰብክ
ይቅር በላቸው ነው ያልክ
ምድረ ቀራንዮ.....
ይሁደ ሞኙ ተላላ
ጌታውን ሸጦ ሲበላ
ገንዘብን ብቻ በመውደድ
ገመድ ሆናቸው ዘመድ
ምድረ ቀራንዮ.....
በዕለተ አርብ ስድስት ሰዓት
ጌታ በመስቀል ሲውልላት
በግራ በቀኝ ፈያት
መካከል አርሱን ሰቀሉት
ምድረ ቀራንዮ.....
በኪሩቤል ላይ የሚኖር
በቀራንዮ ተሰቀለ ለአዳም ክብር
አንደ ወንበዴ ተገረፈ
ሥጋው አለቀ ተገፈፈ
ምድረ ቀራንዮ.....
አገኘን ብለው የሙት ልብስ
ተከፋፈሉት የርሱን ቀሚስ
እርሱን ሲሰቅሉ ጐልጐታ
ወንበዴው በርባን ተፈታ
ምድረ ቀራንዮ.....
ጥቅስ፡ ማቴ27÷1-

መዝሙር
ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን
ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን አባት ሆይ
በመስቀል ሆነህ "
ድምጽን በማሰማት "
ነፍስህን ሰጠህ "
የሰማይ ከዋክብት በሙሉ እረገፉ
ጨረቃና ፀሐይ ደምን አጐረፉ
ብርሃናት ጨለሙ ጠፋተው ተስያዩ
ሥጋህ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ስላዩ
ዘጠኝ ሰዓት.....
ጌታችን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ
አሰምቶ ጮኽ ተጠማሁ አያለ
ማርና ወተትን ለሚመግበው
ሀሞት አጠጡለት ይቀመሰው ብለው
ዘጠኝ ሰዓት.....
አካሉ ሲወጋ ውሃ ደም ፈሰሰ
በምድር ተረጭቶ ዓለምን ቀደሰ
የእሥራኤል ሴቶች ዋይ ዋይ ሲሉልህ
ለእነርሱ አዘንክ አንጂ ለአንተስ አላሰብክም
ዘጠኝ ሰዓት.....
እናትና ስታለቅስ ከመስቀል ሥር ሆና
ዮሐንስን ሰጠ ጠብቆ አንዲያጽናና
መላእክትም ታዩ አጋንንትም ሸሹ
የአይሁድ ሠራዊት ፈርተው ተረበሹ
ዘጠኝ ሰዓት.....
ጥቅስ፡ ማቴ27÷45 ማር15÷33-39

መዝሙር
ሥጋህ ሕይወታችን
ሥጋህ ሕይወታችን ለነፍስ ለስጋችን
አምላክ አንተ ነህ መድኃኒታችን
ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ባንድነት ተባብረው
ሥጋህን ለማውረድ ሲቀብሩህ አስበው
ጥያቄ አቀረቡ ከመሥፍኑ ቀርበው
ሥጋህ ሕይወታችን.....
አውርደው ቀበሩህ በአዲስ መቃብር
ቅዱስ ቅዱስ ኃያል እያሉ በከብር
ንጹህ በፍታ አመጡ እንዲሆን መግነዝ
ሥጋህ ሲጠቀለል በሰንዱን ሲያዝ
ሥጋህ ሕይወታችን.....
ተቀብሮ የሚቀር የሚበሰብስ
መስሏቸው ነበረ በመቃብር ከርስ
ቅዱስ አፀ መስቀል የኛ መድኃኒት
ክብርን አግኝተህል በዚያች ሰዓት
መስቀል ኃይላችን.....
የከበረ ደሙ ባንተ ላይ ቢፈስ
ሆነህል መመኪያ ለሕሙማን ፈውስ
በሲኦል ተጥለን በዚያ እንዳንገዛ
ክርስቶስ ሆነልን ለፍጡራን ቤዛ
መስቀል ኃይላችን.....
ጥቅስ፡ ማቴ27÷57

መዝሙር
አልፋና ኦሜጋ
አልፋና ኦሜጋ ፈጣሪ የሆንክ
በከሀዲዎች እጅ ተይዘህ ቀረብክ
ተገፋህ ተደፋህ በጥፊ ተመታህ
እየደበደቡ ክርስቶስ ሆይ አሉ
ጽድቅን ስለሰራህ በወንጀል ከሰሱህ
ለአዳም ቤዛ ብለህ ብዙ ተንገላታህ
አልፋና.....

ቅዱሳን አጾችህ የፈጥኝ ታስረው
አንደ በግ ተጐተትክ ልትምራቸው
የትም ቦታ ያለህ ሁሉን የምታውቅ
ፊትህን ሸፈኑህ ለመመፃደቅ
አልፋና.....
በአውደ ምኩና በጲላጦስ ዘንድ
አሳልፈው ሰጡህ አጋልጠው ለፍርድ
ከሀና ቀያፋ ከካህናቱ ደጅ
ከነሄሮድስ ዘንድ አቀረቡህ በአዋጅ
አልፋና.....
ግርፋት ሕማሙ አልበቃ ብሎህ
በመስቀል ላይ ልትውል ተፈረደብህ
ሳዶር አና አሳዶር ዳናትና አዴራ
ተፈልገው መጡ ለችንካር በተራ
አልፋና.....
የሠላም ባለቤት ደረትህ ተወጋ
ሲያያዝ በችንካር እጅህ ተዘረጋ
ግፈኞች አይሁዶች ባንተ ላይ ቀለዱ
ምራቅን ተፋብህ አንተኑ ሲጐዱ
አልፋና.....
ጥቅስ፡ ማር 15÷42-47

መዝሙር
ድንግል የዚያን ጊዜ
ድንግል የዚያን ጊዜ (2)ሐዘንሽ በረታ(2)
በመሰቀል ላይ ሆኖ ልጅሽ ሲንገላታ(2)
የግፍ ግፍ ደርሶበት የዚያን ጊዜ
ተጠማሁ ሲልሽ
ስውሻ ያጠጣሽ በወርቅ ጫማሽ(2)
ሴቶች ሲያባርሩት የዚያን ጊዜ አራርቶ ሆድሽ
ስፍጡር በማዘን ውሃ ያጠጣሽ(2)
ተጠማሁ እያለ የዛን ጊዜ ሲናገር ልጅሽ
ታዲያ አንደምን ቻለ ወላድ አንጀትሽ(2)
አንደዚያ ስታስቅሽ የዚያን ጊዜ ሀዘን ሲውጥሽ
አነማን ነበሩ ያስተዛዘኑሽ(2)
ስታስቅሽ በማየት የዛን ጊዜ ራርቶ ልጅሽ
ዮሐንስን አጽናኝ አንደ ልጅ ሰጠሽ(2)
ድንግል የዛን ጊዜ (2)ሐዘንሽ በረታ
በመሰቀል ላይ ሆኖ ልጅሽ ሲንገላታ(2)
ጥቅስ፡ የሐ19÷19-25

መዝሙር
በሰንበት ገባ ወልድ
ሠላም በመስቀልህ ወልድ ባለው ጎልጎታ
ዐርብ ዕለት ለዋልህ " ከቀትር እስከማታ
አቤቱ ቸርነትህ " ስናስታውስ አሁን
በጣም ይገርመናል " መታገስህ ሁሉን
በሰንበት ገባ ወልድ
ምኩራበ አይሁድ
በአይሁድ አደባባይ ወልድ ከጲላጦስ ዘንድ
አቁመው ከሱቡህ " አጋልጠው ለፍርድ
ቀራንዮ አንስተው " ወደ ጎልጎታ
ብዙ አመላለሱህ " አንድትንገላታ
በሰንበት ገባ ወልድ .....
ይህ ሁሉ ግርፋት ወልድ ስላላረካቸው
ደረትህን ወጉት " በመጨከናቸው
ሁሉን ማድርግ ስትችል " የምህረት አምላክ
በመስቀል ተሰቅለህ " በቀራንዮ ዋልክ
በሰንበት ገባ ወልድ .....
የባሕርና የሐይቅ ወልድ የቀላያት ጌታ
ሳንተ ከለከሉህ " የውኃ ጠብታ
አናትህ ውሳለች " አንባዋን ስታፈስ
አንጀታ አልችል ብሎ " ስላንተ መወቀስ
ብቻዋን አንዳትሆን " ሆድ አንደይብሳት
ዮሐንስን አጽናኝ " ሲሆን ሰጠሃት
በሰንበት ገባ ወልድ .....
በቀራዮ ላይ ወልድ መስዋእት ሆነህ
ሥጋና ደምህን " ቀድሰህ ሰጠህ
መስቀል ኃይል ነው " ለሁሉም ግሩም
ሠላምህን ስጠን " መድኃኔዓለም
በሰንበት ገባ ወልድ .....
ጥቅስ፡ ሉቃ23÷1-31

መዝሙር
ወይቤ ኤሎሄ
ወይቤ ኤሎሄ ኤሎሄ
ላማ ሰበቅታኒ አልማሰ ዘበዕይ አይሁድ ተአሰረ
አመድማ ማይ ይአቲ ሀሞተ ወከርቤ መሪረ
አንቃዕዶ ሰማየ ጎበ አቡሁ ነገረ
ሶበ መንፈሱ ትውጽዕ በላዕለ መስቀል ገብሩ
ወይቤ ወይቤ ተፈፀመ ኩሉ
ትርጉም፡ በአይሁድ እጅ ታስሮ አምላኬ አምላኬ ሲል በተጠማ ጊዜ መሪራ የሆነ ሐሞትና ከርቤ ጠጣቀና ብሎም ወደ ሠማይ ወደ አባቱ ተመለከተ በመሰቀል ላይ ሆኖ ነፍሱን ከስጋው በሚለይበት ጊዜም ሁሉ ተፈፀመ አለ።
ጥቅስ፡

መዝሙር
አመ ይሰቅልዎ
አመ ይሰቅልዎ አይሁድ ለእግዚእነ ሚካኤል አርመመ
ወገብርኤል ተደመ(2)
ፀሐይ ፀልመ ወወርህ ደመ ኮነ ወሪዶ አመስቀሉ ለኩሉ
አብርሃ(2)
በሰቀሉት ጊዜ አይሁድ ጌታችንን ሚካኤል ዝም አለ
ገብርኤልም ተደነቀ(2)
ፀሐይ ጠቆረ ጨረቃም ደም ሆነች ከመስቀሉ ወርዶ
ለሁሉ አበራ(2)
ጥቅስ፡ ሉቃ23÷44-49

መዝሙር
መድኃኔዓለም ዘቆምከ
መድኃኔዓለም ዘቆምከ በቅድመ ጲላጦስ
መድኃኔዓለም ዘቆምከ በአውደ ሔሮድስ
ቀራንዮ (2) በዚያች ቦታ
ቀራንዮ (3) ምድረ ጐልጐታ
እጅ እግርህ ታሰረ በራስህ ፈቃድ
ተገፋ ተደፋህ በዕይ አይሁድ
ለሸክም ዳረጉህ የማይቻል ግንድ
መድኃኔዓለም ዘቆምከ.....
እናቶች ሲያለቅሱ ስላንተ መከራ

ሕማምህ ድካምህ ደምህም ሲዘራ
የራሔልም ለቅሶ በነርሱ ደረሰ
ሐዘን ተሰማቸው አንባቸው ፈሰሰ
መድኃኔዓለም ዘቆምከ.....
አይሁድ ባሰባቸው ያዛቸው ጭካኔ
ምራቅን ተፋብህ ገረፋህ ወይኔ
ዳዊት አስቀድሞ አንደተናገረ
አገቱኒ አያለ ትንቢት ተናገረ
መድኃኔዓለም ዘቆምከ.....
ጥቅስ፡ ዮሐ19÷1

መዝሙር
ኪርያላይሶ
ከርያላይሶን(3)
በሰማይ በምድር ሥልጣኑ ያለህ ከርያላይሶን
በፍርድ አደባባይ አንተን አቆሙህ "
አኛን ለመሰብሰብ ምራቅ ተፋብህ "
ከርያላይሶን.....
የተንኮልን ነገር አንዳች ቢያጡብህ ከርያላይሶን
ይህ ይሳደበል ብለው ከሰሱህ "
አሳተ መለኮት ዓለምን የፈጠርህ "
ሥጋ በመልበስህ በጥፊ ተመታህ "
ከርያላይሶን.....
ውሆችን ቀድሰህ አንዳልሰጣሀቸው ከርያላይሶን
ጥም ቢበረታብህ ጨከነ አንጀታቸው "
አንተ በባህሪህ ሁሉን ቻይ ሆነህ "
በመስቀል ቸንክረው ቀራንዮ ሰቀሉህ "
ከርያላይሶን.....
የአኛውን ግርፋት ተገረፍህልን ከርያላይሶን
ሸክም ቁስላችንን የተቀበልህልን "
ኤሎሄ ኤሎሄ የሲቃ ድምጽህ "
ዛሬም ይሰማናል የጥሪ ቃልህ "
ከርያላይሶን.....
ሰቃይህን አስታውሰን አናነባለን ከርያላይሶን
የምሕረት እጆችህን እንዲዳብሱን "
ስለኛ መከራን እንደተቀበልክ "
አሁንም ደግፈን አንዳንጠፋብህ "
ከርያላይሶን.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
እመቤቴ ማርያም ወየው እያለች
እመቤቴ ማርያሙ ወየው እያለች
አምርራ አለቀሰች አየተደፋች ወየው አንድ ልጇ
በመስቀል ላይ ሆኖ ስቃይ በዝቶበት
አልችልላት ብሎ የወላድ አንጀት
አርቃኑን ሰቅለውት ሲሳለቁበት
ደመ ነው ያለቀሰች አንባዋ አልቆበት ወየው
አንድ ልጇ
ዘመዴ ኤልሳቤጥ አረ ወዴት ነች
አንድታላቅሰኝ ወየው እያለች
አህቴ ሰሎሜ ወዴት ነው ያለሽው
በግብጽ በረሃ አብረሽኝ የዞርሽው ወየው አንድ ልጇ
የመረረ ሃዘን ዛሬ ደርሶብኛል
ልጇን አንገላተው ገርፈው ሰቅለውታል ወየው
አንድ ልጇ
በመስቀሉ ሥር ሆና አለቀሰች
ወየው መድኃኒቴ ወየው እያለች ወየው አንድ ልጇ
ተጠማሁኝ ስትል ጡቴን ጨነቀው
አንደ ልጅነትህ ባጠባህ ምነው ወየው አንድ ልጇ
አልችልላት ብሎ የወላድ አንጀት
አርቃኑን ሰቅለውት ሲሳለቁበት
ምን ብላ አለቀሰች የጌታዬ አናት ወየው አንድ ልጇ
አንድ ልጇ አኮ ነው የሌለው አህት
አንድ ልጇ አኮ ነው የሌለው ወንድም
አረ አንዴት ልቻለው መድኃኔዓለም ወየው አንድ ልጇ
ጥቅስ፡ ሰቆቃ ወድንግል

መዝሙር
ምድረ ገልገታ
ምድረ ገልገታ ሲቶስትራ ሆይ
የዓለም መድኃኒት ያየብሽ ስቃይ
መቼ ልጇን ብቻ አይሁድ የገረፋት
የአናቱንም ልብ በሀዘን የቀጠቀቱት
ኧረ ምን አልሽ ይሆን ከቶ የዚያን ለታ
የሠራዊት አምላክ በዚያ ሲንገላታ
ምድረ ገልገልታ.....
ተጠማሁ ሲላቸው ሲሰጡት አሬት
ምን አሉ ጡቶችሽ ጌታን የጠቡት
አጥንቱ እስከሚታይ በሾመል ሲመቱት
ከቶ ምን አልሽ ይሆን አርቃኑን ሲሰቅሉት
ምድረ ገልገልታ.....
የአናትነት ልብሽ ጭካኔ ያስመደው
የሀዘን ሰይፍ አሳት ውስጥሽን ሲያነደው
አመቤቴ ሀዘንሽ አንደምን መራር ነው
የቀራንዮ ውሎሽን በአምነት ስናስበው
ምድረ ገልገልታ.....
የአናቱንም ሀዘን ልቡል ተመልክቶ
የፍቅር ዓይኖቹን በአንባ ተሞልቶ
ብታለቅሽ ብታለቅሽ አይደክምሽም ወይ
አስኪ ለአንድ አፍታ አናቴ ዝም በይ
ብሎ አለቀሰ በለበለው ስጋ
በመስቀል ላይ ሆኖ አልፋና ኦሜጋ
ምድረ ገልገልታ.....
አቤት የሰዎች ልብ አንደምን መራር ነው
በመስቀል ላይ ታስሮ ፍቅሩ የማይገዛው
በል አንዲሁ ማረን የኛን ተወውና
ቁም ነገር የማያውቅ ሥጋ አልቦ ነውና
ምድረ ገልገልታ.....
ጥቅስ፡ ሉቃ23÷28-29

መዝሙር
ወአንተኒ ቀራንዮ
ወአንተኒ ቀራንዮ መካነ ገልጎታ ይቤ(2)
አስመ በንቤኪ (2)ተሰቅለ መድኃኔዓለም(2)
ትርጉም፡ አንቺ ቀራንዮ መካነ ጉልጎታ የተባልሽ በአንቺ
መድኃኔዓለም ተሰቀለ::

ጥቅስ፡ ማቴ27÷

መዝሙር
ለካስ ጌታ ነው የሞተው
ለካስጌታ ነው የሞተው የተቀበረው
መስቀል ተሸክሞ ተራራ የወጣው
የአዳምን ድግስ ሞት ጸዋ የጠጣው
አዬ አዬ
ለካስ ጌታ.....
በአይሁድ ሸንጐ ፊት የተንገላታው
ምራቅ ተተፋቶበት በጥፊ የተመታው
አዬ አዬ
ለካስ ጌታ.....
እንደ ነፍሰ ገዳይ ተሰቅሎ የዋለው
የዓለም መድኃኒት ድውይ ፈዋሽ ሳለ
አዬ አዬ
ለካስ ጌታ.....
ፀሐይ ቢችግራት አይኖቿን ከደነች
የጌታዬን እርቃን እኔ አላይም አለች
አዬ አዬ
ለካስ ጌታ.....
የሾህ አክሊል ደፍቶ በእግር ብረት ታስሮ
ያልሰማ ይሻላል የአናቱን እሮሮ
አዬ አዬ
ለካስ ጌታ.....
ጥቀስ፡ ሉቃ 23÷26-49

መዝሙር
ተፈጸመ አለ
ተፈጸመ አለ ጌታ ነፍሱን ሰጠ
ስለእኔ ኃጢአት በመከራ አለፈ
በግፍ ተሰቃየ ፍዳን ተቀበለ
ተገርፎ ተሰቅሎ ቀራንዩ ዋለ
ደፋ ቀና አያለ ሲወድቅ ሲንገላታ
የብርሃን ፊቱ በጥፊ ተመታ
ተፈፀመ አሌ.....
በሐሰት ተከሶ በሐሰት ተገደለ
በፍርድ ሸንጎ ፊት በአደባባይ ዋለ
በውኃ ጥም ዛለ በረሃብ ተቀጣ
ስለ ሰው ልጅ ሲል የሞት ጽዋን ጠጣ
ተፈፀመ አሌ.....
አንቺ ዕለተ አርብ እንዴት ያለሽው ነሽ
ሰማያዊ አባት የተሰቀለብሽ
ከኋላ ከፊቱ በጠላት ተከቦ
ማንም አልነበረ የሚያጽናናው ከቶ
ተፈፀመ አሌ.....
ሩጎሩጎ ጌታ ስለ እኔ ብለህ
ያን ሁሉ ፈተና በትዕግሥት ያለፍክ
ተፈፀመ አሌ.....
ጥቀስ፡ ዮሐ19÷1-30

መዝሙር
ፀሐይም ጨለመች
ፀሐይም ጨለመች ጨረቃም ደም ሆነች
ያልበደለው ንገሥ ተሰቅሎ ስላዩች
ዋ እኔን ዋ እኔን ለእኛ ይገባል ለቅሶ
በእኛ በደል አርሱ አካላቱን ክሶ
ጠላቶቹን ሁሉ ከማጥፋት ታግሶ
እነሆ ተሰቅሏል ከለሜዳ ስብሶ
ክርስቶስ ንፁሕ ሲሆን ቅዱስ ሲሆን ሐሰት ሳይኖር በቃሉ
እነሆ እዩት ተሰቅሎ ደሙ ይዘንባል ካካሉ
የሚያምንበትን ሰው ሊያድነው ነው አሉ
ቤዛቸው ነው እና ስዓለሙ ሁሉ
ስለኛ ተሰቀለ እንዳሁም ሞተልን
በበደልነው ክሶ እኛን ሊያድነን
ፀሐይም ጨለመች...
ጥቀስ፡ ማር15÷33 ሮሜ5÷21

መዝሙር
ምድረ ቀራንዮ ምድረ ጎልጎታ
ምድረ ቀራንዩ ምድረ ጎልጎታ
መድኃኒት ክርስቶስ በአንቺ ተንገላታ
የዓለም መድኃኒት በአንቺ ተንገላታ
መስክረ አንቺ ምድር ግፁዚቷ ስፍራ
የዓለም መድኃኒት በአንቺ ተንገላታ
ደሙ እንደ ውኃ ሲወርድ መስቀሉ ላይ
መከራን ሲቀበል በዚያች ምድር ላይ
ምድረ ቀራንዮ.....
አጅቱና እግሮቹ በችንካር ተመተው(2)
ይቅርታን አድርጐ ስዚያ ኃጢአታቸው(2)
ሁሉን ማድረግ ሲችል ሥልጣን ሲኖረው(2)
በቀራንዮ መስቀል ፍቅሩን አዋለው(2)
ምድረ ቀራንዮ.....
መከራ በተራ ሲፈራረቅበት(2)
በደልን አልሰራም ምንም ዓይነት ስህተት(2)
ከሰማያት ወርዶ እንዲህ መዋረዱ(2)
የኛን በደል ኃጢአት ክርስቶስ መውሰዱ(2)
ምድረ ቀራንዮ.....
ፀሐይ ከለከለች ከመስጠት ብርሃን(2)
ስመሸፈን ብሳ የአምላኳን አርቃን(2)
በመስቀል ላይ ሆኖ ተጠማሁ አያለ(2)
ተገርፎ ተሰቅሎ ቀራንዮ ዋለ(2)
ምድረ ቀራንዮ.....
በቆረስከው ስጋ ባፈሰስከው ደም(2)
አቤቱ ተራዳን አስከ ዘለዓለም(2)
ቸሩ መድኃኔዓለም አባክህ ማረን(2)
ደካሞች ነንና እንዳንቀር ወድቀን(2)
ምድረ ቀራንዮ.....
ጥቀስ፡ ማቴ27÷1 1ኛጴጥ2÷22-24
መዝ 21÷16-18 ዮሐ6÷53

መዝሙር
ስለእኛ ብሎ
ስለ እኛ ብሎ ልጅሽ ተሰቅሎ
ልብሽ በሀዘን ተወቅቶ ቆስሎ
ከመስቀሉ አውርደውት
ዮሴፍ ኒቆዲሞስ ገንዘውት
ያለቀሽው የእንባሽ ብዛት
ይጠብልን የእኛን ኃጢአት(2)

ጥቀስ፡ ዮሐ19÷25-27

መዝሙር
የድኀነታችን ቀን
የድነታችን ቀን አንቺ አስተ አርብ
አፁብ ነሽ ድንቅ ነሽ የሠላም ኮከብ
ሕይወት አግኝተናል ድኀነትና ሠላም
ስለተሰዋብሽ አምላክ መድኃኔዓለም
አንዴት ተፈፀምሽ አንቺ ዕለት
ከቶ ምን አየሽ የዛን ሰዓት
ፈጣሪሽን ይዘው አይሁድ ሲሰቅሱት
በችንካር እጆቹን ሲቸነክሩት
አሾህን ጉንጉነው አክሊል ሲያቀዳጁት
ሲስቁበት ሲሳለቁበት
አንዴት ሰነበትሽዮ.....
ከዋክብት ሲረግፉ ፀሐይ ስትጨልም
የፈጣሪን አርቃን አንዳናይ ሁሉም
ብርሃንን ሲነፍጉ ዓለም ሲጨልም
ግፁሟ ጨረቃ አዝና ሆና ደም
አንዴት ሰነበትሽዮ.....
ሙታን ሲነሱ ሲሰነጠቅ ዓለት
የመቅደስ መንጦላት ሲከፈት ለሁለት
ዓለም ስትሸበር ሲጠፋባት ውሳ
መላዕክት ተገርመው ሁሉን ሲያስተውሉ
አንዴት ሰነበትሽዮ.....
ጥቅስ፡ ማር15÷33

መዝሙር
ቃል ሥጋ ነበሰ
ከሦስት አካል አንዱ ቃል ስጋ ለበሰ
ማረን(6)
አዳም በበደለው መድኃኔዓለም ካሰ
በኛ ኃጢአት እርሱ ተከሰሰ
ማረን ይቅር በለን
ሁሉን የምታውቅ የዓለም ጌታ ክርስቶስ
አግዚኦ አግዚኦ
አልፋና ኦሜጋ የዓለም ቤዛ የዓለም ፈውስ
አግዚኦ አግዚኦ
ሞትን አጠፋልን ሰጠን አዲስ ሕይወት
ማረን(6)
ባለ ተስፋ አረገን ለዘለዓለም ሕይወት
ማረን(6)
በደሙ <u>ሰራልን</u> አዲስ ስነ ስርዓት
ማረን ይቅር በለን
ሁሉን የምታውቅ የዓለም ጌታ ክርስቶስ
አግዚኦ አግዚኦ
አልፋና ዓሜጋ የአለም ቤዛ የዓለም ፈውስ
አግዚኦ አግዚኦ
ተወቀሰ ቆሞ ከጲላጦስ ደጃፍ
ማረን(6)
ከትዕግሥት በቀር አላሳየም ፀያፍ
ማረን(6)
አምላክ በመሆኑ አነዛን ከአድፍ
ማረን ይቅር በለን
ሁሉን የምታውቅ...
ጥቅስ፡ ሉቃ18÷31-34

መዝሙር
ሰቀሉህ ምስሌሁ
ሰቀሉ ምስሌሁ ክሲኤተ ፈያተ(2)በየማኑ ወበፀጋሙ(2)
ወበ ማእከሉሙ(2)ኢየሱስ(2)
ትርጉም፡ ከእርሱ ጋር ሁለት ወንበዴዎችን በቀኝና
በግራ ሰቀሉ በመካከላቸውም ኢየሱስ አለ።
ጥቅስ፡ ማቴ 27÷28

መዝሙር
እፎ ሰቀሉከ
እፎ ሰቀሉከ ካሕናተ ይሁዳ ወሌዊ(2)
መድኃኔዓለም ናዝራዌ(4)
ትርጉም፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስን የአይሁድ ካህናት
እንደምን ሰቀሉህ
ጥቅስ፡ ማቴ27÷42-44 ማር15÷31-32

መዝሙር
ዘአልበስዎ
ዘአልበስዎ አይሁድ ከለሜዳ(2)
እኁ ከለሜዳ ዘለይ (2)ከለሜዳ(2)
ትርጉም፡ አይሁድ ጌታችንን ቀይ ግምጃ አለበሱት
ጥቅስ፡ ማቴ 27÷27-

መዝሙር
ሞተሀልና ስለእኔ
ሞተሀልና ስለእኔ ምንም ሳይኖርብህ ጥፋት
ተከሰህ ተወቅሰህ በጲላጦስ ፊት
ኢየሱስ አምላክ ምሕረት ስብሐት ለከ(2)
ያንተ መንገላታት ሁል ጊዜ ያሳዝነኛል ሲወሪ
በመስቀል ላይ ሆነህ ያየህው መከራ
ኢየሱስ የሕይወት አንጀራ ስብሀት ለከ(2)
ከልዑል ቦታ ዝቅ ብለህ ፈጣሪ ፍጡራን አምላክ
በሰው ፊት ተዋርደህ ስለሰው የሞትክ
በመስቀል ላይ ተጠማሁ እያልክ ስብሃት ለከ(2)
ክፋ አድራጌዎች ተነስተው በምቀኝነት መንፈስ
ብዙ ሲጣጣሩ ደምህን ለማፍሰስ
ሞትክላቸው ደስ እንዲሳቸው ስብሃት ለከ(2)
መሐሪ ጌታ አሁንም እንደቸርነትህ ብዛት
የኛን በደል ኃጢአት ሳትመለከት
አድነን ከዳግም ሞት ስብሃት ለከ
ጥቅስ፡ ማቴ 27÷ ዮሐ19÷

መዝሙር
ሙታንን ያድን ዘንድ
ሙታንን ያድን ዘንድ የሞት ሞትን ሽሮ
ወልደ አምላክ ሄደ ወደ ኃላ ታስሮ
ግርማን ለኪሩቤል ያጎናፀፋቸው
ዘውድን ለሱራፌል የሚያቀዳጃቸው
ከለሜዳ ስብሶ ዋለ ከፈታቸው
ሙታንን.....
ቅዱሳን አጆቹ አዳምን የሰሩ
ቅዱሳን አግሮቹ በገነት የዘሩ
ተቸንክረው ዋሉ በጠንካራ ብረት
ሙታንን.....
አዳም በበደለ የግፍ ግፍ በሠራ
ቸሩ ወልደ አምላክ ዋለ በመከራ

ሙታንን.....
ምን በበደስ ነው ምን ባደረገ ነው
ወልድ አንደቀማኛ ሲገረፍ የዋለው
ሙታንን.....
በምን አስታገሰህ በምን ቻስ ሆድህ
ትልቁም ትንሹም ሲዘባበቱብህ
ሙታንን.....
ጥቅስ፡ ዮሐ 19÷1 መዝ21÷16

መዝሙር

<u>መድ≠ኄዓለም አዳነን</u>

መድ≠ኄዓለም አዳነን በማይሻር ቃሉ (2)
እ, ደስ ይበለን (2) እልል በሉ (2)
እዳነን በማይሻር ቃሉ (2)

መዝሙር
ችሩ ሆይ
ችሩ ሆይ (2) ስአኛ ብለህ ተሰቀልክ ወይ
ሔዋን ብትበድል <u>አንዲህ አንደዋዛ</u>(2)
መጣ ተሰቀለ <u>የዓለሙ ቤዛ</u>(2)
ችሩ ሆይ.....
የተከሰስክበት <u>ወንጀሉ ሲወራ</u>(2)
ለምፃም ስላዳነ <u>አውር ስላበራ</u>(2)
ችሩ ሆይ.....
አንካሳ ማዳኑን <u>ማቅናት ጎባጣውን</u> (2)
በፍቅር ተገዶ <u>ስለሰው መሞት (2)</u>
ችሩ ሆይ.....
ባሕል ለውጧል <u>ሰንበትንም ሽሯል (2)</u>
ይህ በደለኛ ነው <u>መሞት ይገባዋል(2)</u>
ችሩ ሆይ.....
ጥቅስ፡ ዮሐ5÷18 ዮሐ19÷4-7

መዝሙር
በመስቀል ተሰቅለህ
በመስቀል ተሰቅለህ የሞትክልን ጌታ
ብድርህ ምንድን ነው ወሮችህ ምንድን ነው
ለአንተ ውለታ
አንካን መክፈል ቀርቶ ብድር ውለታህን
ለአኔ አይቻለኝም መፈፀም ቃልህን
አኔ የማልጸዳ ታጥቦ ጭቃ ነኝ
ከትአዛዝህ አንዱ ለመፈፀም የተሳነኝ
በመስቀል .....
አንተን ከማስከፋት ከማሳዘን በቀር
ምንም ደግ ሥራ የሌለኝ ነኝ አኔ ከንቱ ፍጡር
ስለዚህ አምላክ ሆይ በደሌን ደምስሰህ
ልቤንም ቀስቅሰው ላንተ አንዲገዛልህ
አድርገኝ ምርጥ አቃ ያንተ መገልገያ
ከኃጢአት ባርነት አውጣኝ ከዲያብሎስ ጉያ(2)
ጥቅስ: ዮሐ14÷15-23

መዝሙር
በሞት ጥሳ ወድቀን
በሞት ጥሳ ወድቀን ስንከራተት(2)
በረቀቀ ፍቅሩ ዋጀን ከጥፋት(2)
በጎልጎታ የታየው ፍፁም መድኃኒት
ሀሌ ሀሌ ሉያ ላንተ ስኃያሉ ጌታ(2)
ስለኛ ተዋረድክ በጎልጎታ
የሞት ሸክም ከብዶን በጣር ስንባዝን(2)
ወረደ ከሰማይ መጣ ሊያግዘን(2)
ከባረነት ሸክም ሊገላግለን
በሞት ጥሳ ወድቀን .....

ምንም ባልበደለ ምንም ባላጠፋ (2)
ሁሉን ማድረግ ሲችል <u>ደካማ የሆነው</u>(2)
ሕይወትን ሊያስድለን ለመደደ ነው
በሞት ጥሳ ወድቀን .....
አለኪ አለተውሉ <u>የፈቀሩን ብዛት</u>(2)
ለመስቀል ሞት ታዞ <u>አኛን ያዳነበት</u>(2)
ምንም አቻ የለው የጌታ ችሪነት
በሞት ጥሳ ወድቀን .....
ጥቅስ:

መዝሙር
የትንሣኤው ብርሃን
የትንሣኤው ብርሃን የሰው ልጅ ሕይወት(2)
አዳምን መስሰው ከወጣበት ቤት (2)
አሰይ የምሥራች ደስ ይበላችሁ
ሞትን ድል አድርጐ ተነሳላችሁ(2)
ያ በሙሴ አሪት የተነገረው(2)
ሞትን ዛሬ አጥፍቶ የተነሳው ነው(2)
አሰይ የምሥራች.....
ማርያም መቅደላዊት ምንኛ ታደልሽ(2)
ከሰው ሁሉ በፊት ትንሣኤን አየሽ(2)
አሰይ የምሥራች.....
ብርሃን ያሳየዋል የጽድቅንም ፋና(2)
ስሚገዛለቱ በእውነቱ ጐደና (2)
አሰይ የምሥራች.....
ስምህን ተናገርክ ሁሉን ተቀበል (2)
ከጥፋት ልጅ በቀር ማንም አልታጐለ(2)
አሰይ የምሥራች.....
አባት ሆይ በጽድቅህ ባርከህ ቀድሳቸው(2)
ከጥፋት ልጅ በቀር ሁሉም ያንተው ናቸው(2)
አሰይ የምሥራች.....
አንድ ይሁኑ እነርሱ በሰላም በፍቅር(2)
እኔም አንድ እንደሆንኩ ካንተው ከአባቴ ጋር(2)
አሰይ የምሥራች.....
ጥቅስ፡ ዮሐ17÷23-43

መዝሙር
ተገርፎ ተሰቅሎ
ተገርፎ ተሰቅሎ የሞተው አንበሣ
ተገንዞ በጨርቅ ተቀብሮ እንደሬሳ
በሞት እጅ ተይዞ አልቀረም ተነሳ
እናምናለን ትንሣኤህን
በሥልጣንህ መነሣትህን
አርአያ ነውና ለሁላችን
አፈር ቢረበረብ ሣጥን ቢደረደር
ድንጋይ በድንጋይ ላይ ደግሞም ቢነባበር
ምድር አልቻለችም አምላክን ለመቅበር(2)
እናምናለን .....
አምላክ ስትነሳ ፈርሶ መቃብሩ
ሴቶች ትንሣኤህን ደፍረው ተናገሩ
እንሞታለን ብለው ማንንም ሳይፈሩ(2)
እናምናለን .....
እንግዲህ አልፈራም ሞትና ኩነኔ
አምላክ ከሞተልኝ ተሰቅሎ ስለኔ
ተደምስሷልና የሞት ስልጣኔ(2)
እናምናለን .....
ጥቅስ፡ ሉቃ24÷5

መዝሙር
ሃሌ ሉያ እዳና በደልን
ሃሌ ሃሌ ሉያ እዳና በደልን (2)
በመስቀሉ አጥፍቶ
ነፍሳትም ከሲኦል አውጥቶ (2)
ሃሌ ሃሌ ሉያ ሰላምን ሠራልን (2)
በመስቀል ላይ ሆኖ
መነሣቱን በግልጽ አሣምኖ (2)
ሃሌ ሃሌ ሉያ ህያው ተንስአ (2)
ሞትን በሞት ሽሮ
ጠላትንም በመስቀል ሰባብሮ (2)
ሃሌ ሃሌ ሉያ እንዘምር ሁላችን (2)
ለአምላካችን በአዲስ መንፈስ
ስላዳነን በሥጋ ወበነፍስ (2)
ጥቅስ፡ 1ጴጥ 3÷19

መዝሙር
ትንሣኤከ
ትንሣኤከ ለአለ አመነ(2)
ብርሃነከ ፈኑ ዲቤነ(2)
ትንሣኤህን ለአመንን ለአኛ (2)
ብርሃንን ላክልን ወደአኛ (2)
ጥቅስ፡ ዮሐ 20÷14

መዝሙር
አምላካችን አዳነን
አምላካችን አዳነን በማይሻር ቃሉ(2)
እኽ ደስ ይበለን(2)አልል በሉ(2)አዳነን በማይሻር ቃሉ(2)
ጥቅስ፡ ዮሐ 3÷16

መዝሙር
ክርስቶስ ተንስአ
ክርስቶስ ተንስአ በአማን
ክርስቶስ ተንስአ እሙታን(2)
አማን በአማን መድኃኔዓለም(2)
ዲያብሎስ ተመታ በመስቀል(2)
የአዳም ልጆች ሁሉ እንበል አልል(2)
ጥቅስ፡ ኤፌ2÷14-16

መዝሙር
ወምድርኒ
ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ(2)
ተሀሚበ በደመ ክርስቶስ(2)
ትርጉም፡ በክርስቶስ ደም ታጥባ ምድር ደስታ
አደረገች::
ጥቅስ፡ 1ዮሐ1÷7

መዝሙር
እስመ ለዓለም ምሕረቱ
እስመለዓለም ምሕረቱ(2)
አያልቅም ብዙ ነው የአምላክ ቸርነቱ
አመስግኑት ጌታ ሁላችሁ በአንድነት(2)
መሃሪ ነውና ለሰው ልጆች ሕይወት(2)
እስመለዓለም.....
የማይሞተው ሞቶ የተቀበረው(2)
ከገሃነም እሳት አኛን ሊያድን ነው(2)
እስመለዓለም.....
ከማርያም የነሳው ያ ቅዱስ ሥጋው(2)
ቀራንዮ ሲውል የሚያሳዝን ነው(2)
እስመለዓለም.....
በፈጠረው ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ(2)
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል ጐትቶ(2)
እስመለዓለም.....
ጥቅስ፡ 1ጴ3÷18-19

መዝሙር
ፈኑ ዲቤነ
ፈኑ ዲቤነ ብርሃንከ(2)
ትንሣኤከ(2)ለአለሰመነ (2)
ትርጉም፡ ትንሳኤህን ላምነነ ለኛ ብርሃንህን ላክልን::
ጥቅስ፡ ማቴ 28÷1-5

መዝሙር
በደሙ ክቡር
በደሙ ክቡር(2)ቤዘወነ(2)
አኮ በወርቅ ኃላፊ ዘተሳየጠነ(2)
ትርጉም፡ በኃላፊው ወርቅ ሳይሆን በከበረው ደሙ አዳነን::
ጥቅስ፡ 1ኛቆሮ6÷19-20

መዝሙር
ምንሰጡህ ይሁዳ
ሙትን ልታስነሣ ድውይን ልትፈውስ
ሥልጣን ሰጥቶህ ነበር ኢየሱስ ክርስቶስ
ልታስር ልትፈታ በነፍስም በሥጋ(2)
ሥልጣን ሰጥቶህ ነበር <u>ሰልፋና ሶሜጋ</u>(2)
ምን ሰጡህ ይሁዳ አይሁድ ዘመዶችህ
ስአነርሱ አሳልፈህ ጌታህን የሰጠህ
ከሁሉ የሚበልጥ ሥልጣን ሰጥቶህ ሳለ(2)
ብርን ለመቀበል ልብህ ተታለለ(2)
ሠማይና ምድርን በቃሉ የፈጠረ
አንዴት በመቃብር ሦስት ቀን አደረ
አንተ የሠጠኸው አሳልፈህ በሞት(2)
ሞትን ድል አድርጐ <u>ተነሣ በሰንበት</u>(2)
ጥቀስ፡ ሐዋ2÷24

መዝሙር
ንግበር በዓለ
ንግበር በዓለ በቃለ አሜን ንግበር በዓለ(2)
ንግበር በዓለ የስራውን ሥጋ ንግበር በዓለ
" " በፈቃዱ ስብሶ " "
" " የወደቀውን ሠው " "
" " ከቦታው መልሶ " "
" " ጠላት ዲያቢሎስን " "
" " በመስቀል ድል ነስቶ " "
" " ሠላምን ሠበከ " "
" " ከሙታን ተነስቶ " "
ንግበር በዓለ በቃለ አሜን ንግበር በዓለ(2)
ንግበር በዓለ ሐዋን ያዘጋችው ንግበር በዓለ
" " የገነት ደጃፍ " "
" " ሲጠበቅ የኖረው " "
" " በሱራፌል ሠይፍ " "
" " አስይ የምሥራች " "
" " አልል አንበል " "
" " ዳግም ተከፈተ " "
" " በማርያም ድንግል " "
ንግበር በዓለ በቃለ አሜን ንግበር በዓለ(2)
ንግብር በዓለ ሞቶ የነበረው ንግበር በዓለ
" " የዋሁ አዳም " "
" " አጸበለስ በልቶ " "
" " አንዲኖር ታድሶ " "
" " አስከ ዘለዓለም " "
" " ሕይወት ተሰጣቸው " "
" " በሥጋ ወደም " "
ንግበር በዓለ በቃለአሜን ንግበር በዓለ(2)
ንግበር በዓለ የጥበብ ሀገሯ ንግበር በዓለ
" " መንፈስ ቅዱስ ሠደ " "
" " ዕውቀትን አሳድር " "
" " በሕዝቦችህ ላይ " "
" " ሃሌ ሃሌ ሉያ " "
" " ሃሌ ሃሌ ሉያ " "
" " ሠላምን አድሳት " "
" " ስኢትዮጵያ " "
ንግበር በዓለ በቃለ አሜን ንግበር በዓለ (2)
ጥቀስ፤- ኦሪት ዘፍጥረተ ምዕ 3÷22-24
ማቶ ምዕ 27÷15-25 ሐዋ 2÷4

መዝሙር
ሠበካ ትንሣኤ
ሠበካ ትንሣኤ(2)
አዋልዲሃ ስፅዮን(2)
ትርጉም፤-የፅዮን ቆንጆዅት ትንሣኤውን ሠበኩ
ጥቅስ፤- ዮሐ 20÷13

መዝሙር
ብርሃን ወጣ
ብርሃን ወጣ ከመስቀሉ የሚያንፀባርቅ
የአምላክና የሠው ልጆች አውነኛ ዕርቅ
ደስ ይበለን በትንሣኤው ብርሃን
አልል አንበል በአንድነት ሆነን
ተነሳልን መድኃኒታችን
ከፊት ለፊት በምሣሉ የመስቀሉ ነገር
ለሚወደው ሐዋርያ የወንጌል መምህር
ዮሐንስም ስቅለቱን በማየቱ
አለቀሰ አስከ ዕለተ ሞቱ
ሲያሰቅቀው ሞቱ ግርፋቱ
ብርሃን ወጣ.....
ሞኝነት ነው ለሚጠ|ት መሰናከያቸው
በዓለም ጥበብ ለሚኖሩት አውነት ተስኗቸው
ለጠቢብ ሠው በመንፈስ ለሚኖረው
የመዳን ቀን አውነተኛ ዓርማ ነው
ከገሃነም እሣት የሚያድን ነው
ብርሃን ወጣ.....
አስከ መሞት ላልተለየው ቅዱስ ሐዋርያ
ለዮሐንሰ የወንጌል ሠው የፍቅር ባለሙያ
ምሥጋናችን ከምድር ይደረሠው
አንድናለን በሠጠን ምሣሌው
ሰዎች ሁሉ አንከተለው
ብርሃን ወጣ.....
ጥቅስ፤- ኤፌ 2÷16

መዝሙር
ሞቶ የነበረው
ሞቶ የነበረው(2) ተቀብሮ(2) አንደሬሣ(2)
ሙስና መቃብርን <u>ድል አርጉ</u>(2) ተነሣ(2)
የሙታን ትንሣኤ(2) አንዳለ በገሃድ ሲነግረን

ሞትን ድል አድረጐገ ተነሣ(2) መድኃን
ጭፍሮች ጠባቂዎች(2) በጣሙን ፈርተው ደነገጡ
ድንጋዩ ሲከፈት(2) መግቢያቸውን አጡ
ሞቶ የነበረው.....
በሰንበት ቀን ማልደው(2) ወደ አዚያ አየገሰገሱ
ብዙ ሴቶች ሆነው(2) በሐዘን አስበው ሲያለቅሱ
አየተሯሯጡ መቃብሩ በሌሊት ደረሱ ኧኸ
ሞቶ የነበረው.....
አሁድ በማለዳ(2) ድንጋዩ መቃብሩ ተከፍቶ
አገኙት በደስታ ጌታችን(2) ተነስቶ(2)
ሴቶች ትንሣኤውን(2) ሲያወሩ ሲያበሥሩ በአልልታ
ጨሀ ስትመሰክር(2) በገሀድ ምድር አፏን ከፍታ
ያልታደሠ የለም ፍጡር(2) የዚያን ለታ(3)
ሞቶ የነበረው.....
ጥቅስ፤-ማር 16÷4-6

መዝሙር
በክብር ተነሣ
በክብር ተነሣ ከሙታን(2)
ሕያው የሆነው አምላካችን ንጉሣችን(2)
ጥቅስ፤- ሉቃ 24÷6

መዝሙር
ተሰቅለ
ተሠቅለ ከመያፅድቀነ(2)
ተንሰአ ከመ ያንስእነ(4)
ትርጉም፤-እውነተኞች ያደርገን ዘንድ ተሠቀለ
ከስንፍና አንቅልፍ ያነሣን ዘንድ
ተነሣ::
ጥቅስ፤- ኤፌ 5÷14 ኤፌ 2÷5

መዝሙር
አማን በአማን ተንስአ
አማን በአማን(4)
ተንስአ እምነ ሙታን(2)
ትርጉም፤-እውነት በእውነት ክርስቶስ ከሙታን
ትለይቶ ተነሣ ::
ጥቅስ ሉቃ 24÷34

መዝሙር
ድል አድራጊው ጌታ
ድል አድራጊው ጌታ ሸረት የሌለበት (2)
በመስቀሉ ሻረው የሲዖልን መንግስት
ዓለም ተቀደሰ ሰይጣን ድል ተመታ (2)
በመስቀል ላይ ሣለ የሠራዊተ ጌታ
ገሃነም ተዘጋ ሲዖልም ፈረሰ
ወደቀድሞ ቦታው አዳም ተመለሠ (2)
ከሥልጣኑ ወርዶ ዲያብሎስ ታሠረ (2)
በኢየሱስ መስቀል የሠው ልጅ ከበረ (2)
እውራንም አዩ ሙታንም በነሡ (2)
የሲዖል ደጃፎች በመስቀል ፈረሱ (2)
ኃያሉ ጌታችን ምሥጋና ይድረስህ
ከኃጢአት ያዳንከን ደምህን አፍስሰህ (2)
ጥቅስ፤-1ኛ ቆሮ 15÷54-55

መዝሙር
ከመቃበር ተነስቷል
ከመቃብር ተነስቷል
ጠላቶቹን አረግጦ በጭራሽ ደምስሷል
አሸንፎ ተነሳ የጨለማውን ግዞት ዘለዓለም
ስዘለዓለም የሚኖ በሠማይ ገነት
ተነስቷል (2) ሃሌ ሉያ ክርስቶስ ተነስቷል
ጥቅስ፡ ማቴ 28÷5-7

መዝሙር
በደምህ ተገዛን
በደምህ ተገዛ የጠፋው ዓለም
ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ አምላክ
በደምህ አጠበው ኃጢአታችንን
ሃሌ ሃሌ ሉያ የዓለም መድኃን
ሞተህ ብትነሳ ደምህን አፍስሰህ
ሃሌ ሃሌ ሉያ የዓለም ነፍስ ነው የአንተ ሥጋህ
ወንዞች ተነሱ አንተን ለማመስገን
ሃሌ ሃሌ ሉያ አምላክ ብርሃን
ጥቅስ፡ ራዕ 7÷14

መዝሙር
አስመ በዝንቱ
አስመ በዝንቱ በዓል ተፈስሁ ኩሉ ፍጥረት(2)
አስመ እግዚአብሔር ትንሣኤሁ ገብረ በሰንበት
አስመ እግዚአብሔር ትንሳኤሁ በሰንበት ገብረ(2)
ትርጉም፡ እግዚአብሔር ትንሣኤውን በሰንበት ስላደረገ
በዚህ በዓል ፍጥረት ሁሉ ደስ ተሰኙ::
ጥቅስ፡

መዝሙር
አንትሙስ ንበሩ
አንትሙስ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም (2)
እስከትስብሱ ኃይለ እምእርያም (2)
እናንተ ግን ቆዩ በኢየሩሳሌም ሀገር(2)
እስከምታገኙ ኃይል ከሠማይ(2)

ጥቅስ፤- ሉቃ 24÷49

መዘሙር
በምሥጋና አረገ
እንዘምር ሁሳችን ለቸሩ ፈጣሪ
በትንሣኤ ኃይሉ ሞትን አሣፋሪ
እስደ አገኘነው ሕይወታችንን(2)
ደስ ይበለን
ትጉህ የማይተኛ ጊዜውን አክብሮ (2)
ነፈሣትን አወጣ ከሲዖል በርብሮ (2)
እስደ አገኘነው.....
ዐረገ በስብሐት ዐረገ በእልልታ (2)
ሞትን ድል አድረጐ የሥራዊት ጌታ(2)
እስደ አገኘነው.....
ሞት ሆይ ወዴት አለ ከቶ ማሸነፍህ (2)
ኃይለህ ተዋረደ አንተም ድል ተነሣህ (2)
እስደ አገኘነው.....

ጥቅስ፤-ሉቃ 24÷50-51 1ኛ ጴጥ 3÷19

መዝሙር
እየባረካቸው
እየባረቸው ወደሳይ አቀና
ዓይናቸው እያየው ሰወረው ደመና
መንፈስ ቅዱስ መጣ ከዐረገ በኋላ
ተሰብስበው ሳሉ ሁሉም በገሊላ
እንረሱም አገኙ የመንፈስ ሥጦታ
እስከ መጨረሻው ኃይል የሚያበረታ
ዓለም ተቀበለ የአነርሱን ትምህርት
ከክፋትም ዳኑ አገኙ ሕይወት
ሐዋርያት ዞሩ እስከ ዓለም ዳርቻ
ቢሰሙ ሲሰብኩ ያለ እንዳች ፍራቻ
እናንተም አሳችሁ ትጠሉ ዘንድ ደግሞ
እኔን እንደጠላ ዓለም አስቀድሞ
ጥቅስ፤- ሐዋ 1÷6 ሉቃ 24÷50

መዝሙር
ዐረገ በስብሐት
ዐርገ በስብሐት ዐረገ በእልልታ
በስብሐት በእልልታ ዐረገ (2) በዕልልታ (2)
ሞትን ድል አድረጐ የሥራዊት ጌታ ዐረገ(2)
በዕልልታ(2)

ጥቅስ፤-መዝ 46÷5

መዝሙር
ወረደ መንፈስ ቅዱስ
ወረደ መንፈስ ቅዱስ ሳዕለ ሐዋርያት(2)
ከመ ዘእሣት(2) ተናገሩ(2) በነገረ ኩሉ በሐውርት (2)
ትርጉም፤-

ጥቅስ፤- ሐዋ 2÷1-2

መዝሙር
መንፈስ ቅዱስ ወረደ
መንፈስ ቅዱስ ወረደ ሳዕለ ሐዋርያት(2)
ተመሲሎ(5) በነበደ እሣት(2)
ትርጉም፤- መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ በእሣት
አምሣል ተመስሎ ወረደ::
ጥቅስ፤- ሐዋ 2÷1-2

መዝሙር
አሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት
አሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ምንኛ ዕድለኞት ናቸው
ፀጋ መንፈስ ቅዱስ በፅዮን አዳራሽ የወረደላቸው
ዞረው እንዲያስተምሩ በዮምድባቸው
ሰባ ሁለት ቋንቋ(2) ተገለፀላቸው
ጴጥሮስ ሲጠባበቅ ያንን የተስፋ ቃል(2)
ወርደ አጥለቀለቀው የመንፈስ ማዕበል(2)
አሥራ ሁለቱ.....
ደቀመዛሙርቱ በመንፈስ ሲሞሉ(2)
ጉሽ ጠላ ነው ብለው አይሁድ አሳበኡ(2)
አሥራ ሁለቱ.....
በመንፈስ መሪነት ፅድቅን የሚመኙ(2)
ሦስት ሺህ አማኞች(2) በአንድ ቀን ተገኙ(2)
አሥራ ሁለቱ.....
እንደባረካቸው ሐዋርያትን(2)
አቤቱ ጌታ ሆይ (2)እኛንም ባርከን (2)
አሥራ ሁለቱ.....
የፍቅር መደብር ነህና ገበያ(2)
ሠላምን አድላት(2) ለኢትዮጵያ(2)
አሥራ ሁለቱ.....
ጥቅስ ሐዋ 2÷1-4

መዝሙር
ጲራቅሊጦስሃ
ጲራቅሊጦስሃ መንፈስ ጽድቅ(4)
ወደ ሂሱ ዘልፈ ምስሌክሙ (2)
ትርጉም፤-

ጥቅስ: ዮሐ 16÷13

መዝሙር
በመንፈስ ደሀሙረ
በመንፈስ ደሀሙር ወበኃይል ኤልያስሠ(2)
አልቦ ዘኢያስዮ ለዮሐንስ(2)
ትርጉም፡-

ጥቅስ: ማቴ 17÷11-13

መዝሙር
ፀጋ ነሣይነ
ፀጋ ነሣይነ ወሕይወተ ረከብነ(2)
በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ
በኃይለ መስቀሉ(2)
ኪያከ አግዚኦ ነአኩት ወንሴብሐከ
አግዚአብሔር(2)
ትርጉም፡- ፀጋን ተቀበልን ህይወትንም አግኝተን
በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
መስቀል የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ
ተቀብለን አንተን አናመሰግንሃለን::
ጥቅስ፡- ሮሜ 12÷4-3

መዝሙር
በከመ መሀሮሙ
በከመ መሐሮሙ(2)
በከመ መሐሮሙ መንፈስ ቅዱስ (2)
አንደ አስተማራቸው (2)
አንደ አስተማራቸው መንፈስ ቅዱስ(2)
በዓለም ሁሉ ቋንቋን ተናገሩ(2)
አንደ አስተማራቸው መንፈስ ቅዱስ (2)
ጥቅስ፡- ዮሐ 14÷26

መዝሙር
ንስግድ ለአበ ብርሃናት
ንሰግድ ለአበ ብርሃናት ወለወልዱ ዋህድ(2)
ወለመንፈስ ቅዱስ ጺራቅሊጦስ ሥሉስ ሕሩይ(2)
ትርጉም፡- ለብርሃናት አባት (ፈጣሪ) ተቀዳሚ
ተከታይ ለሌለው አንድ ልጁም አጽናኝ
ለተባለ ለመንፈስ ቅዱስ ሦስትና
ትክክል ለሚሆኑ አንስገድ::
ጥቅስ፡-

መዝሙር
የታቦር ተራራ
የታቦር ተራራ በጣም ደስ ይበልሽ(2)
እግዚአብሔር መስኮቱን ስለገለፀብሽ(2)
ጥቅስ፡ ማቴ 17÷1-8

መዝሙር
ሰላም ሰላም የታቦር ተራራ
ሠላም ሠላም (2) የታቦር ተራራ
ብርሃነ መለኮት ባንቺ ላይ አበራ(2)
ሙሴና ኤልያስ እንዲያ ሲሸበሩ
ምነው አንቺ አልፈራሽ ምንድነው ምሰጢሩ
ሠላም ሠላም.....
ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር የዋሉ
የአምላክን ድምጽ ሰምተው ለመጽናት አልቻሉ
ሠላም ሠላም.....
ጥቅስ፡ ማቴ 17÷1-8

መዝሙር
ታቦር ወአርሞንኤም
ታቦር(2) ወአርሞንኤም
የጌታችን ክብሩ የተገለፀብሽ
ብርሃነ መለኮት ባንቺ ያደረብሽ
ታቦር.....
ምስጢረ ሥላሴ የተገለፀብሽ
የወልድ አምላክነት የተነገረብሽ
ታቦር.....
የታቦር ተራራ ምንኛ ድንቅ ነሽ
ከተራሮች ሁሉ አንቺ የተመረጥሽ
ታቦር.....
ብርሃነ መለኮት ባንቺ ላይ ሲያበራ
ምነው አንቺ አልፈራሽ የታቦር ተራራ
ታቦር.....
የታቦር ተራራ ተደሰች በስሙ
ተፈስሒ አንዳለው ዳዊት በመዝሙሩ
ታቦር.....
ጥቅስ፡ መዝ 88÷12-13 ማቴ 17÷1-8

መዝሙር
ወተወለጠ
ወተወለጠ ራዕዩ በቅድሜሆሙ(2)
ወአልባሲሁኒ(5) ኮነ ፀአዳ ከመበረድ(2)
ትርጉም፡ በፊታቸው መልኩ አበራ ልብሱም እንደ በረድ ነጭ ሆነ አማረ።

ጥቅስ፡ ማር 9÷2-8 ማቴ 17÷1-8

መዝሙር
በደብር በደብረ ታቦር
በደብር በደብረ ታቦር(2)
ሰባሕኩከ በደብር(2)
ትርጉም፡ በታቦር ተራራ አመሰገንኩህ

ጥቅስ፡ መዝ88÷12

መዝሙር
መስመ ዚአከ
በስመ ዚአከ ይትፌስሁዩም(2)
ታቦር ወአርሞንኤም(2)
ትርጉም፡ ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ደስ ይላቸዋል።
ጥቅሰ፡ መዝ 88÷12-18

መዝሙር
እንዲህ አለው ጴጥሮስ
እንዲህ አለው ጴጥሮስ ኢየሱስ ምስጢር ገሀድ ሲሆን
በዚያ በተራራ
በአንድ ላይ አንኑር ሦስት ዳስ እንስራ
እንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ
ተለወጠ ገጽ ከመጽጌዳ
ወርዶ ከለላቸው ደመና ፀአዳ
እንዲህ አለው.....
ከሠማይ ቃል መጣ እንደዚህ የሚል
የምወደው ልጄ እርሱን ስሙት ሲል
እንዲህ አለው.....
ኤልያስም ሄደ በሰረገላው
ሙሴም ከመቃብር ወደ መኖሪያው
እንዲህ አለው.....
ስላስደነቃቸው ግሩም ተአምራቱ
ይህን ምስጢር አይተው ተሰነባበቱ
እንዲህ አለው.....
ጥቅስ ማቴ17÷1-8 ማር9÷2-8 ሉቃ9÷28-36

መዝሙር
አሃደ ለከ
አሃደ ለከ ወአሃደ ለሙሴ(2)
ወአሃደ ለኤልያስ ንግበር ማህደር(2)
ትርጉም፡ አንድ ለአንተ አንድ ለሙሴ አንድ ለኤልያስ ማደሪያ እንስራ።
ጥቅስ፡ ማቴ17÷1-8

መዝሙር
የተገለፀብሽ
የተገለፀብሽ ብርሃነ መለኮት
የክብሩ ብርሃን የአምላክነት
ሠላም ላንቺ ይሁን ደብረታቦር ክብርት(2)
ጌታችን ክርስቶስ አምላክነቱን
ሊያሳይ ሰበሰበ ሐዋርያቱን
ወደ አንቺ ተጓዙ ሊገለጽ መለኮቱን(2)
የተገለፀብሽ.....
ጴጥሮስ ያዕቆብን ወንድሙ ዮሐንስን
ኤልያስንና አንዲሁም ሙሴን
ወደ አንቺ አወጣቸው ሊያሳይ ክብሩን
የተገለፀብሽ.....
ተናግሮ ነበረ ዳዊት በትንቢቱ
ታቦር አርሞንኤም በስምህ ተደሰቱ
ይህውም አልቀረ በአውን ተደሰቱ
የተገለፀብሽ.....
የመለኮት ብርሃን በላይሽ ሲያራ
ሠለስቱ ሐዋርያት ሲወድቁ በተራ
ምነው አንቺ አልፈራሽ የታቦር ተራራ
የተገለፀብሽ.....

አብ መሠከረብሽ በደመና ሳስ
የምደው ልጂ ደሄነው እያስ
ከአድባራቱ ሁሉ ያንች ክብር አየስ
የተገስፀብሽ.....
ጥቅስ: ማቴ 17 ÷ 1-8

መዝሙር
ቡሔ በሉ
መጣና በዓመቱ አረ አንምን ሰነበቱ (2)
ክፈት በለው ተነሣ ያንን አንበሣ (2
ክፈት በለው በሩን የጌታዮን (2)
አዚህ ቤቶች ሆ
አንደምናችሁ "
በዓመት አንድ ቀን "
መጣንላችሁ "
የደብረ ታቦር "
ክብረ በዓሉ "
ደዋል ደከበር "
በዓለም ሁሉ "
የጌታዬ ክብር "
የተስፀብሽ "
ምስጢሩን ለሰው "
በእውነት ያሳየብሽ "
በደብረ ታቦር "
በዚያ ተራራ "
የዓለም ጌታ "
ተአምራትን ሰራ "
ሆያሆዬ በሉ ልጆች በሙሉ
ሆያዬ በሉ ክርስቲያኖች በሙሉ
ሆያሆዬ በሉ ደቂቀ አዳም በሙሉ
ያቆብና ጴጥሮስ ሆ
ደግሞም ዮሐንስ "
ከነቢያት ወገን "
ሙሴና ኤልያስ "
ተገኝተው ነበር "
በደብረ ታቦር "
ከሰማይ "
በደመና "
የምወደው ልጄ "
ይህ ነውና "
እርሱን ስሙት "
በጥሞና "
የሚል ቃል መጣ "
በሥርዓቱ "
የነገሙ
ሐዋርያቱ "
ጌታም ቀርቦ "
አነሳቸው "
እንዳፈሩ "
አጽናናቸው "
አይናቸውንም "
አቅንተው ሲያዩ "
ከኢየሱስ በቀር "
ማንንም አላዩ "
ሆያሆዬ በሉ
ቡሄ ማለት ሆ
ትርጓሜው "
መላጣ ገላጣ "
ማለት ነው "
በደብረ ታቦር "
በዚያ ተራራ "
የዓለም ጌታ "
ተአምራትን ሰራ "
ይህንን ተአምር "
ተመልክቶ "
እንዲህ ብሎ አለ "
ጌታን ተገናኝቶ "
በዚህ ተራራ "
ዳስ እንስራ "
እንዱን ላንተ "
አንዱን ለሙሴ "
አንዱን ለኤልያስ "
ቶሎ እንስራ "
ሳናቅማማ "
ብሎ ተናገረ "
ጴጥሮስ ሐዋርያ "
ሆያሆዬ በሉ
እዛ ማደ ሰገነት ሆ
አዚህ ማደ ሰገነት "
ለዘለዓለም ኑሪ "
ተዋህዶ አምነት "
ጴጥሮስ በአደባባይ "
የተሰየፈልሽ "
እስጢፋኖስም "
የተወገረልሽ "
አንዲቷ አምነታችን "
የተቀደስሽ ነሽ "
የመሰከረልሽ "
ዳዊት በትንቢቱ "
ምስጋና ይድረስሽ "
ድንግል ወላዲቱ "
አምላክን የወለድሽ "
በንጽህና "
የተመገብሽው "
ሰማያዊ መና "
ወላዲተ አምላክ "
ድረሽልን "
ችግራችንን "
አመልክችልን "
ኢትዮጵያ አገራችን "
ሠላም አድርጊልን "

ሆያሆዬ በሉ

ዓመት አውደ ዓመት ድገምና ዓመት ድገምና (2)
የተዋህዶን ቤት ድገምና ዓመት (2)
ጠርቅ ስፍስበት

መዝሙር
በሐይማኖት
በጭራሽ አንዲደርቅ የኃጢአት ሥሩ
መበርታት አለበት ሁሉም በምግባሩ
በሃይማኖት/2/ አስብን መፅናት(2)
እንፅና በመንፈስ አንሁን ልበ መንታ
እንዲከተትልን ደጁን ስንመታ
በሃይማኖት.....
ሕይወትን የሚሰጥ ወደ አብ የሚመስድ
ከኢየሱስ በቀር የለም ሌላ መንገድ
በሃይማኖት.....
ምግባራችን አምሮ በእምነት ከፀናን
ሲያበራ ይኖራል የስራችን ብርሃን
በሃይማኖት.....
ይብዛ ሠላማችን መልካም ስራ አንስራ
የመንፈስን ፍሬ ሁላችን እናፍራ
በሃይማኖት.....
ጥቅስ : ማቴ 5:16 ዮሐ14:6-12
ዮሐ 16:33 ማቴ 24:43-45
የሐ7:15-19

መዝሙር
ተዋህዶ
ተዋህዶ /2/ ሰማያዊት
የቀናች እምነት/2/ሃሌ ሉያ
ተዋህዶ/2/ መንፈሳዊት
የመንፈስ መብራት/2/ ሃሌ ሉያ
ተዋህዶ /2/ መለኮታዊት
ንጽህት እምነት/2/ ሃሌ ሉያ
ባንቺ ቢያምኑ/2/ ቅዱሳን
ድል ነሱ ሰይጣን/2/ ሃሌ ሉያ
ባንቺ ቢያምኑ /2/ ሰማዕታት
ተፈተኑ በእሳት/2/ሃሌ ሉያ
እንደ ወርቅ/2/ ፀርተው
አበራ ገድሳቸው/2/ሃሌ ሉያ
ክርስቲያኖች/2/ አስተውሉ
መዝኑ አስተውሉ/2/ ሃሌ ሉያ
ተዋህዶ /2/ መሰረት
የጽድቃችን ሐውልት/2/ ሃሌ ሉያ
ትኑርልን/2/ እምነታችን
ተዋህዶ መክበሪያችን/2/ ሃሌ ሉያ
ጥቅስ: ዮሐ 1:14 ማቴ7:6 ዕብ11:35

መዝሙር
ተዋሕዶ ንጽሕት
ተዋሕዶ ንጽሕት ቅድስት እምነታችን/2/
ኑሪ ለዘለዓለም ተከብረሽ በአምላካችን/2/
ጥቅስ: ዮሐ 4:14-18

መዝሙር
ሠላም ተዋሕዶ
ሠላም ተዋሕዶ ሰላም ኦርቶዶክስ
የአትናቴዎስ ሐውልት የዲዎስቆሮስ
የአዳም መመኪያ የሐዋን ሀገር
አንቺ አይደለሽም ወይ የቅዱሳን ክብር
ሠላም.....
በከንቱ የሞተው የአቤል መስዋዕት
የሔኖክ ሃይማኖት ያዳንሽው ከሞት
አንቺ የኖህ መርከብ የሴም በረከት
ሠላም.....
በአብርሃም ድንኳን ተወልደሽ ያደግሽ
የይስሐቅ መዓዛ ወደር የሌለሽ
የያቆብ በህልሙ በቤቴል ያየሽ
የዌሴፍ አጽናኙ ተዋህዶ ነሽ
ሠላም.....
የሙሴ ጽላት ነሽ የአሮን በትር
የኢያሱ ሀውልት የጌድዮን ፀምር
የሳሙኤል ሙዳይ ከዕሴይ ትውልድ
የዳዊት በገና የሰሎሞን ዘውድ
የታተመች ገነት የምስጢር ጉድጓድ
ሠላም.....
ቡአዴና ህድረት የኬልቄዶን ዘር
ቱሳሔና ሚጠት ውሳጤም ጭምር
ያልተቀሳቀስች ንጽሕይቲቱ ምድር
ኢሳይያስ አይቶ በሩቅ መነጽር
ስለቅድስናሽ ሆነ ምስክር
ሠላም.....
የንስጥሮስ ወንድም ሲሆን ያልደፈረሽ
የዳንኤል ድንግል ተዋህዶ አንቺ ነሽ
በነኢልያስ ቤት የወርቅ መሶብ
በውስጥሽ የሞላው የምስጢር ምግብ
የኤልሳዕ ማሰሮ የሕይወት መዝገብ
ፋራን የምትባል የአንባቆም ተራራ
ሁሉን የምታሳይ ከቀኝም ከግራ
ሠላም.....
የሕዝቅኤል እልፍኝ ባለ አንድ በራፍ
የማትከፈተው በኬልቄዶን ቁልፍ
የሕግ መፍለቂያ የነፃነት ቦታ
የሚልክያስ ሀገር አንቺ ነሽ ኤፍራታ
ዕፀ ሕይወታችን የኤፌሶን ቅርስ
የተፈወሱቡሽ አነ አቡን ቄርሎስ
ስተፈወስንብሽ ከኬልቄዶን ቁስል
ተዋህዶ ላንቺ እልል እንበል
ሠላም.....
አንቺን በማየቱ በብርሃን ተቂም
ደስ አለው ከልቡ ዘካርያስም
በውስጥም በውጭም የሌለብሽ አንከን
የሕይወት መዝገብ ነሽ ተዋህዶአችን
ሠላም.....
ሐዋርያት ይምጡ ያውሩ ያንችን ዝና
የሚያውቅ ሲናገር ደስ ያሰኛልና
ሰማዕታት ልጆችሽ የፃፉሽ በደም
የሕይወት መጽሐፍ ነሽ የጽድቅ የሠላም
ሠላም.....
አንቺን ለመጠበቅ እስከ ዓለም ፍፃሜ
ቃል አንገባለን ባለነበት አድሜ
አናምናለንና በፈጣሪያችን
ካንቺ አንደማይለየን ምን ጊዜም ቢሆን
ሠላም.....

መዝሙር
ሐይማኖት አንዲት ናት
ሐይማኖት አንዲት ናት እውነተኛይቱ(2)
በወንጌል ያስችው ቀጥተኛይቱ(2)
አንድ አካል አንዱ በሕርይ ብለን እናመናለን(2)
በስራና በቃል እንመስክራለን(2)
ከጥርጥር ነፋስ ከጕርፍ ተጠብቀን(2)
እስከ መጨረሻው በእምነት እንፀናለን(2)
ጥቅስ: ኤር 4÷4-6

መዝሙር
ፅንሱ በተዋህዶ
ፅንሁ በተዋህዶ አምነት(2)
መሠረት(2) ናትና ሕይወት(2)
ትርጉም፦ የሕይወት መሠረት ናትና
በተዋህዶ ሃይማኖት ፅኑ::
ጥቅስ፣ 1ኛ ቆሮ 16÷13-14

መዝሙር
እምነት ተስፋ ፍቅር
እምነት ተስፋ ፍቅር(2)
እኒህ ሦስቱ ፀንተው ይኖራሉ ፍቅር ግን ይበልጣል
ከሁሉ(2)
ጥቅስ፦1ኛ ቆሮ 13÷14

መዝሙር
ሰላም ለኪ እናታችን
ሰላም ለኪ እናታችን(2) ቤተክርስቲያን(2)
በደሙ የዋጀሽ(2) ኢየሱስ መድኃን(2)
ጥቅስ:

መዝሙር
ወደ ሃይማኖታችን
ወደ ሃይማኖታችን የሁሉችን ሕይወት(2)
አንቺ ከምትጠፊ እኛ አንጥፋ በፊት(2)
እነ ሁሉ ሳፊ እነ አቶ ለከርሱ
አምላክ የለም ብለው በአንተ ላይ ተነሱ
ሠማይና ምድርን የፈጠረ እያለ
የኤርትራን ባሕር የከፈለ እያለ
ክረምትና በጋን የፈጠረ እያለ
የሰው ልጅ ደፋሩ አምላክ የለም አለ(2)
በዝናብ አብቅሎ የሚመግብህን
በፀሐይ አብስሎ የሚመግብህን
አምላክ የለም ብለህ ካድከው ፈጣሪህን
አእምሮ አለኝ ማለት አእምሮ ማጣት
አንክርዳድ ለመዝራት በሰው ጭንቅላት
ይፍጨረጨራሉ ቀንና ሌሊት(2)
እነ ሁሉ ሳፊ እነመንፈቅ ልጅ
ይኸ ዓለም ጠፊ ነው ባያውቁት ነው አንጂ
ተው ንስሀ ግባ የሰው ልጅ ተመለስ(2)
እንደ ልጅነትህ ኋላ ከምታሰቅስ(2)
ጥቅስ: ኢሳ 44÷24-28 ዘፀ 14÷15-31
2ኛጴጥ 2÷ በሙሉ

መዝሙር
የክርስቲያን ደሴት
የክርስቲያን ደሴት የሰበው ሃይማኖት
ሐዋርያዊት አገር ጥንታዊት እናት
የቅዱሳን መንደር የፀሎት ቤታችን
ኢትዮጵያ አንቺ ነሽ ቅድስት አገራችን
ትነሻለሽ ስፍርድ ወንጌሉን ይዘሽ
ለሰሎሞን አምላክ ምስክር የሆንሽ
ሰልፕነሻልና በሃይማኖት ምስጢር
ኢትዮጵያ መስክሪ የስላሴን ክብር
ከእስራኤል ቀጠለሽ አምልኮ ያለሽ
የሃይማኖት አገር ኢትዮጵያ አንቺ ነሽ
በወንጌል ብርሃን ዳግም የተወለድሽ
በሥጋ በደሙ ሕይወት የገበየሽ
ጥበብን ለማየት እስራኤል የሄድሽ
በወንጌል ተጽፏል ቀናው እምነትሽ
አይዞሽ ኢትዮጵያ ዘርጊ እጆችሽን
ጌታ ይቀበለዋል ንፁህ አምልኮሽን
ጥቅስ:

መዝሙር
የሰው ልጆች ፀጋ
የሰው ልጆች ፀጋ(3) የሰው ልጆች ሕይወት
ትኑር ለዘለዓለም(2) የሰበው ሃይማኖት
የሰበው ሃይማኖት(3) የሰው ልጆች ፀጋ
በሰማይ በመሬት(2) ለሳት ታላቅ ዋጋ
የሰበው ሃይማኖት(3) እድለኛይቱ
የልብ አሰሪ ነሽ(2) ለያዘሽ በእውነቱ
በማያልፈው ዓለም(3) በላይኛው ስፍራ
ቦታን ታሰጣለች(2) ሆና ከእኛ ሀገራ
አጥብቆ የያዛት(3) አይሂድ ወደ ሌላ
ክብርን ታሰጣለች(2) የኋላ የኋላ
ጥቅስ: ኤር6÷6 ኤፌ4÷4-7

መዝሙር
አንድንተባበር
አንድንተባበር በሃይማኖታችን
ፍቀርና ሠላምን ለኛ ያጎናፂፈን(2)
ዛሬም ዘወትርም አንተን እያስታወስን
እዝነ ልባችንን በመንፈስህ አድስ (2)
በሃይማኖታችን ተግተን አንድንሰራ
ቅዱስ መንፈስህ ይኑር ከእኛ ጋራ(2)
ከወንጌል ዓላማ አንዳያናውጸን
ግርማ መለኮትህ ይኑር ሲጠብቀን(2)
ጥቅስ፣- 1ኛ ቆሮ 13÷1-13

መዝሙር
እንዘ ይበሉ
እንዘ ይበሉ ይዜምሩ በልሳነ ዘኢያረምም(2)
መንግሥተ ሥላሴ ዘለዓለም(2)
ትርጉም: ዝም በማይል በእንደበታቸው እንዲህ እያሉ ይዘምራሉ::የሥላሴ መንግሥት ዘለዓለማዊ ነው ::
ጥቅስ: ኢሳ6 ÷ 3

መዝሙር
አማን በአማን
አማን በአማን አማን በአማን(2)
መንግሥተ ስላሴ ዘለዓለም(2)
ትርጉም : እውነት በእውነት የሥላሴ መንግስት ዘለዓለም ነው::
ጥቅስ: ማቴ 19 ÷ 28

መዝሙር
ስብሐት ለአብ
ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ
ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ
ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም
ምስጋና ከማቅረብ ከቶ አንወሰንም(2)
ዛሬም ወደፊትም ደግሞም ለዘለዓለም
ስብሐት ለአብ.....
ከዚህ ከማራኪው ከኃላፊው ዓለም
የጠራ ይድናል የፈጣሪውን ስም(2)
በእውነት ያለሐሰት ያለጥርጥር
ስብሐት ለአብ.....
ከቶ መደኃኒቱን የሚጠላ የለም
ኑሯችን አንዲያምር አንድነታችንም(2)
ይኸው ተገኝተናል ሁለት ሦስት ሆነን
ስብሐት ለአብ.....
ያልከውን አስበህ አናንተ ሁላችሁ
ስሜን ከጠራች ሁለተ ሦስት ሆናችሁ(2)
እኔም አገኛለሁ በመካከላችሁ
ስብሐት ለአብ.....
ጥቅስ: ኢዮ2 ÷ 32 ማቴ 18 ÷ 20

መዝሙር
ስብሐት ወክብር
ስብሐት ወክብር ለሥላሴ(2)ይደሉ(2)
ተዋህዶአውያን ይቤሉ አስመ ፈጠረነ በእስትንፋሱ ወበቃሉ(2)
ትርጉም: ክብርና ምስጋና ለሥላሴ ይገባል የተዋህዶ ልጆችም ሥለሴ በአርአያችን እንፍጠር ብለው ፈጠሩን የሕይወትንም እስትንፋስ እፍ አሉብን ብለው ያምናሉ::
ጥቅስ: ዘፍ1 ÷ 26 ዘፍ2 ÷ 7

መዝሙር
አብ ወወልድ
አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሥላሴ (2)
የሲዎልን እሳት ትፈራለች ነፍሴ(2)አንተው አድናት አምላከ ሙሴ(2)
ጥቅስ: ሰዓታት

መዝሙር
የሥላሴን መንበር
የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት
ድንግልን ከመሀል ሚካኤልን ከፊት
አእላፍ መላዕክት ሲሰግዱ በፍርሃት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን ድምቀት
እዩት ተመልከቱት የሰማዩን አባት
የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት
እያሸበሸቡ የሰማይ መላዕክት
ካህናተ ሰማይ ቅዱስ፣ቅዱስ፣ቅዱስ ሲሉት
ይህንን ልዩ ክብር ሲያዩ የታደሉ
በጽድቅ ስራቸው በምድር ይታያሉ(2)
የሥላሴን መንበር.....
የቅዱሳን ሕብረት የቅዱሳን ሀገር
ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር
ጽድቅና ርህራሔ የተመላ ሠማይ
አግዚአብሔር ያድለን በትንሣኤ አንድናይ(2)
የሥላሴን መንበር.....
ጥቅስ: ኢሳ6 ÷ 1-3 ራዕ4 ÷

መዝሙር
አምኩሉ ይሔይስ
አምኩሉ ይሔይስ በሥላሴከ ተአምኖ(2)
ወላዲትከ (2)ወላዲትከ ተማኅፀኖ(2)
ከሁሉም ከሁሉም ሥላሴን ነው መማን መመስገን(2)
ወልድን በወለደች (2)ድንግል አማላጃችን በእርሷ አንማጸን(2)
ጥቅስ: መልክአ ኢየሱስ

መዝሙር
ስብሀት ለአብ ለአሀዜ ኩሉ
ስብሐት ለአብ ለአሀዜ ኩሉ ዓለም
ስብሐት ለወልድ ለገባሬ ኩሉ ዓለም(2)
ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ለዘያርህዎ ክረምተ በበዓመት(2)
ትርጉም: ዓለምን ለያዘ ለአብ ምስጋና ይገባል ዓለምን ለሚገዛ ለወልድ ምስጋና ይገባል ክረምትን ለሚያፈራርቅ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባል::
ጥቅስ: ኢሳ6 ÷ 1-4 ኢሳ44 ÷ 24 ኢሳ45 ÷ 8 ዮሐ1 ÷ 1-5

መዝሙር
ነአምን በአብ
ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ(2)
ወነአምን(4) ነአምነ በመንፈስ ቅዱስ
ትርጉም፡-በአብ እናምናለን በወልድ እናምናለን በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን::
ጥቅስ፡- ማቴ 28 ÷ 19 1ኛ ዮሐ 2 ÷ 23-25
2ኛ ዮሐ 1 ÷ 9

መዝሙር

እናምናለን በአብ

አናምናለን በአብ አናምናለን በወልድ
አናምናለንበመንፈስ ቅዱስ (2)ፍጹም ጥርጣሬ
ሳይኖር በአንድ አምላክ መኖር (2

መዝሙር

ኢያቄም ወለዳ

ኢያቄም ወለዳ ኢያቄም(2)
ዳዊት ዘመዳ ኢያቄም ወለዳ(2)
ትርጉም፡- ኢያቄም የወለዳት እመቤታችን
የንጉሱ የዳዊት ዘመድ ናት::
ጥቅስ፡- ማቴ 1÷16

መዝሙር

ድንግል ተወለደች

ድንግል ተወለደች የአምላክ እናት
ድንግል ተወለደች የዓለም መድኃኒት
ድንግል ተወለደች(2)አመ ምህረት
አኛን ደስ ይበለን ኃጥአንን በሙሉ
ተወልዳለችና ድንግል እመኩሉ
ሀሴትን አድርጉ(2) የአዳም ልጆች ሁሉ(2)
የምሥራች ዛሬ ድንግል ተወለደች
ተወልዳም አምላክን ፈጣሪን አስገኘች
ምህረትን ለኛ(2)ለኃጥአን አስጠች(2)
ፀሐይን የምትወልድ ወልደ አምላክን
ከዘለዓለም ጥፋት የሚያድነን አኛን
ተገርፎ ተሰቅሎ(2)ቤዛ የሚሆነን(2)
ጥቅስ፡- ኢሳ 11÷9

መዝሙር

ሃና እም አነስት

ሃና እም አንስት ተአቢ ወትቴአል(2)
እሰመ ወለዳት ቃል ለድንግል ለቅድስት ድንግል
ዘወለደት ቃል በከመ ዜነው በወንጌል ዮሐንስ
በወንጌል(2)
ትርጉም፡-

ጥቅስ፡- ዮሐ 1÷14 19÷25

መዝሙር

ነይ ነይ ድንግል ማርያም

ነይ ነይ ድንግል ማርየም
አፅናኝና አማላጂ ተስፋዬ ሁኚ ለዘለዓለም
ኃጢአያቴ በዝቶ የበደሌ ሸክም በጣም የከባደ
አጨሃለሁኝ ካንቺ ሥጋን ነስቶ ወደ ተዋሀደ
ነይ ነይ ማርያም.....
ከገነትና ከመንግስተ ሠማይ ተስደን አንዳንቀር
ሰለወደደ
ቅዱስ የአግዚአብሔር በግ በገዛ ፈቃድ ለኛ ሲል
ታረደ
አዳምን ለማዳን በጥንታዊ ፍቅሩ ስለተገደደ
መሀሪ ይቅር ባይ በቤተልሔም በረት ለኛ ተወለደ
ነይ ነይ ማርያም.....
ኃጥአንን ለማዳን ንፁህ መስዋዕት አንዲሠዋ ስለወደደ
መሀሪ ይቀረ ባይ በቤተልሔም በረት ለኛ ተወለደ
ነይ ነይ ማርያም.....
ጥቅስ፡- ኢሳ 1÷9

መዝሙር

ኢያቄም ወሃና

ኢያቄም ወሃና አናት አባትሽ
ቤተ አገዚአብሔር ወስደው ስአለት የሰጡሽ
መና ከሰማያት የወረደልሽ
ፍፁም ድንግል የሆንሽ ማርያም አንቺ ነሽ
ኦ. ፅረሀ ክርስቶስ ማርያም አንቺ ነሽ(3)
ጥቅስ: መዝ44(45) መዝ65(66)13-20 መዝ86÷1

መዝሙር

ሲተ ሃና

ሲተ ሃና ለነፍስየ ዓመተ ሃና(2)
ሃበ ተስፋ ሕይወት ተሰራ(2) ተዶሎሙ በፃታ(2)
ትርጉም:

ጥቅስ: መኃ6÷9 1ኛ ሣሙ2÷1 መዝ86÷1

መዝሙር

ምስራቀ ምስራቃት

ምሥራቀ ምሥራታት ሙሳሽ ፀሐይ አግዝአትየ ዘመና
ሙዳይ(2)
ዘመና ሙዳ ማርያም ዘመና ሙዳይ(4)
ትርጉም: የሕብስት ክርስቶስ መገኛ መሶብ የፀሐይ
መወጫ ምስራቅ አንቺ ነሽ
ጥቅስ: ት.ሕዝ 4÷1-5

መዝሙር

ንፅህተ ንፁሐን

ንፅሕተ ንፁሐን ከዊና ከመታቦተ ዶር ዘሲና ውስተ
ቤተመቅደስ ነበረት በድንግልና ነበረት(2)
ሲሳያ ህብስተ መና ወስቴ ሃኒ ስቴ ጽሙና(2)
ትርጉም: ከንፁህንም ሁሉ ንፁህ ሃና በሲና
አንደነበረችው ታቦት በድንግልና በቤተመቅደስ
ኖረች ምግቧም ህብስተ መና መጠጧም
የፀጥታ መጠጥ ነው::
ጥቅስ: ዘፀ 25÷10-22 መዝ 144÷45

መዝሙር

ሃሌ ሉያ ክነፈ ርግብ

ሃሌ ሉያ ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር(2)
ወገበዋቲ ሃኒ ሐመልማለ ወርቅ በሐመልማለ ወርቅ(2)
ትርጉም: ከወርቅና ከብር የተሰሩ የርግብ ክንፎች ምስያ
ነች ጐንና ጐናቿም በወርቅ የተጌጡ ናቸው::
ጥቅስ: መኃ4÷1-2

መዝሙር
አንቲ ምስራቅ
አንቲ ምስራቅ ለወልድኪ ፀሐየ ጽድቅ አማን በአማን(2)
አማን በአማን(2)ኢይሀልቅ ኪዳንኪ ወሳዲተ አምላክ(2)
ትርጉም: አንቺ ምሥራቅ ነሽ ልጅሽም ፀሐየ ጽድቅ ነው በእውነት አንቺ የአምላክ እናት ቃል ኪዳንሽ አያልቅም::
ጥቅስ: ሚል4÷2

መዝሙር
እመቤታችን ሳንቺ
እመቤታችን ሳንቺ ሰላምታ ይገባሻል(2)
ከሴቶች ሁሉ ተመርጠሻል(2)
ሀርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል
ተዘጋጀሳት(3) የመመረጥ ኃይል
እመቤታችን ሳንቺ.....
እያረጓጎት የሠማይ መላእክት(2)
ቤተ መቅደስ ኖረች(3) አስራ ሁለት ዓመት
እመቤታችን ሳንቺ.....
መንፈስ ቅዱስም እንደቀረባት አውቆ(2)
ሰገደሳት(3)ዘካርያስ ታጥቆ
እመቤታችን ሳንቺ.....
መንፈስ ቅዱስም እንደቀረባት አውቃ
ተሳስመቻት(3) ኤልሳቤጥም ታጥቃ
እመቤታችን ሳንቺ.....
አያስደንቅም ወይ የማርያም ትህትና
ውኃ ስትቀዳ(3) የአምላክ እናት ሆና
እመቤታችን ሳንቺ.....
የምንጭ ውኃ ምስጢር የሚያመለክተው(2)
የአምላክ መገኛ ምንጭ(3) እርሷ መሆኗን ነው
እመቤታችን ሳንቺ.....
ጥቅስ:

መዝሙር
ነይ ነይ የኛ እመቤት
ነይ ነይ የኛ እመቤት ነይ ነይ
የዓለም መድኃኒት ሙዳይ
የአዳም ዘር ሁሉ ሲሳይ
ነይ ነይ ማርያም ነይ ነይ
አምላክ ከሰማይ ያየሽ
የወገኖችሽ ክርር ነሽ
የአህዛብ ሁሉ ድኅነት
በአንቺ ተገኘ በእውነት
ነይ ነይ .....
የቤተ መቅደስ አጣን
ያማረ ቅመም ምጥን
መልካም ማዓዛ ሽተትን
ልጅሽ ተሰዋ መድኃን
ነይ ነይ .....
ፀሐይ ወጣልን ከአቅፍሽ
ሰማዕታት ሁሉ ከበቡሽ
መሰላል ሆነሽ ሊድኑ
በልጅሽ ሥራ ያመኑ
ነይ ነይ .....
ክብርሽ ተገልጾአል በልጅሽ
አግዚአብሔር አንዱ ቀደሰሽ
የቃሉ ሕንፃ ሆነሻል
አብ በሰማያት ወደሻል
ነይ ነይ .....
ጥቅስ:

መዝሙር
ማርያመ ድንግል
ማርያም ድንግል ወሳዲትቃል (2)
ንኢ ድንግል(4) ድንግል ወሳዲተ ቃል(2)
ትርጉም: ቃል የተባለ ወልድን የወለድሽ እመቤታችን ሆይ ወደ እኛ ነይ::
ጥቅስ፤- ዮሐ 1÷14

መዝሙር
ሰላም ለኪ
ሰላም ለኪ አንዘ ንሰግድ ንብለኪ(2)
ማርያም እምነ ናስተበቁ አኪ(2)
ትርጉም: ሰላም ላንቺ ይሁን አያልን አንሰግድልሻለን አናታችን ማርያም እንማልድሻለን
ጥቅስ: መዝ 88÷5 ኢሳ 60÷14

መዝሙር
ሰላም ላንቺ ይሁን
ሠላም ላንቺ ይሁን (3) ማርያም ድንግል(2)
የሴቶች መመኪያ የሴቶች(2)አክሊል
ሠላም ላንቺ ይሁን(3)የሁሉ እመቤት(2)
የኃጥአን ተስፋ የዓድቃን (2)ሕይወት
ሠላም ላንቺ ይሁን(3)የሁሉ ወዳጅ(2)
የጽድቅ መሰላል የዓለም(2) አማላጅ
ሠላም ለወለድሽው(3)አምላካችንን(2)
ሰማይና ምድር የማይችሉ(2)ትን
ሠላም ለእመቤቴ (3) አምላክን ለወለድሽ
የሰማይ መላእክት የሚያመሰግኑሽ(2)
ሠላም ለእመቤቴ(3) አምላክ ለመረጠሽ
ከሴቶቹ ሁሉ የተባረክሽ ነሽ(2)
ጥቅስ: ሚክያስ 4÷6-13
መዝ86(87)

መዝሙር
የዓለም መድኃኒት ድንግል
የዓለም መድኃኒት ድንግል ወስተ ኢያቄም ወሃና
ሳንቺ ይሁን ሳንቺ ክብርና ምስጋና(2)
ተቂመ ማህቶት ድንግል የኃጥአን ምድር አስኝታ
ችግር አንዳይገጥመን በላይኛዪ ቦታ
ቃልኪዳንሽ ለኛ ይሁነን መከታ
የዓለም ፀሐይ ድንግል ክልልተ ሞገስ ወግርማ
ቦታችን እንዲሆን ከፃድቃን ከተማ
አርቂልን ከኛ ያን ከባድ ጨለማ(2)
የማህፀንሽ ፍሬ ክረስቶስ ንጉሰ ሰማይ ወምድር
አንቺን መርጦ ለአንቺ ስለሰጠሽ ክብር
ቀለስልን ለኛ የችግር ቀንበር(2)
ምልዕተ ምሕረት ወተስፋ የዓለም ቤዛ ድንግል
ፃድቃን በበረሃ በዱር በገደል
ያለቅሳሉ ካንቺ እንዲያገኙ ኃይል(2)
ጥቅስ: ሉቃ1÷26-31

መዝሙር
የሰማይ የምድር
የሰማይ የምድር የአርያም ንግስት
አንቺ ነሽ እመቤት የአምላክ እናት
እኸ ድንግል አማልጅን
እኸ ቅድስት ተራጅን
ለሔዋን ተስፋዋ ለአዳም ዘር ሕይወት
ለድኀነቱ ምክንያት አንቺ ነሽ ንጽህት
የኦሪት መጽናኛ የዓዲስ ኪዳን በር
የወንጌል መሰረት የአምላክ ማህደር
እኸ ድንግል .....
የአብርሃም አርሻ የምስጢር ዋሻው
አናትና ድንግል ሁለቱን ሆንሸው
የኤፍሬም ውዳሴ የያሬድ ውብ ዜማ
የማትጠልቂ ፀሐይ የሃይማኖት ሻማ
እኸ ድንግል .....
ጥቅስ: ራዕ12÷1

መዝሙር
የአብ ቃል አክብሮሽ
የአብ ቃል አክብሮሽ እናት ያደረገሽ
አግዚአብሔር በቃሉ ፍፁም ያከበረሽ
የምንመካብሽ መሰላል አንቺ ነሽ(2)
ቅድስና ሳንቺ ጽድቅም ሳንቺ ሆኖ
ዓለም የተጠረ ባንቺ ተወሰኖ
የገነት ፈረ ነሽ ሕይወት ያፈራሽ
አንቺን ስመረጠ አንቺን ሳነፃሽ
ምስጋና ይደረሰው ለቸር አምላክሽ
አዳም የኖረብሽ የኤደም ገነት ነሽ
የኤፌሶን ወንዝ ወርቅ የሚፈልቅብሽ
የግዮን ማዕበል ኢትዮጵያን የከበብሽ
ዮርዳኖስ ሆነሽ አህዛብን ፈወስሽ
በልጁ ቃልነት አብም አከበረሽ
መዓዛሽን ወዶ ወልድ ዋህድ ዋጀሽ
አብም በሰማያት በሕሊናው ፃፈሽ
መንፈስ ቅዱስ መጥቶ አንቺን አከበረሽ
እመካብሻለሁ እመቤቴ ስልሽ(2)
ወልድ በመውደዱ ካንቺ መወለዱ
ንፁህ ሆኖ አግኝቶት ቅዱሱ ሥጋሽን
ለቃሉ ማደሪያ ጽላትና ታቦት
በብሩህ ደመና ተመስለሽለት
ከሥጋሽ ተከፍሎ ከደምሽ ደመ ወስዶ
ከነፍሽም ነፍስን ፍፁም ተዋህዶ(2)
ጥቅስ: መኃ4÷12 ዘፍ2÷13 ኤፌ1÷4
መዝ46÷5

መዝሙር
የብርሃን መውጫ
የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል
የተነበየላት ነቢየ ህዝቅኤል(2)
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማህደር(2)
የዳዊት መሰንቆ የጌዲዎን ፀምር
በገነት መካከል ያለች ለምለም ሣር
አፍርታልናለች ያለ ወንድ ዘር
እሰቲ እናመስግናት እንዲህ በማለት
ቅድስት አናታችን ስብህያት ወብርክት
አንቀፀ ብርሃን ማዕረገ ሕይወት
አዘክሪ ድንግል ለልጅሽ በአውነት
በደህና እንዲያደርሰን ለመጭው ዓመት(2)
እንድናገኝ ፍቅር እንደ ሐዋርያት
እንደ እመቤታችን አርምሞ ትእግስት
ያድለን ፈጣሪ ፍፁም መድኃኒት(2)
ጥቅስ:
መዝሙር
አስተርዮ
ሐዋርያት ሁሉ አዘኑ ተከዙ
በስብሐት በማሕሌት ስጋዋን ገነዙ
አስተርዕዮ በሰማይ ኮነ
አስተርዕዮ አስተርዕዮ
በክብር ወሰዷት መላእክት በራማ
እያማሰገኗት በጥዑመ ዜማ
አስተርዮ .....
የማትፈቅጂ ድንግል ስኃፕአን ሞት
እባክሽ አማልጅኝ ስንስሀ ጥቂት
አስተርዮ .....
የምታምር ርግብ ሰሎሞን አለሽ
ስጋሽን አንፅቶ ወልድ መረጠሽ
አስተርዮ .....
ሞትንስ መሞትን ለሁሉም ይገባል
የድንግልስ መሞት በጣም ያሳዝናል(ያስደንቃል)
አስተርዮ .....
ጥቅስ: መኃ2÷14 መዝ44÷5-6

መዝሙር
ስጋ ሰብ መዋቲ
ወገብረ መንጦላዕተ(2)
ስጋ ሰስ መዋዕቲ(2)
ትርጉም: የሚሞት (የሟች) ሰውን ስጋ ተዋሃደ
ጥቅስ:
መዝሙር
አረገቷ ውስተ ሰማያት
አርገቷ ውስተ ሰማያት(2)
ወበአታ (2) ውስተ ገነት(2)
ትርጉም: አመቤታችን ወደ ሰማይ አረገች አረገቷ ወደ
ነገት ነው ሐዋርያት ስጋዋን በምስጋና ነገዙ::
ጥቅስ :

መዝሙር
በሰላም ንሺ
በሠላም ንሺ ንሺ ማርያም(2)
ተናዘዘኒ ሀዘነ ልቦየ
በሠላም ንሺ ንሺ ማርያም(2)
ምስለ ሚካኤል (2)ወገብርኤል
በሠላም ንሺ ንሺ ማርያም
ምስለ ሱራፌል(2)ወኪሩቤል
በሠላም ንሺ ንሺ ማርያም(2)
ምስለ ዑራኤል (2)ወራጉኤል
በሠላም ንሺ ንሺ ማርያም(2)
ምስለ ኰሉሙ(2)ቅዱሳን
በሠላም ንሺ ንሺ ማርያም(2)
ምስለ ወልድኪ (2)አማኑኤል

በሠላም ንዒ ንዒ ማርያም
ትርጉም: የልቦናዬን ሐዘን ታረጋጊልኝ ዘንድ
ማርያም ሆይ ከሚካኤል፣
ከገብርኤል፣ ከሱራፌል፣
ከኪሩቤል፣ከዑራኤል
ከራጉኤልከ፣ሁሉቅዱሳንና ከልጅሽ ጋር
በሠላም ነይ::
ጥቅስ:

መዝሙር
ድንግል እመቤቴ

ድንግል እመቤቲ አዛኝቷ ሆይ
አለሁኝ ከጐንሽ አትይኝም ወይ
ብቸኛም እንደሆንኩ ድንግል
ድንግል ሆይ ታውቂያለሽ "
ከሔድኩበት ሁሉ ድንግል
አትርሺኝ አባክሽ
አናትም የለኝም ድንግል
አንቺው ነሽ አናቴ
አባትም የለኝም ድንግል
ልጅሽ ነው አባቴ "
እርሱም ይጠብቀኝ ድንግል (2)
ንገሪው በሞቴ
ድንግል እመቤቴ.....
ድንግል እመቤቴ ድንግል
ተማጽኜሻለሁ
ካንቺ ተለይቼ ድንግል
ወዴት እሄዳለሁ
በሌትም በቀንም ድንግል
ስምሽን አጠራለሁ (2)
ድንግል እመቤቴ.....
ሐዘንና ችግር ድንግል
ተደራርቦብኝ
ታርዤ ተርቤ ድንግል
ችግር ፀንቶብኝ
አያልኩኝ ስጠይቅ ድንግል
ወገኖቼ አርዱኝ
አይተውኝ አለፉ ድንግል
ሁሉም አያዩኝ
ድንግል እመቤቴ.....
ሩህሩህ ለሁሉም ድንግል
መቼውም አንቺ ነሽ
በቃኝ ቆርጫለሁ ድንግል
የትም ላልለይሽ
አንቺም አትለይኝ ድንግል
ቃሌን ተቀብለሽ(2)
ድንግል እመቤቴ.....
ጥቅስ መዝ44÷9-16

መዝሙር
ማርያም እመቤቴ

ማርያም እመቤቴ የአምላክ እናት
ማደሪያ የሆንሽው ዙፋን ለመለኮት
ከሴቶች ሁሉ አንቺ ነሽ የተባረክሽ የነፃሽ በእውነት
ከቶ እንደምን ቻልሽው መድኃኔዓለምን
ሠማይና ምድር የማይችሉትን
ለዚህ የተመረጥሽ ታላቂ እድለኛ
ምሕረትን ከልጅሽ ለምኝልን ለኛ(2)
ማርያም እመቤቴ.....
የነቢያት ሞገስ የሐዋርያት
የሰማዕታት አክሊል የፃድቃን እናት
የኛ መመኪያችን የኃጥአን ተስፋ
ወልድን በመውለድሽ ሀዘናችን ጠፋ(2)
ማርያም እመቤቴ.....
ቅዱሳን በገነት ሲያመሰግኑሽ
መላእክት በሰማይ ሲያገለግሉሽ
እኛም የአዳም ልጆች ከመረሬት ሆነን
ስዓሊነ ቅድስት እንልሻለን
ማርያም እመቤቴ.....
ጥቅስ: ሉቃ1÷28 2ኛ ዜና2÷1-6

መዝሙር
ኪዳነ ምህረት

ኪዳነ ምሕረት የሁሳችን እመቤት
ኪዳነ ምሕረት የአንድዮ ወላጅ እናት
ሰላም ሳንቺ ይሁን ኪዳነምሕረት
ቤዛዊት ዓለም እመቤት
ከሴቶች ከቶ ኪዳነ ምሕረት
የሚያይልሽ የለም እመቤት
ኪደነ ምሕረት.....
አዳም ቢወድሽ ኪዳነምሕረት
ከአዳም ተገኘሽ እመቤት
ራሱን ሰዋልን ኪዳነምሕረት
የማጎፀን ፍሬሽ እመቤት
ኪደነ ምሕረት.....
ድንግል ማርያም ኪዳነምሕረት
ርህርት አዛኝ ነሽ እመቤት
ስዓሊነ ቅድስት ኪዳነምሕረት
ከአንዱ ከልጅሽ እመቤት
ኪደነ ምሕረት.....
ጥቅስ: መዝ88÷3

መዝሙር
አምላክ ለእኛ ብሎ

አምላክ ለእኛ ብሎ ቃልኪዳን የሰጣት
የሰዎች አማላጅ ኪዳነ ምሕረት ናት(2)
እንደ አማለድሽው በላየ ሰብን
እኛንም እንዲሁ አደራ አማልጅን(2)
ምሕረት እንድናገኝ ከአምላካችን
አማላጅ ትሁነን እመቤታችን(2)
ከአንቺ በተገኘው በመልካሙ ፍሬ
ዓለም ተቀድሷል ይህውና ዛሬ(2)
ካህናት በከበሮ ሲያመሰግኑሽ
እኛም በጭብጨባ እንዘምርልሽ(2)
ስምሽ ግርማ ያለው ኪደነ ምሕረት
የሰዎች አማላጅ የጌታዬ እናት(2)
ጥቅስ: 62÷1

መዝሙር
ኪዳንኪ ኮነ

ኪዳንኪ ኮነ(3)
ለኃጥአነ ተስፋነ(2) ኪደነኪ ኮነ(2)
ትርጉም: ቃልኪዳንሽ ለኃጥአን ተስፋ ሆናቸው
ጥቅስ:

መዝሙር
ሶበሰ ኪዳንኪ
ሶበሰ ኪዳንኪ ምክንያተ ድሒን ሃሎ(2)
ፈስገ አሳት ወደይን ኢማስጠመ ኩሎ(2)
ትርጉም፡ ቃልኪዳንሽ የመዳናችን ምክንያት በሆነ
ጊዜ የአሳትና የጥፋት ባሕር
አያሰጥመንም::
ጥቅስ፡

መዝሙር
ተናዝዘብኪ አኮኑ
ትናዝዘብኪ አኮኑ ሕሊና ቀዳማይ አብ(2)
ኪዳነ ምሕረት ማርያም(3) ኪዳነ አምላክ(2)
ትርጉም፡ አምላክ ቃልኪዳን የተሰጠሽ
አመቤታችን ነሽ ስላንቺ ተነግሮልሻልና
ቃል ኪዳን የተቀበልሽ ነሽ::
ጥቅስ፡

መዝሙር
መሠረተ ሕይወት
መሠረተ ሕይወት ማርያም ወጥንተ መድኃኒት
ዘአምቀዲሙ(2)
ለወልድኪ(2) አምሳለ ደሙ(2)
ትርጉም፡ ቅድመ ዓለም የነበረ መድኃኒት
ከሚባል የተገኘሽ የሕይወት መሠረት
ማርያም አንቺ ነሽ መሠረትነሽም
የልጅሽም የደሙ ምሳሌ ነው::
ጥቅስ፡ መልክዐ ኤደም

መዝሙር
አንቺ ነሽ ተስፋው
አንቺ ነሽ ተስፋው ለአዳም ኪዳነ ምሕረት(2)
በተሰደደ ጊዜ ከገነት(2)
ጥቅስ፡ ቅዳሴ ማርያም

መዝሙር
ተንስዑ ንሁር
ተንስዑ ንሁር ወጣት ሕፃናት(2)
ጸበሏ ያድናል(2) ኪዳነ ምሕረት(2)
ጥቅስ፡ ዮሐ 5÷1-9

መዝሙር
የማነ የማነ ሕይወት
የማነ የማነ ሕይወት
አንቺ ነሽ ኪዳነ ምህረት(2)
ቅድስት አመቤቴ የአምላክ እናት
ሁነሽ የተገኘሽ ንጽሕይት ቅድስት
አንቺ ነሽ(2)ኪዳነምህረት(2)
የማነ የማነ.....
የሲና ሐመልማል የሰው ልጅ ሕይወት
አንቺን የመረጠ ይክበር መለኮት
አንቺ ነሽ(2) ኪዳነ ምህረት
የማነ የማነ.....
ጥቅስ፡ ዘዳ3÷1-6 ሉቃ1÷26-33

መዝሙር
ኪዳነ ምሕረት አመቤት
ኪዳነ ምሕረት አመቤት
የዓለም ሁሉ መድኃኒት(2)
ቅድስተ ቅዱሳን ንጽዕህይት
አንቺ ነሽ ለአምላካችን እናት
ጌታ አንቺን መረጠሽ ልዩ አድርጉ
በሚያስደንቅ ምስጢሩ ተዋሕዶ
ለልዑል ማደሪያነት የተመረጥሽ
ያስ ሕማም ወለድሽው ድንግል ሆነሽ
እናትነት ድንግልና(2)
አስተባብረሽ ይዘሻልና (2)
ድንግልም እናትም አመብርሃን
ንጽሕተ ንጹሐን እኛን አማልጂን(2)አኽ
ጥቅስ፡ ዮሐ 1÷14

መዝሙር
ማርያም ሀዘነ ልቦና
ማርያም ሀዘነ ልቦና ታቀልል(2)
ሀዘነ ልቦና(4) ታቀልል(2)
ማርያም የልብን ሀዘን ታቀላለች(2)
የልብን ሀዘን(4) ታቀላላች (2)
ጥቅስ፡- ዮሐ 2÷1-11

መዝሙር
ድንግል ሆይ አዘኝልን
ድንግል ሆይ አዘኝልን
ድንግል ሆይ አራሪልን
ድንግል ሆይ ከልጁሽ አስታርቂን
በሃና በአናትሽ ተማጽኜሻሁ
በኢያቄም በአባትሽ ተማጽኜሻለሁ
በስደት በልደትሽ ተማጽኜሻለሁ
ከልጅሽ አስታርቂኝ ድንግል ብዬሻለሁ
ድንግል ሆይ .....
በአንድዬ በልጅሽ ተማጽሼሻለሁ
በቃል ኪዳንሽም ተማጽኜሻለሁ
ድንግል ሆይ ጠብቂኝ ክፋ አንዳልናገር
ከምስጋናሽና ከበጉ በስተቀር
ድንግል ሆይ .....
በአምስቱ ሀዘኖችሽ ተማጽኜሻለሁ
በረሃብ በጽምሽ በማጽኜሻለሁ
በሀዘን በስደትሽ ተማጽኜሻለሁ
ከልጅሽ አስታርቂኝ ድንግል ብዬሻለሀ
ድንግል ሆይ .....
ከፍቅርሽ አትለይኝ ደግመም በሃይማኖት
ህጉንም ጠብቄ አንድኖር በሥርዓት
ከስላዬ ሁኝኝ ጠብቂኝ ከጠላት
ከዚያ ከዲያብሎስ የኃጢአት አባት
ድንግል ሆይ .....
ጥቅስ፡ የሐ 2÷1-9

መዝሙር
ማርያም በስምሽ
ማርያም በስምሽ ይዘናል ቀኖና
ትንሣኤሽን ልጅሽ ያሳየናልና
ፃም ማለት እንግዲህ ይኸው ነው ስርዓቱ
ሐዋርያት ፃመው ለእኛ አበረከቱ
ነፍስና ስጋችን በመብል ተጣልተው
ሽማግሌ ሆኖ ፃም አስታረቃቸው

አብረው አየዋሉ አብረው አያደሩ
አያምርም አይመስልም በመብል ሲጣሉ
ነፍስም ከስጋዋ መለየቷን አውቃ
የዓለም ተድላዋን ደስታዋን ንቃ
በፃም በሱባኤ ትኖራለች ታጥቃ
ነፍስም ለስጋዋ ትመክረው ጀመረች
በብዙ ምሳሌ አያመሳሰለች
ሥጋዬ ሞኝ ነህ መብልን አትውደደው
ከአዳም አንስቶ ከመጀመሪያው ሰው
መብል ሲጐዳ እንጂ ሲጠቅም መች አየነው(2)
ጥቅስ፡ ኢሣ 58 በሙሉ

መዝሙር
የዘለዓለም ቤቴ
የዘለዓለም ቤቴ(2) እመቤቴ ነሽ መድኃኒቴ
የዘለዓለም ቤቴ
የዘለዓለም ሐብቴ(2) ድንግል ማርያም ነሽ
መድኃኒቴ የዘለዓለም ሐብቴ
አንቺን ደዜ ለመሄድ በተዋህዶ ፀንቼ
አማፀንሻለሁ እጆቼን ዘርግቼ
የዘለዓለም ቤቴ.....
ወደ ጽድቅ ስጓዝ እንዳልሰናከል
አንቺን ተመርኩዜ ልሂድ ወደ ልዑል
የዘለዓለም ቤቴ.....
የልጅሽ በረከት የአምላክ ስጦታ
በአንቺ ይታደላል የዘለዓለም ደስታ
የዘለዓለም ቤቴ.....
ከበደሌ ብዛት ወድቄ እንዳልቀር
ካሁኑ አስታርቂኝ ከቸሩ ልጅሽ ጋር
የዘለዓለም ቤቴ.....
መምጫው አይታወቅ ያ ተልከስካሽ ውሻ
ተከላከይልኝ ድንግል የኔ ጋሻ
ዘለዓለም ቤቴ.....
መግቢያ ስከፍትለት የኃጢአትን በር
ዝጊበት አምአምላክ አንቺ የኔ አጋር
የዘለዓለም ቤቴ.....
አንገት አታስደፊ ፊት አታስቀልሺ
የሕይወቴ ተስፋ ማርያም አንቺ ነሽ
የዘለዓለም ቤቴ.....
ጥቅስ፡ መዝ131÷14-16

መዝሙር
ሰላም ሰላም ማርያም
ሠላም ሰላም (2) ማርያም ድንግል
ልመናሽ ለሚያምኑ ድኅነት ያሰጣል(2)
ደቀ መዛሙርቱ በሀሳብ ሲዋኙ
ይኸው በቅርብ ቀን ምልክት አገኙ
ሰላም ሰላም.....
ለኛ ለልጆችሽ ኃጢአት ላይከመን
ከልጅሽ ይቅርታን ድንግል ለምኝልን
ሰላም ሰላም.....
በሃና በኢያቄም እመቤታችን
በዚች ቀን ባርኪልን ስብሰባችንን
ሰላም ሰላም.....
ጥቅስ፡ ዮሐ2÷1-5

መዝሙር
ድንግል ወላዲተ ቃል
ድንግል (2)ወላዲተ ቃል(2)
ኦሚማትሽ በጥር ነሐሴ መቃብር ድንግል
ያንችሽ የብቻው ነው ትንሣኤሽ ሲነገር ድነግል
ሥጋሽ በምድር ላይ የታለ አንደፍጡር ድንግል
አርጓል ወደ ሰማይ ከክርስቶስ መንበር ድንግል
ድንግል.....
ሥጋሽን ሲያሳርጉ መላእክት በሠማይ ድንግል
ቶማስ በደመና ሲመጣ መንገድ ላይ "
መግነዝ ተረከበ ለሐዋርያት ሲያሳይ "
ድንግል.....
ትንሣኤሽን ሽተው ግራ ቢገባቸው ድንግል
ሐዋርያት ፃመው ተገለጽሽላቸው "
ተቀብራ አልቀረችም ከምድር ከደጇ "
ወደ ላይ አርጋለች አርሷም አንደ ልጇ "
ድንግል.....
ለማየት ሲጓጉ የድንግል ትንሣኤ ድንግል
አረገቷን አወቁ በብዙ ሱባኤ "
አኛም አንፀልይ ደጇችን አንዝጋ "
ከወላዲት አምላክ አንድናገኝ ዋጋ "
ድንግል.....
ጧት ማታ አትዘንጉ ማሪኝ ከማለት ድንግል
ዝክሯን ከመዘከር ስሟን ከመጥራት "
ጊዮርጊስም ብሏል ሲዘራበት አጽሙ "
ምስለ ፍልሰትኪ ደምረኒ እሙ "
ድንግል.....
ጥቅስ፡ መዝ131÷8-9

መዝሙር
ወትቀውም ንግሥት
ወትቀውም ንግሥት(2) በየማን(2)
በአልባሰ ወርቅ(2) ዑጽፍት ወሀብርት(2)
ትርጉም፡ በወርቅ መጐናፀፊያ ተጐናጽፋ ንገሥቲቱ
በቀኝህ ትቀማለች::
ጥቅስ፡ መዝ 44/45/÷9-11

መዝሙር
ማርያም ድንግል ለደናግል
ማርያም(2) ማርያም ድንግል(2)
ለደናግል(2) ምክሆን ለደናግል(2)
ትርጉም፡ ድንግል ማርያም ለደናግል መመኪያ ናት::
ጥቅስ፡ ዘፍ3÷በሙሉ

መዝሙር
በመኑ በአምሳለ መኑ
በመኑ በአምሳለ መኑ ናስተማስለኪ(2)
አዛኝቴ ወላዲቴ ኦ ድንግል ምልአተ ውዳሴ(2)
ትርጉም፡ ማን በተመሠለው ምሳሌ እንመስልሻለን አዛኝቷ
ወላዲቷ ምስጋናን የተመላሽ ድንግል ሆይ
በምን እንመስልሻለን::
ጥቅስ፡ ሉቃ1÷28 ሉቃ1÷42-45

መዝሙር
እመቤታችን ሳንቺ
እመቤታችን ሳንቺ እናቀርባለን ምስጋና

አንቺ የወለድሽው ክርስቶስ
የዓለመ መድኃኒት ሆኗልና
ሕፃናት ስላውቁት ደግነትሽን በሙሉ
ወደ አንቺ ሁል ጊዜ ይማልላሉ
ከፈጣሪሽ አማልጅን አደራ
ጥቅስ፡ ዘፍ 18÷22-23 ማር9÷33-37

መዝሙር
እናታችን ቅድስት
እናታችን ቅድስት የዓለም ርህርህት(2)
እኽ አንስገድላት(2) አንስገድ (2)በእውነት
ስለምላክ እናት(2)
ጥቅስ፡ መዝ 86÷5

መዝሙር
በምን በምን አንመስላት
በምን በምን አንመስላት ድንግል ማርያምን
ምሳሌ የላትም (2) ክብሯን የሚመስል(2)
የሙሴ ጽላት ነሽ - የምሕረት ቃል ኪዳን
የያዕቆስ መሰላል - የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ - የኖህ ድንቅ መርከብ
የመላእክት እህት - መክብበ ርግብ(2)
በምን በምን.....
የሰሎሞን አክሊል - የእሮን በትር
የእዝራ መሰንቆ - የጌዲዮን ፀምር
ድንግል እመቤት ናት- የፃድቃኖች በር
ሆና የተገኘች - የአምላክ ማኅደር(2)
በምን በምን.....
የቅዱስን እናት - የፃድቃን እመቤት
በርሷ ስላደረ - አምላካዊ እሣት
ጨለማን ገላልጣ - ብርሃን ትሁነን
ከሚመጣው ፍዳ -አማልዳ ታስምረን(2)
በምን በምን.....
ከማር ይጣፍጣል - የማርያም ስም
እናቱ ናትና - ለመድኃኔዓለም
ይህ ዓለም የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ጽዮን - ይደረስሽ ምስጋና(2)
በምን በምን.....
ጥቅስ፡ መኃ 4÷7 ሉቃ1÷28

መዝሙር
አማናዊት ኪዳን
አማናዊት ኪዳን የሰው ልጆች ተስፋ
ድንግል ሆይ አማልጅን በሞት እንዳንጠፋ
የአባቶች ነቢያት ተስፋ ትንቢታቸው
የሐዋርያትም ጣዕመ ስብከታቸው
የሰማዕታት እናት የፃድቃን እመቤት
ደግሞም እህታቸው ስሠማይ መላእክት
አማናዊት.....
የነ ቅዱስ ኤፍሬም ድንቅ ድርስታቸው
የነ ቅዱስ ያሬድ ድጓ ዝማሬያቸው
የእምነታቸው ቅመም አንቺ ነሽ በእውነቱ
ስአባ ጊዮርጊስም ፀሎት ሰዓታቱ
አማናዊት.....
የአባ ህርያቆስ ምስጢረ ቅዳሴ
የመነከ√ሣት ስንቅ የኤፍሬም ውዳሴ
የሊቃውንተ አበው የምስጢር ቋንቋቸው

ጥቅስ፤- 1ኛ ጢሞ 3÷15 1ኛ ቆሮ 1÷18

መዝሙር
እዳ አስብን
የእመቤታችን አማላጅነቷን
ክብሯን የቀነስን ያዋረድን
እዳ አስብን (2) ከፈጣሪያችን (2)
የተሰጣት ሙሉ ሥልጣን
ክብር ያገኘች በቃል ኪዳን
ስሟን የጠራ አንደሚድን
በመጽሐፍ ሲነገረን
እዳ አስብን.....
ቤዛዊተ ኩሉ የተባለች
በእነ ቅዱስ ኤፍሬም የተመሰገነች
በእነ አባ ጊዮርጊስ ውዳሴን ያገኘች
በመናፍቃን ዘንድ ምነው ተዘነጋች
እዳ አስብን.....
ከሴቶቹ ሁሉ ልዩ ነች ስንል
በሁለቱም ወገን በፍፁም ድንግል
የብርሃን እናቱ ማርያም ስትባል
በደካማዎች ዘንድ እንዴት ትቃለል
እዳ አስብን.....
ቃና ዘገሊላ ከልጇ ጋር ሳለች
ከሠርግ ቤት ገብታ ድንግል አማልዳለች
አንኳንስ እመ አምላክ ቤዛዊተ ኩሉ
ፃድቃን ሰማእታት በእውነት ያማልዳሉ
እዳ አስብን.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ማርያም ድንግል
ማርያም ድንግል ምክሆነ ለደናግል ይእቲኬ ቤተ
ምስዐል ዘአስተአጸቡ ታቀልል(2)
ለኩሉ ፍጥረት ትትነብል በአክናፈ መላእክት ትትኬለል
ይእቲ ተዓብይ እምኪሩቤል ወትፈደፍድ እምሱራፌል
ትርጉም፡

ጥቅስ፡ ዘፍ 3÷በሙሉ ገላ 4÷4

መዝሙር
ሙሴ ዘርዕየ
ሙሴ ዘርዕየ (2) በደብረ ሲና(2)
ሐመልማላዊት አፅ(2) ሐመልማላዊት(2)
ሙሴ ያያት(2) በደብረ ሲና(2)
የለመለመች አጽ(2)የለመለመች(2)
ጥቅስ፡ ዘፀ

መዝሙር
ማሕደረ መለኮት
ማሕደረ መለኮት(2)
ማርያም እመ ብዙኃን(2)
ትርጉም፡ የአምላክ ማደሪያ የሆነች እመቤታችን
የብዙዎች እናት ናት።።
ጥቅስ፡

መዝሙር
ድንግል ማርያም የወርቅ መሰላል
ድንግል ማርያም የወርቅ መሰላል ነሽ (2)
ሠውና አምላክን ያገናኘሽ(2)
አባታች ያዕቀብ በፍኖተ ሎዛ(2)
አሸልቦት እንቅልፍ ተኝቶ ከጤዛ
ከምድር እስከ ሠማይ የምትደርስ መሰላል
ምሳሌሽን አየ ማርያም ድንግል
ድንግል ማርያም.....
መላእት ሲውጡ ሲወርዱ ከሠማይ(2)
እንዳየ ያዕቆብ ተኝቶ መንገድ ሳይ
ተስፋ አድርጎ ሲኖር የሠላሙን ዘመን
ይኸው ተፈፀመ ባንቺ በእናታችን
ድንግል ማርያም.....
ባንቺ በልጅሽ ሆነልን ሠላም(2)
ባንቺ ተፈፀመ የያዕቀብ ሕልም
ሰውና መላእክት ተለያይተው ሲኖሩ
በልጅሽ መወለድ በአንድነት ዘመሩ
ድንግል ማርያም.....
ጥቅስ፡ ዘፍ28÷15

መዝሙር
ኦ ርህርተ ሕሊና
ኦ ርህርተ ሕሊና አፍቅሮተ ሰብ ልማዳ(2)
ስእለ ጌሰሞ(4) ትመስል (3) እንግዳ(2)
ትርጉም፡ ሰውን መውደድ ልማዷ የሆነ
እመቤታችን ጌሴም በምትባል ምድር
በእንግድነት ተቀመጠች።።
ጥቅስ፡ መልክአ ሥዕል

መዝሙር
የደናግል መመኪያ
የአዋጅ ነጋሪ ቃል በበረሀ አየለ
የእግዚአብሔርን መንግስት አስተካክሉ እያለ
ምስክርነቱን ዮሐንስ ካስረዳ
ልባችን ለጌታ መልካም መንገድ ይሁን
የደናግል መመኪያ የነቢያት ገዳም
አውደ ዓመቱን ባርኪልን ድንግል ማርያም
ተራራው ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና
ካልተስተካከለ መንገድ የለምና
የእግዚአብሔርን መንገድ እንመስርት ሁሳችን
ማስፈያ እንዲሆነን ስመጪው ሀብታችን
የደናግል.....
ክፋትና ተንኮል ከልባችን ይጥፋ
ጽድቅና ርህራሔ በኛ ላይ ይስፋፋ
ሥጋና ደምህን በክብር አግኝተናል
ሕይወት እንዲሆነን አምላክ ተማጽነናል
የደናግል.....

ሁለት ልብሶች ያሉት ከማብዛት ልብስን
ስሌለው ያድለው ሁለተኛውን
ከበደላችንም እንፃን አደራህን
በክፋ እንዳንጠፋ እኛ ባሮችህ
የደናግል.....
ጥቅስ፡ ሉቃ3÷3-14

መዝሙር
እመቤታችን ማርያም ሆይ
እመቤታችን ማርያም ሆይ(2) በመላኩ ገብርኤል ሠላምታ
እንደተነገረሽ
ስላም እንላለን እኛም ልጆችሽ(2)
በሀሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ
የልዑል እናቱ ደግሞም የአሸናፊ
ማኅበራችንን <u>በእውነት ደግፊ</u>(2)
ከሴቶች ሁሉ <u>ተስይተሽ</u>(2) የተባረክሽ ነሽ
ቡርክ ከሚባለው ከማህፀንሽ ፈሬ
ፀጋን እንድናገኝ <u>ስምኝል ዛሬ</u>(2)
ስምኒ ጌታችንን <u>ይቅር እንዲለን</u>(2) በደላችንን
ሲያወርድ የነበረው ለእስራኤል መና
ቸሩ ፈጣሪያችን ከእንቺ ጋር ነውና
አሜን
ጥቅስ፡ ሉቃ1÷26-38 ኢሣ 44÷14-26
መዘ146÷ በሙሉ

መዝሙር
ርግብየ
ርግብየ (2) ማርያም እሙ ስእግዝየ
በቀስመ ወርቅ ፃፊ ስምየ
በአምደ ብርሃን ፃፊ ስምየ
በቀስመ ወርቅ ፃፊ ስምየ
የተመረጥሽ ጌጤ(2) ሽልማቴ
የክብሬ አክሊል ነይ እመቤቴ ርግብየ
ወደ እንቺ አጮሀለሁ በቸገረኝ ጊዜ
እንድታስቀሪልኝ የልቤን ትካዜ ርግብየ
ርግብየ.....
የማትፈርሺ መቅደስ ንጽህይት አዳራሽ
የመለኮት አሳት በማሕፀንሽ ያዝሽ ርግብየ
የድህነቴ ምክንያት የሕይወቴ ፋና
የችግሬ ደራሽ ርህርህተ ሕሊና ርግብየ
ርግብየ.....
ስጠራ ስምሽን ከጠዋት እስከ ማታ
ፈጥነሽ ድረሽልኝ እንዳልገላታ ርግብየ
የነቢያት ትንቢት የሠማዕታት አክሊል
የፀሎት ማረጊያ የወርቅ መሠላል ርግብየ
ርግብየ.....
ምርኩዝ መደገፊያ የሃይማኖት በትር
ሆነሽ የተገኘሽ የሕይወት ማህደር ርግብየ
መንገዴ ጨልሞ ወድቄ እንዳልቀር
ደግፈሽ አሻግሪኝ ያንን የኃጢአት ባሕር ርግብየ
ርግብየ.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
የብርሃን ጐርፍ ናት
የብርሃን ጐርፍ ናት ድንግል እናቻችን
ከሠማይ ያበራ ደስ አለው ልባችን
ፍቅርሽን ሠላምሽን ድህነት ይሁነን

ፍጥረት በሙሉ(2) ፊትሽ ደመደቃሉ
ፀጋሽ ይድረሰን(2 ይሰጠን እያሉ
የኔ ልብ መች ጽድቅ አለው አንቺን
ለማስተናገድ
የኃጢአት ጉተራ ነው የተመላ በስስት
ኧረ አንዴት(2) ድንግል ትኑርበት
አትፀየፍም የኔን ልብ ታሰናዳዋለች
ስለ ኃጢአቴ የኔ እናት ምልጃን ታቀርባለች
የብርሃን.....
ልባቸውን የዘጉ ድንግልን ለማስገባት
ሕሊናቸው ይመለስ እንፀልይ ለዚህ ጥፋት
አምላክን ይዛ ነው ድንግል የምትምጣው
እርሷን ስንመልስ ልጇን ነው የምናስቀይመው
የብርሃን.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
አዘኝልን ድንግል
አዘኝልኝ ድንግል አዘኝልኝ ቅድስት <u>አዘኝልኝ</u>(2)
ለኔ ለደካማው ኃጢአት ሳጠቃኝ አዘኝልኝ
ከአንድዬ ከልጅሽ ፈጥነሽ ለስታርቂኝ **?**
አዘኝልኝ.....
ሥጋዬ ለኃጢአት አንዳይዳርገኝ አዘኝልኝ
ድንግል በብርሃነ መስቀሉ ባርኪኝ "
አዘኝልኝ.....
ወጥመዱ አንዳይዘኝ የዓለም አሽክላ አዘኝልኝ
እመ አምላክ ደግፈኝ ከሰይጣን አሽክላ "
መርዙን አንዳይዘራ ጠላት በአካላቴ "
አደራ ጠብቂኝ ማርያም እመቤቴ "
አዘኝልኝ.....
አንቺ ታውቂዋለሽ የኔን ጉስቁልና አዘኝልኝ
የአማኑኤል እናት ስጭኝ ንጽህና "
" " " ቅድስና "
የባለወልድ እናት ስጭኝ ቅን ልቦና "
ለተጠማውሻ የራራሽለት "
ለኔም አራሪልኝ ኪደነ ምሕረት "
አዘኝልኝ.....
ደካማ ስለሆንኩ ክፋ አውሬ ሊውጠኝ አዘኝልኝ
አፋን ከፍቶብኛል ድንግል ድረሽልኝ "
ፈጥነሽ ድረሽልኝ የዓለም ጠባቂ "
አዘኝልኝ.....
አዘኝልኝ ድንግል አዘኝልኝ ቅድስት አዘኝልኝ
አማልደሽ ለስታርቂኝ ኪደነ ምሕረት "
አዘኝልኝ ቅድስት አዘኝል ቅድስት "
ለኔ ለደካማው ሀጢአት ሳጠቃኝ "
አዘኝልኝ.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
በምድራዊ ሕይወት
በምድራዊ ሕይወት (2) በፈተና ቦታ(2)
ማርያም ትጠብቀን አጇቿን ዘርግታ
ድንግል ትጠብቀን <u>አጇቿን ዘርግታ</u>(2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
የመላእክት እህት
የመላእክት እህት የሰማእታት እናት የፃድቃን
አመቤት(2)
ለምኝልን (2) ከልጅሽ ማርያም ምሕረት(2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
የሀዘን እናት
የሀዘን እናት የአንባሽ ባሕር
ወሰን የለው ሥፍር ቁጥር
ቅድስት የአንድ አምላክ መንበር
ዋ የኔ ጭንቅ የአንባሽ ባሕር
መጠን የለው ስፍር ቁጥር
ድንግል የአንድ አምላክ መንበር
ምን ይመስል ሀዘንሽ
ከመስቀሉ ያ ልጅሽ
ቁልቁል አንቺን ሲያይሽ
ሳልቅስ ሳልቅስ ከአንቺ ጋራ
ነፍሴ ሳለች ሳሳባራ
ስለ ጌታዬ ኢየሱስ መከራ
አበሳዬ ስዚያች ዕለት
አሳልፎ አንዳይሰጣት
ድንግል ነፍሴን ታደጊያት
የሀዘን እናት.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
እኔስ በምግባሬ
እኔስ በመግባሬ ደካማ ሆኛለሁ
አዘኝልኝ ድንግል አለምንሻለሁ(2)
ያንን የአሳት ባሕር አንዳላይ አደራ
ድረሽልኝ ድንግል <u>ስምሽን ስጠራ</u>(2)
እኔስ በምግራ.....
ፀምር ዘጌድዬን የሲያሱ ሐውልት
የሠሎሞን አክሊል <u>አፀ መድኃኒት</u>(2)
እኔስ በምግራ.....
የዳዊት መሰንቆ የኤልያስ መና
የናሆም መድኃኒት <u>ንዒ በደመና</u>(2
እኔስ በምግራ.....
የሰማዕታት እናት የሐዋርያት ግርማ
የመላእክት እህት <u>የደናግል ዜማ</u>(2
እኔስ በምግራ.....
አንቺ ነሽ ጉልበቴ በደከመኝ ጊዜ
የልቤ መጽናኛ <u>አረዳት ምርኩዜ</u>(2)
አፈሳስሁ አንባ በጣም ተጨንቄ
አማፀንሻለሁ በደሴን አውቄ(2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
አትለይን
አትለይን(2) ድንግል ሆይ ድረሽልን(2)
ከዲያብሎስ እጅ አንቺ አድኝን
ምሕረት ከልጅሽ ለምኝልን(2) እኽ
መሀሪ አምላክ ለሰው ልጅ ብለህ መከራን አየህ(2)
ለፈለጉህ(2) አንተ ብርሃን ነህ(2) እኽ
ከጠላት መከራ(2) ሰውረን ከኃጢአት(2)
መንገድህን(2) አንዳንሳሳት(2) እኽ
ጥቅስ፡ ኢሳ 59÷20-27 ራዕ 12÷13 ዮሐ2÷1-17

መዝሙር
ማርያም ሆይ ስለዚህ
ማርያም ሆይ ስለዚህ አናከብርሻለን(2)
ወልደሽዋልና የሕይወት እንጀራን
ወልደሽዋልና የሕይወት መጠጥን
አማላጅቱ ሆይ ለኛ ፀልይልን(2)
ፈተናና ስቃይ ችግር ስበዛብን(2)
ምልዕተ ውዳሴ የደስታ መፍለቂያ
የኪሩቤል አምሳል የሰይጣን ድል መንሻ
ምስራቅን ምዕራብን ሰሜንን ደቡብን
ሁሉን ተመልክቶ አብ መረጠሽ አንቺን
አንቺን የወደደ አንዱ አብ ቅዱስ ነው
ከአንቺም ሰው የሆነ ወልድም ቅዱስ ነው
ያፀናሽ መንፈስም አርሱ ቅዱስ ነው
በማንና በምን አንመስልሻለን
ምሳሌ አናገኝም ሳንቺ የሚሆን
አብብ ነው ድንቅ ነው የተዋህዶ ምስጢር
ይህን ያደረገ አምላካችን ይከበር
ማርያም ሆይ ስለዚህ.....
ጥቅስ: ቅዳሴ ማርያም

መዝሙር
ለኖህ ሐመሩ
ሠላም ለኪ(2) ለኖህ ሐመሩ
" ለአሮን በትሩ
" ለቅዱስ ዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ
" ለጌድዮን ፀምሩ
" ለሰሎሞን መንበረ ክብሩ
" ለፍሬ ስብሐት መፃሩ (2)
እመ አግዚአብሔር ፀባኦት ሰላም ለኪ (2)
ሠላም ለኪ ህብስተ መና ዘስራኤል
" የሰማዕታት ንጹህ አክሊል
" አፀ ጳጦስ ዘሲና
" የኤልያስ መና (2)
አንዘ ንሴፍሆ ለበረከትኪ ዘምስለ አምሐ አሰግድ ለኪ
ሠላም ለኪ ሰረገላሁ ለአሚናዳብ
" መና ያለብሽ ንፁህ መሶብ
" ያዕቆብ ያየሽ በሎዛ
" የደስሐቅ መአዛ (2)
አንዘ ንሴፍዎ ለበረከትኪ ዘምስለ አምሐ ንሰግድ ለኪ
ጥቅስ: ሰዓታት ?

መዝሙር
አምዬ ማርያም
አምዬ ማርያም ፈጥነሽ ድረሽልኝ አማልጂኝ
አስታርቂኝ(2)
አምዬ ማርያም በጣም አዝናለሁ አምዬ ማርያም
ሀጥአ በመሆኔ
ዳግም አለቅሳለሁ
አርኩስ በመሆኔ
ስለመላው ክፋት
አላለሁ ወይኔ
ያለኝ ፍፁም ተስፋ
አንቺ ነሽ ወገኔ
ምንም መልካም ሥራ
አይገባኝም አኔ
ከአዳም ዘር ሁሉ
ድካሜ ነኝ አኔ
ስለዚህ አደራሽን
አዘንልኝ ለአኔ
አምዬ ማርያም.....
አምዬ ማርያም አሮጥ አሮጥና አምዬ ማርያም
አወድቃለሁ ድንገት
አሄድ አሄድና
አሰራለሁ ስተት
ይሁንልኝ መሪ
ፍፁም አውነት
ይሁነኝ አለኝታ
የዓለም መድኃኒት
መመኪያዬም ይሁን
የቀራንዮ መስዋእት
ይሁነኝ መጠጊያዬ
የሰው ዘር ሕይወት
ማረፊያ ይሁነኝ
የፍጥረት ባለቤት
አምዬ ማርያም...
አምዬ ማርያም አትርሺኝ አናቴ አምዬ ማርያ
ሁኝኝ አረዳቴ
ደግፊኝ አመቤቴ
ማሪኝ በሕይወቴ
ፀጋዬ ነሽና
ከሕያው መድኃኒቴ
ታድለሽናልና
ከፍፁም ረድኤት
ውዳሴሽን ሁሉ
ይመገብ ሰውነቴ
ግሩም ምስጋናሽን
ይናገር አንደበቴ
አምዬ ማርያም ቅዳሴሽን በሙሉ አምዬ ማርያም
ይልበስ አካሳቴ
ደስታዬ ነሽና
አስከ አስተ ሞቴ
ተድላዬም ነሽና
በመላው ሕይወቴ
አምዬ ማርያም...
አምዬ ማርያም የበረሃው ውሃ አምዬ ማርያም
ይበልጣል ከወይን ጠጅ
አኔስ ናፍቄአለሁ
የፈጣሪን ደጅ
ፈጥነሽ ድረሽና
ሁኝኝ አማላጅ
አስከ መቼ ድረስ
ልቁም በሰው ደጅ
በጣም ናፍቄአለሁ
የአፍቃሪዬን ደጅ
በቶሎ ድረሽና
አስታርቂኝ አንጂ
አስከ መቼ ድረስ
ልኑር በጥላት ደጅ
አጅግ ናፍቄአለሁ
የመሐሪዬን ደጅ
ፈጥነሽ ድረሽና
አስታርቂኝ አንጂ

አስከ መቼ ድረስ
ልቁም በጨካኝ እጅ
እኔስ ናፍቄአለሁ
የአምላክን ደጅ
ፈጥነሽ ድረሽና
አስርቂኝ እንጂ
አስከ መቼ ድረስ
ልኑር በጣኦት ደጅ
በጣም ናፍቄአለሁ
የሕይወትን ደጅ
በቶሎ ድረሽና
አማልጅኝ እንጂ
አስከ መቼ ድረስ
ልኑር በኃጥአን ደጅ
እጅግ አናፍቃለሁ
የመድኃኒቴን ደጅ
ፈጥነሽ ድረሽና
አማልጅኝ እንጂ
አስከ መቼ ድረስ
ልሁን በደዌ ደጅ
እኔስ አናፍቃለሁ
የሰላምን ደጅ
በቶሎ ድረሽ
አሰታርቂኝ እንጂ
አስከ መቼ ድረስ
ልኑር በረብሻ ደጅ
ፈጥነሽ ድረሽና
አማልጅኝ እንጂ
ተፈጥረሻልና
ለኃጥአን አማላጅ
ይቀበለሻልና
ሕያው ወልደ አብ ያንቺ ልጅ
አምዬ ማርያም...

አምዬ ማርያም አኔስ አልፈልግም አምዬ ማርያም
ከሰው ጋር ቀጠሮ
የኃጢአቴ ብዛት
ከብዶኛል ዘንድሮ
በበደሌ ክብደት
ጨንቆኛል ዘንድሮ
በፍፁም አልፈቅድም
መዘር በቀጠሮ
አግሬን ሰብስቤ
ልኑር በተምሮ
በአንደዚህ ነውና
የሚገኝ አአይምሮ
ጥቅስ:

መዝሙር
አመቤታችን ማኅበራችንን
አመቤታችን ማርያም ማኅበራችን
(ሀገራችንን)ጠብቂልን በምልጃሽ (2)
ከመናፍቃን ከክህድያን ከጠላት ሰይጣን ሰውረሽ
አንድትጠብቂን በምልጃሽ (2)

መዝሙር
አይአቲ ዛቲ

አይአቲ ዛቲ አንተ ታስተርኢ አምርሁቅ ከመ ማቶት
ደብረ ገነት(2)
ሙሴ ኒርዕያ ሀገር ቅድስት አዝራኒ ተናገራ(3) ዘመራ
ዳዊት(2)
ትርጉም: ሙሴ ቅድስት ሀገር ሆኖ ያያት አዝራ
የተረከባት ያቺ አመቤት ናት::
ጥቅስ: ዘፀ 34÷1-8

መዝሙር
ደዌ ድስዋ
ደዌ ድስዋ መላእክት(2) ስማርያም(2)
በውስተ ውሳቴ መንጦላይት ዘይብልዋ በሀኪ ማርያም
ሀዳሴዎ ጣዕዋ(2)
ትርጉም : በመጋረጃ ውስጥ መላእክት ማርያምን
ያመሰግኗታል ሰላምታ ይገባሻል ማርያም
አዲሲቷ እንቦሳ ይሏታል::
ጥቅስ: ማቴ11÷27

መዝሙር
በምድራዊ ሕይወት
በምድራዊ ሕይወት(2)በፈተና ቦታ(2)
ማርያም ትጠብቀን አጆቿን ዘርግታ
ድንግል ትጠብቀን አጆቿን ዘርግታ(2)
ጥቅስ: መዝ44÷12

መዝሙር
አመቤቴ ማረያም አለምንሻለሁ
አመቤቴ ማርያም አለምንሻለሁ
በስቅሶ በዋይታ ፊትሽ ወድቄአለሁ
አመቤቴ ስሚኝ ተማጽኜሻለሁ(2)
ሀዘኔን ጭንቀቴን ለማን አነግራለሁ
ችግሬን ጉዳቴን ለማን አዋያለሁ
አመቤቴ ስሚኝ ተማጽኜሻለሁ
ሀዘኑ በዛብኝ ፈተናው ከበደኝ
አንደምን ልቻለው አኔስ ብቻዬን ነኝ
የአማኑኤል እናት ፈጥነሽ ድረሽልኝ
በጣም ተንገዳገድኩ ልወድቅ ነው እኔ
እመ አምላክ ጠብቂኝ ቁሚልኝ ከጐኔ
ምንም አጋር የለኝ ካንቺ በቀር ለኔ(2)
ጥቅስ: መዝ22÷5

መዝሙር
ነይ ነይ ድንግል ማርያም
ነይ(3) ድንግል ማርያም
አጽናኜና አማላጂ ተስፋዬም ሁኝ ለዘለዓለም
ኃጢአቴ በዝቶ የበደሌ ሸክም በጣም የከበደ
አጨሀለሁኝ ካንቺ ሥጋ ነስቶ ወደ ተዋሀደ
ነይ ነይ.....
አዳምን ለማዳን በጥንታዊ ፍቅሩ ስለተገደደ
መሀሪ ይቅር ባይ በቤተልሔም በረት ለኛ ተወለደ
ነይ ነይ.....
ከገነትና ከመንግሥተ ሰማይ ተሰደን እንዳንቀር ስለወደደ
ከቅድስት አገር ከአንቺ ጋር ተሰደደ
ነይ ነይ.....
አዳምን ለማዳን ንፁህ ማስዋእት እንዲሰዋ ስለወደደ

ቅዱስ የእግዚአብሔር በግ በገዛ ፈቃዱ በቀራንዮ
ላይ ለእኛ ሲል ታረደ
ነይ ነይ.....
ጥቅስ: ሉቃ2÷1-11 ማቴ2÷13

መዝሙር
ድንግል ሆይ ስላንቺ
ድንግል ሆይ ስላንቺ ነውና መሀሪ
አማልጅኝ ከአንድ ልጅሽ ከፈጣሪ
ስሙን እንዳልጠራ አንደበትም የለኝ
ፊቱንም እንዳላይ ስራዬ አሳፈረኝ
ድንግል ሆይ.....
ታውቆኛል ጥፋቴ ብዙ እንደበደልኩኝ
ትዕዛዙን እንደ ሻርኩ ሕጉን እንደጣስኩኝ
አንተ ክቡር መልአክ ልደቱን አብሳሪ
አማልደኝ ከጌታዬ ከፈጣሪ
ድንግል ሆይ.....
በፊቱ እንዳላፍር የተጠራሁ ለታ
አለምነዋለሁ ከአሁኑ ይቅርታ
ፃድቃን ሰማእታት እናንተ ሁሳችሁ
አማልዱኝ ከአምላኬ ከአምላካችሁ
ድንግል ሆይ.....
ጥቅስ: ዘፍ20÷8-18 ዘካ 7÷12-18

መዝሙር
የመለኮት እናት
የመለኮት እናት ቅድስተ ቅዱሳን(2)
ለኛ ለልጆችሽ ኃጢአት ሳጠለቀን(2)
አፍጣኒተ ረድኤት ማርያም እመቤት
የዘለዓለም ድንግል አፀደ ምሕረት (2)
ከልጅሽ አስታርቂን አሰጭን ስረይት(2)
ሲኦል እንዳንገባ ዳግም እንዳንሞት(2)
አፍጣኒተ.....
ጥቅስ: መዝ9 በሙሉ ዮሐ19÷25-27
ዕብ2÷14-18

መዝሙር
<u>የጠራሽ</u>
የጠራሽ አንቺን ተማፅነው የዳኑብሽ
የበላዩ ሰብ እመቤት የአምላክ እናት
ድንግል አዛኝቱ ማርያም ቅድስት/2/
በቃል ኪዳንሽ ብዙዎች ድነዋል
በምልጃሽም ፅድቅን አግኝተዋል
የአምላክ ቸርነቱን አይተዋል/2/
የጠራሽ_____
የአሳት ባሕርን ባንቺ ተሻግረዋል
የሠይጣንን ፃር በአንቺ ድል ነስተዋል
ለሠማያዊው ክብር በቅተዋል/2/
የጠራሽ_____
ነፍሳቸውም ፅድቅን አግኝታለች
ሕይወታቸውም ባንቺ ትድናለች
ድንግል ሆይ አትጣይን ስላለች/2/
የጠራሽ_____
እኔም ባአንቺ አታመናለሁ
የአምላክ እናት አሳስቢኝ አላለሁ
ባአማላጅነትሽ አድናለሁ/2/
የጠራሽ_____
እኛም ባንቺ አንታመናለን
የአምላክ እናት አሳስቢን አንላለን
ባአማላጅነትሽ አንድናለን/2/
የጠራሽ_____
ምዕመናንም ባንቺ ያምናሉ
የአምላክ እናት አሳስቢን ይላሉ
ባአማላጅነትሽ ይድናሉ/2/
የጠራሽ_____

መዝሙር
<u>ትህትናሽ ግሩም ነው</u>
ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም
እናቱ ሆነሻል ለመድኃኔዓለም
ንፅህያት ስለሆንሽ <u>አመቤቴ(2)</u>
አንከን የሌለብሽ "
የፍጥረታት ጌታ "
ባንቺ አደረብሽ "
የድንግል መመረጥ "
ዜናው አስገረመኝ "
አሳቱን ታቀፊች "
የማይታለውን "
ትህትናሽ_____
ምርኩዜ ልበልሽ <u>አመቤቴ(2)</u>
ጥላ ከለላዬ "
ጋሻዬ ነሽ አንቺ "
ለእኔ መመኪያዬ "
በዓለም አንዳልጠፋ "
ሕይወቴ መሆብኝ "
አንደ ወይን አጣፍጭው "
ድንግል ድረሽልኝ "
ትህትናሽ_____
የምስራቅ ደጃፍ ነሽ አመቤቴ
የሁሳችን ተስፋ "
እሙ ለፀሐይ ጽድቅ "
የሁሉ ጠበቃ "
ድንግል የድል አክሊል "
ድንግል የጽድቅ ሥራ "
ድንግል መሠላል ነሽ "
የተዋህዶ ተስፋ "
ትህትናሽ_____
<u>ጥቅስ</u>:

መዝሙር
<u>ውዳሴ ማርያም</u>
ውዳሴ ማርያም አጨሀለሁ
ድንግል እናቴን እጣራለሁ
እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ
ወድሰኒ ልጄ በይኝ
ውዳሴ ማርያም በሠርክ ፀሎት ላይ
" " ዜማ ስናደርስ
" " ድንግል ትመጣለች
" " ከቤተ መቅደስ
" " የብርሃን ምንጣፍ
" " ከፊቷ ተነጥፏል
" " ቅዱስ ኤፍሬም ታጥቆ
" " ያመሠግናታል

ውዳሴ ማርያም_____
ውዳሴ ማርያም አባ ሕርያቆስ
" " ምስጋናን ያቀርባል
" " የቅዳሴው ዜማ
" " ልብን ደመስጣል
" " በጐ ነገር ልቤ
" " አወጣ አያስ
" " ዳዊት በገናውን
" " እየደረደር
ውዳሴ ማርያም_____
ውዳሴ ማርያም የንፅህናችን
" " መሠረት ነሽና
" " አንቺን ለማመስገን
" " ልቡናዬ ይብራ
" " ተፈስሒ ድንግል
" " በቤተልሔም
" " ካንቺ ተወለደ
" " መድኃኔዓለም
ውዳሴ ማርያም_____
ውዳሴ ማርያም ቅዱሳኑ ሁሉ
" " ዙሪያሽን ከበዋል
" " አባ ጊዮርጊስም
" " ምስጋናን ያደርሳል
" " በወርቅ ዙፋን ሳይ
" " ተቀመጠሽ ሳይሽ
" " ልቤ ተሰወር
" " ድንግል በግርማሽ
ውዳሴ ማርያም_____
ጥቅስ፡

መዝሙር
ኪዳነ ምህረት
ኪዳነ ምህረት አመቤት
የዓለሙ ሁሉ መድኃኒት (2)
ቅድስተ ቅዱሳን ንፅሕት
አንቺ ነሽ ለአምላካችን እናት
ጌታችን መረጠሽ ልዩ አድርጎ
በማያስደንቅ ምስጢሩ ተዋሕዶ
ለልዑል ማደሪያነት የተመረጥሽ
ያለ ህማም ወለድሽው ድንግል ሆነሽ
እናትነት ድንግልና አስተባብረሽ ይዘሻልና (2)
እናትም ድንግልም አመብርሃን
ንፅሕይተ ንፁሐን እኛን አማልጅን (2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
አማናዊት እናት
አማናዊት እናት እነኋት ማርያም
ለቅዱስ ዮሐንስ ተሰጠች ለዓለም
ድኅነት የምታሰጥ የዘለዓለም ሕይወት (2)
የኛ ተስፋችን ኪዳነ ምሕረት (2)
ከሥጋዋ ስጋ ከነፍሷ ነፍስን
ተዋሐደ አምላክ እኛኑ ሊያድን
አልተለየችም በማዳኑ ሥራ እናታችን(2)
ፅዬን ማርያም መጠጊያ አለችን (2)
አማናዊት.....

ወልዳ ያሣደገች አዝላ የተሰደደች
የጌታችን እናት ድንግል ተንከራታለች
ከአፀ መስቀሉ ከዙፋኑ በቀኝ ቆማለች(2)
ትሳንት ዛሬም ነገ ማርልኝ አያለች(2)
አማናዊት.....

መዝሙር
አድኝኝ እናቴ
አድኝኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
ሥጋዊ ከኃጢአት ከቶ አራቀምና
ሸክሜ የከበደ ብችኛ ሆኛለሁ
አትለይኝ ድንግል አደራ አልሻለሁ(2)
የአማኑኤል እናት የተዋህዶ አክሊል
አትጥፊ ከመሀል አንድትሆኝኝ ኃይል
ምንም ቢበዛብሽ የኛ ጉስቁለና
ከኛ ጋራ ከሆንሽ አለን ቅድስና(2)
አድኝኝ.....
ተስፋዬ ነሽና እመካብሻለሁ
ግራ ቀኝም አልል ምርኮኛሽ ሆኛለሁ
ስቅበዘበዝ አይቶ ተስፋ የሰጠኝ
አግዚአብሔር ይመስገን ካንቺ ያሰጠጋኝ(2)
አድኝኝ.....
በሥጋ ደክሜ በነፍሴ አንዳልጠፋ
አማፀንሻለሁ ድንግል የኔ ተስፋ
የመንግሥቱ ወራሽ አንድሆን አድርጊኝ
መልካም ሥራን መስራት እኔን አስተምሪኝ
አድኝኝ.....
አንቺ የሌለሽበት ጉባኤው ባዶ ነው
በቁመ የደረቀ ሕይወት የተለየው
ከመሀከል ገብተሽ ሙይ የጐደለውን
ሠርጉ ተደግሷል ጎብኝልን ጓዳውን (2)
አድኝኝ.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ማርያም ፈደል
ማርያም ፈደል የሁሉ መማሪያ (2)
በንጽህና(2) ተጽፋለችና (2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
ስግደት ላንቺ ይሁን
ስግደት ላንቺ ይሁን (2) የአብ ሙሽራው
የሐዋርያት (2) ሞገሳቸው
የመነኮሳት የደናግልም መመኪያቸው (2)
ሠላም ላንቺ ይሁን (2) የወልድ ማደሪያው
የሰማዕታት (2) እናታቸው
የመላእክትም(2) አህታቸው (2)
ስብሐት ላንቺ ይሁን (2)
ጽርሐ መንፈስ ቅዱስ ማርያም ቅድስት
የእስጢፋኖስ (2) አክሊሉ
የጊዮርጊስም(2) ቀፀላ መንግስት2)
ውዳሴና ስብሐት (2) ድንግል ላንቺ ይሁን (2)

በሰማያት በአርያም አኮቴት
በኪሩቤል በሱራፌል ልሳን(2)
ዳግምም በምድር (2) የአዳም ልጅ ሁሉ
አናታችን ፅዮን (2) ማርያም
ብፅእት ነሽ ድንቅ ነሽ ግርምት ነሽ ክብርት
ነሽይበሉ
ጥቅስ፡

መዝሙር
ልቤን አነሳስቶ
ልቤን አነሳስቶ ያመለክተኛል የአምላክን አናት
አመናት ይሰኛል(2)
አመን አመን (2) የአምላክን አናት አዛኝቱን(2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
አንተ በምድር
አንተ በምድር ስረዊሀ ወበ ሠማይ አንፃኪያ (2)
ሐረገ ወይን (2) ድንግል ሐረገ ወይን (2)
ትርጉም፡
ጥቅስ፡

መዝሙር
በዝናመ ንሕጽኪ
በዝናመ ንጽሕኪ ሐረገ ወይን ፀገየ (2)
ወሮማን (5) አሳዘ ፈረየ (2)
ትርጉም፡ በንጽህናሽ ዝናም የወይን ሀረግ
አበበ
ጥቅስ፡

መዝሙር
እመቤታችን ማርያም ሆይ ተቀነዩ
እመቤታችን <u>ማርያም ሆይ</u> (2)
በመላኩ ገብርኤል ሠላምታ አንደተነገረሽ
ሰላም አንላስን አኛም ልጆችሽ (2)
በሀሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ
የልዑል አናቱ ደግሞም የአሸናፊ
ማኅበራንን <u>በአውነት ደግፊ</u>(2)
ከሴቶች ሁሉ <u>ተለይተሽ</u> (2) የተባረክሽ ነሽ
ቡሩክ ከሚባለው ከማህፀንሽ ፍሬ
ፀጋን አንድናገኝ <u>ለምኝልን ዛሬ</u> (2)
ለምኝ ጌታችንን <u>ይቅር አንዲለን</u>
(2)በደላችንን
ሲያወርድ የነበረው ለእስራኤል መና
ቸሩ ፈጣሪያችን <u>ከአንቺ ጋር ነውና</u> (2)
አሜን
ጥቅስ፡ ሉቃ 1÷26-36

መዝሙር
የድንግልን ነገር
የድንግልን ነገር የድንግልን ሥራ
ምን አፍ ይናገረው ምን አንደበት ያውራ
የአምላክ አናት ስትሆን ከፍጥረታት ከብራ
አምላክ ለሰው ልጆች ድኅነት የሰጠባት
ብዙ መከራና እጃግ የከፋ ሞት
ለድንግል ነበረ ፍፁም መራራ ሀሞት
የአዳም ተስፋው እመቤታችን
መከራ ስደትሽ ህይወት ይሁነን
አምላክሽ ሲወለድ በሔሮድስ ግዛት
አንቺም ደርሶሽ ነበር መከራ ስደት
በዳገት ቁልቁለት መራብ መጠማት
ቀን በፀሐይ ሀሩር ሌሊትም በቁር
ስታቆራርጭ ጫካውን ሳይቀር
ድንግል የዛን ጊዜ ሆድሽ ምን ይናገር
የአዳም ተስፋው.....

አንቺ ቀራንዮ ምድረ ጉልጐታ
የድንግልን ነገር አጫውችኝ ለአንዳፍታ
ምን ብላ አለቀሰች አንዱን ልጇን አጥታ
ይህ ሁሉ ሀዘንሽ ደስታ ተክቶ
አየሽው ልጅሽን በግርማ ተነስቶ
በኃይል በሥልጣኑ ሰይጣንን ድል ነስቶ
የአዳም ተስፋው.....
ሳንቺ ሳቅርብ አንጂ ክብርና ውዳሴ
ሳስሁ በሕይወቱ በሥጋ በነፍሰ
ተወልደሻልና በቅድሰት ስላሰ
ክርስቶስ በሠራው ለሰው ልጅ ውለታ
ድንግል አትታይም ከርሱ ተለይታ
በሞቱ በመከራው በስቃዩ ቦታ
የአዳም ተስፋው እመቤታችን
በጽድቅሽ ጽድቃችን ይታሰብልንን
የአዳም ተስፋው.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
አማላጅ ነው
በፍጡራንና ፈጣሪ መካከል
ድርሻ የተሰጠው ሰውን ለማገልገል
ተራዳኢው መልአክ ጠባቂ የእስራኤል
የመልአክት አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል
አማላጅ ነው ሚካኤል(2) የአምላክ ባለሟል
ለእነ ሙሴ ለሕዝበ እስራኤል (2)
ፈርኦን በእስራኤል ላይ በትእቢት ተነስቶ
ሲከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ
ይመራቸው ነበር ሚካኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና
አማላጅ ነው.....
ከባሕር ያወጣኸው ፀጋ ዘአብን
ከአረመኔው ንጉሥ አግዚሃረያን
ከልስህ የጠበቅህ በታላቅ ታምራት
አኖንም ጠብቀን ከበደል ከኃጢአት
አማላጅ ነው.....
በአፎምያ ላይ ሲፎክር ጠላት
ፈጥህ የደረስከው ሊቀ መልአክት
አኖንም ጠብቀን ከክፋ መቅሰፍት
ፈጥነህ ድረስልን ሁነን አረዳት
አማላጅ ነው.....
መልአኩ ሚካኤል አማላጆችን
አንለምንሃለን አንድትጠብቀን
አምላክ በፍርድ ቀን ጻድቃንን ሲጠራ
ዋስ ጠበቃ ሁነን ሚካኤል አደራ
አማላጅ ነው.....
ጥቅስ፡ ዘፀ 23÷20

መዝሙር
ሚካኤል ሊቅ
ሚካኤል ሊቅ ልብሱ ዘመብረቅ(2)
አይኑ ዘርግብ አይኑ(4) ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ(2)
ትርጉም፡ ሊቅ የሆነ ሚካኤል ልብሱ መብረቅ ነው አይኖቹ የእርግብ ዓይን ይመስላሉ። ሚካኤል የወርቅ ሐመልማል ነው።
ጥቅስ፡

መዝሙር
ሚካኤል ክብርከ
ሚካኤል ክብርከ እምክብረ መላእክተ ልዑል(2)
በብሂለ ኦ (2) አብፃነ ቃለ(2)
ትርጉም፡ ሚካኤል ክብርህ ከመላእክት ክብር ሁሉ በላይ ነው። እሺ በጄ በማለት አድሰን።
ጥቅስ፡ ት.ዳን12÷1-14

መዝሙር
ውእቱ ሚካኤል
ውእቱ ሚካኤል መላእክ ኃይል ልዑል ውእቱ(2)
ረዳኢ ይኩነነ (2)ሀበ ምንዳቤ(2)
ትርጉም፡
ጥቅስ ዳን10÷13

መዝሙር
ውእቱ ሊቆሙ
ውእቱ ሊቆሙ ለመላእክት ለመላእክት ሊቆሙ ስሙ ሚካኤል(2)
ልብሱ ዘመብረቅ ዓይኑ ዘርግብ ሊቀ መላእክት(2)
ትርጉም፡ ለመላእክት አለቃቸው እርሱ ነው ስሙ ሚካኤል ነው የሚካኤል ልብሱ የመብረቅ ልብስ ነው አይኑ የርግብ አይን ይመስላል
ጥቅስ፡ ይሁዳ 1÷8-13 ራዕ2÷1-10

መዝሙር
ሚካኤል ወገብርኤል
ሚካኤል ወገብርኤል ሱራፌል ወኪሩቤል(2)
ወይሴብህሃ(2)ለአምላክ ልዑል(5) ይሴብህሃ ለአምላክ ልዑል(2)
ትርጉም፡ ሚካኤል ገብርኤል ሱራፌል ኪሩቤል ገናና የሆነውን አምላክ ያመስግኑታል
ጥቅስ ኢሳ 6÷1-3 መዝ33/34/1-22

መዝሙር
አንተኑ ሚካኤል
አንተኑ ሚካኤል(2)
ዘአውረድከ መና(4) በገዳም ዘአውረድከ መና(2)
ትርጉም፡ በምድረ በዳ መና ያወረድክ አንተ ሚካኤል ነህ።
ጥቅስ፡ ዘፀ14÷19

መዝሙር
ልዑል ውእቱ
ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር(2)
ሚካኤል ልዑለ መንበር(2)
ትርጉም፡ ሚካኤል መቀመጫው ገናና ነው
ጥቅስ፡ ዳን12÷1-4 ይሁ1÷7አና 8

መዝሙር
ባህራንኒ
ባህራንኒ ይቤ ዘነገደ ባህር(2)
ርኢክዎ ለሚካኤል ወስዕንኩ ጠይቆቶ ዘይብል(2)
ትርጉም፡- ባህርን አቋርጦ የሄደው ባህራን አንዲህ አለ ሚካኤልን አይተቼ መረዳት ተሳነኝ አለ።

መዝሙር
ምስለ ሚካኤል ወገብርኤ
ምስለ ሚካኤል ወገብርኤል ንዒ ሠናይትየ ማርያም(2)
ንዒ ንዒ ንዒ(2) አመ አምላክ ንዒ ማርያም(2)
ትርጉም፡- የአምላክ እናት መልካሟ ርግብ እመቤታችን ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር ሆነሽ ወደ እኛ ነይ።
ጥቅስ፡- መኃ 4÷7-8
ሉቃ 1÷39-46

መዝሙር
ምስለ ሚካኤል መልዐክ
ምሰለ ሚካኤል መልዐክ ወገብረአል ንዒ(2)
ርግብየ ንዒ(3) ርግብ (2)ኽኽ

ትርጉም፦- ርግብ እመቤታችን ሆይ ከመልአኩ
ሚካኤል ከገብርኤል ጋራ ሆነሽ ወደ
አኛ ነይ
ጥቅስ፦- መኃ4÷6-8

መዝሙር
እልፍ አእላፋት
እልፍ አእላፋት ወትልፍት
ቅዱሳን ንፁሀን መላእክት
ቆመው ለአገልግሎት
ፀንተው በአንድነት
ቅዱስ (3) አመላክ በማለት
ኢዮር አራማ ሌረር የመላእክት ሀገር
የሃይማኖት የክብር የምልክት ሥር
እውነት የታየብሽ የመላእክት ክብር
እልፍ አእላፋት.....
አንጽና ሲል ገብርኤል ባለንበት ቦታ
በሳጥናኤል ነገድ ነበረ ሁካታ
ግማሹ እየከደ ቀሪው ሲያመነታ
እልፍ አእላፋት.....
የሳጥናኤል ምኞት አንደ አበባ አረገፎ
ሚካኤል ተሾመ በአምነት ተደግፎ
ሳጥናኤል ወደቀ ፀጋውን ተገፍ
እልፍ አእላፋት.....
ቅዱሳን መላእክት በአምነት የፀናችሁ
በታላቅ አክብሮት ሠላም አንበላችሁ
ስግደት ዘበፀጋ አንስገድላች
እልፍ አእላፋት.....
ጥቅስ: 2ቆሮ 12÷2 ራዕ12÷7 ኢያ5÷13

መዝሙር
አማልደን ስንልህ
አማልደን ስንልህ ስማን አዘንልን(2)
አጽናን አረጋጋን(2)
ገብርኤል የኛ መመኪያችን አባታችን
አግዚአብሔር አራሱ ክብርን አቀዳጀህ
በተልኮ አንድትፈጽም ያደረገና የሾመህ
አንደ ሦስቱ ሕፃናት አንተን አንደጠሩ
ዛሬም አውጣ ገብርኤል ሆይ ነፍሳችንን ከጠላት
አማልደን ስንልህ.....
አምነት አለን አያልን ንቀናል ምግባርን
አባክህ ሊቀ መላእክ አንድናስብ አርዳን
መላእክቱን ሁሉ ያረጋጋሀቸው
አንተ አኮ ነህ ኃያል መላእክ
ጽኑ ቁሙ ያልካቸው
አማልደን ስንልህ.....
አኛስ አናምናለን በአማላጅነትህ
በተሰጠህ የአምላክ ፀጋ ኃይላችን አንተ ነህ
የምስራች መላእክ ተብለሃልና
ደስ አሰኝን ደስታን ስጠን ተጨንቀናልና
አማልደን ስንልህ.....
ኢትዮጵያንም ታደግ ተዋህዶንም ጠብቅ
ሊቀ መላእክ በል ቁምልን ሰይፍህንም ታጠቅ
ሠራዊትህ ከበው አነሱ ያጽናኑን
ዘወትርም ሳትርቀን ሠላምን ስግሰን
አማልደን ስንልህ.....

ጥቅስ: ሉቃ 13÷6-9

መዝሙር
ንዓ ንዓ ገብርኤል
ንዓ ንዓ ገብርኤል መልአከ ራማ ዘውገ ማርያም አሃቲ
ድንግል(2)
ዘዳግመ በሉ አሰይ ዘዳግመ ጽጌ ደበል ሀምሳስ ኪያሁ
ዘይመስል አልቦ ካህን ጥዑመ ልሳን(2)
ትርጉም:
ጥቅስ ሉቃ1÷3

መዝሙር
እም አቶነ አሳት
እም አቶን አሳት(2)ዘይንድድ
አንግፈኒ በስፈሀ ሊቀ መላዕክት አኽ
ታላቅ መመኪያ ነህ ስሚያምኑብህ ሁሉ
ናዛዜ ህዙናን(2) ገብርኤል ስልዑስ መላእክ ኃይሉ
የነበልባሉ ኃይሉ ሞገሱ ሲበዛ
ስሠስቱ ደቂቅ የሆነችው ቤዛ
ታላቅ መመኪያ .....
ፈጥነህ የምትደርሰ በዕስተ ሠርቅ
ሰቡህኒ አንተ ወልዑስ ፅድቅ
ታላቅ መመኪያ .....
ዜናው የፍስሀ የሰው ልጅ ሕይወት
መላክ ሠላምነ ሊቀ መላዕክት
ታላቅ መመኪያ .....
ባማለጅነትህ አንኮራስን
ምስለ ንጉሰነ ፃድቀ ፅዮን
ታላቅ መመኪያ .....
ጥቅስ ዳን 3÷8-30

መዝሙር
አንደ አናንያ
አንደ አናንያ አንደ አዛርያ አንደ ሚሳኤል አፃናን አኛን(2)
አፃናን አኛን(2) አፅናን አኛንም በአምነታችን(2)
ጌታ በመስቀል(2) ጌታ በመስቀል ሳይ ሰቀሉህ ወይ(2)
ለሰው ስትል ታስሮ መገርፍ ሁሉንም የቻልክው
አማኑኤል(2)
ጥቅስ: ዳን 3÷1-30 ዮሐ 20÷17-18

መዝሙር
ገብርኤል ምልአኒ
ገብርኤል ምልዐኒ መንፈስ ልዛን ስተናብቦ መንፈሰ ልዛን
ሞጣህተ ብርሃን(2) ዘይትገስብቦ ሞጣህተ ብረሃን(2)
ትርጉም፤ የብረሃን መጎናፀፊያ የምትስብስ ገብርኤል
መንፈሳዊ ነገር የሚያናግር መንፈሳዊ
አንድነትን ስጠን::
ጥቅስ፦- ሉቃ 1÷26

መዝሙር
ገብርኤል አወፈኒ
ገብርኤል አወፈኒ ህፃነ ማርያም ድንግል(2)
ወበ ቤተልሔም(2) ተወልደ(2)አማኑኤል(2)
ትርጉም፤-አመቤታችን ድንግል ማርያምን ገብርኤል
ነገራት (አበሠራት) በቤተልሔም አማኑኤል
ተወለደ::
ጥቅስ፦- ሉቃ 1÷26-33 1ኛ ዮሐ 4÷9-21

መዝሙር
ገብኤል መላከ
ገብረኤል መልአከ መፅአ ወዜነዋ(4)
ለማርያም(2)
በዕንቁ ባሕርይ(2) እንዘ ትፈትል ወርቅ(2)
ትርጉም፡-መላከኩ ገብርኤል መጥቶ ለእመቤችን
ለማርያም ወርቀና ሐር እያስማማች
ስትፈትል ሳለች አስረድቶ ነገራት።
ጥቀስ፡-ሉቃ 1÷26

መዝሙር
የራማው ልዑል
የራማው ልዑል ገብረኤል(2)
ተመላለስ መሀላችን ስምህን ጠርተን ና ስንል(2)
ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ገብርኤል አባታችን
አንተ አኮ ነህ መመኪያችን
የራማው ልዑል.....
የምሥራች ነጋሪ ድንቅ ልደትን አብሣሪ
የፅድቅ ፋና የሕይወት ጎዳና(2)
የራማው ልዑል.....
ለአናንያ ለዛርያ ለሚሣኤል መመኪያቸው
ከእሣት ነበልባል ያዳንካቸው(2)
የራማው ልዑል.....
ምሶሶ አምዳችን መጠጊያችን
ቅዱስ ገብርኤል ጠባቂያችን(2)
የራማው ልዑል.....
ላመኑብህ ስተማፀንህ
ፈጥኖ ደራሽ አለኝታቸው ነህ(2)
የራማው ልዑል.....
ዕለት ዕለት የምንማልድህን
ልጆቸህን ይምራን መንፈስህ(2)
የራማው ልዑል.....
ብርሃን ለብሰህ እሣታዊው መላእክ
አንተ አማልደን ከመሀሪው አምላክ(2)
የራማው ልዑል.....

ጥቀስ ሉቃ 1÷26

መዝሙር
ገብርኤል ነው አሉ
ገብርኤል ነው አሉ አስደሳች መልአክ(2)
ትርጓሜውም ሰውና አምላክ(2)
ቂርቆስ ከእናቱ ጋር በእሳት ሲጣሉ(2)
ውኃ ሆነ ጠፋ ነበልባሉ ውኃ ሆነ በገብርኤል
ኃያሉ
ጥቀስ፡- ሉቃ 1÷31

መዝሙር
ተልኮ መጥቶ
ተልኮ መጥቶ ገብርኤል(2)
እንዲህ ብሎ አላት ለድንግል(2)
ሠላም ለኪ ማርያም (2)
ፀጋን የተመላሽ በፍፁም(2)
የማሕፀንሽ ፍሬ ኢየሱስ(2)
የተባረከ ነው ቅዱስ(2)
ጥቀስ፡ ሉቃ1÷18-26

መዝሙር
መልአክ በሰላም
መልዐክ በሠላም ተናገራ መልአክ በሠላም(2)
ቡርክት አንቲ እም አንስት ቡርክት አንቲ(2)
መላክ በሠላም ድንግልን መልአክ ተናገራት(2)
ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ ቡርክት ነሽ አላት(2)
ጥቀስ፡ ሉቃ1÷28

መዝሙር
ማርያም ደስ ይበልሽ
ማርያም (3) ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሠላምታ
ባንቺ ስላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ
የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጣ ብርሃን
ማርያም.....
መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን አንዳፈረ
የዘናው አብሳሪ ገብርኤል ነበረ
ማርያም.....
ገብርኤል(2) ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ሥጋን በመልበስ
ማርያም.....
ድንግል ተቀምጣ በቤተመቅደስ
ሐር ወርቁን ለስማምታ ስትፈትል ንግሥት
ማርያም.....
ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ
ማርያም.....
እውነተኛ መላእክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀሰለች
ማርያም.....
ጥቀስ፡ ሉቃ1÷26-38

መዝሙር
አስተራየ ገብርኤል ግብተ
አስተራየ ገብርኤል ግብተ
ወአንዘ ትፈል(4) ወርቀ ወሜሳተ
አስተራየ(2) ገብርኤል ግብተ
ቤተመቅደስ ስትኖር ገብርኤል ግብተ
አስራ ሁለት ዓመት "
ወደ እርሷ ተላከ "
መልአከ ብሥራት "
አስተራየ.....
ዳዊት በበገና ገብርኤል ግብተ
እያጫወታት "
እዝራ በመሰንቆ "
እያጫወታት "
ሳታውቀው አለፈ "
ያን መልአከ ሞት "
አስተራየ.....
ዳዊት እደግማለሁ ገብርኤል ግብተ
ይሔይስ ተአምኖ "
ባልጀራ ሲሞት "
ይሔዷል መንኖ "
አስተራየ.....
ዳዊት እደግማለሁ ገብርኤል ግብተ
"

አንባቆም ላይ ስደርስ "
አንቢ አለው ዓይኔን "
አስተራዩ.....
ጥቅስ፡ ሉቃ 1÷28

መዝሙር
ስሙ ገብርኤል
ስሙ ገብርኤል የተባለ
ለድንግል ነገራት መልካም ዜና
እንደምትወልደው ወልድን በድንግልና (2)
ባሰማት ጊዜ ቃሉን ቅዱስ ገብርኤል በለዛ
ድንግል ቀረበች ወደ እርሱ ፍፁም ትናተናን ይዛ
ትፀንሻለሽ ሲላት መላኩ
ፍፁም በልቧ ሳትመካ
እንደ ቃልህ ይሁን አለችው በቃሉ ተማርካ(2)
ባሰማት ጊዜ.....
የዓለም መድኃኒት ነውና
ካንቺ የሚወለደው በመንፈስ ቅዱስ
ትሰይሚዋለሽ ስሙን ብለሽ ኢየሱስ(2)
ባሰማት ጊዜ.....
እፁብ ድንቅ ነው ሁል ጊዜ
ለድንግል ማርያም የተሰጣት አድል
የአምላክ እናት ሆና መመረጥ ከሴቶች
መካከል(2)
ባሰማት ጊዜ.....
ፀጋን የተመላሽ ድንግል ሆይ
ደገባሻል ለአንቺ ክብርና ምስጋና
የክብር ባለቤት ምንጊዜም ከአንቺ ጋር
ባሰማት ጊዜ.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ክንፎ ፀለላ
ክንፎ ፀለላ(3) ኧኸ
ተፈስሒ ለድንግል ይቤላ(2)
ትርጉም፡- በአቅፋ ጋርዶ ድንግል ሆይ ደስ
ይበልሽ አላት::
ጥቅስ፡- ሉቃ 1÷28

መዝሙር
ዑራኤል መልዐክ
ዑራኤል መልአክ(2)ለአዝራ ነቢይ(2)
ዘአስተዩ(2) ጽዉዓ ልቦና(2)
ትርጉም፡ መልአኩ ኡራኤል ለአዝራ አውቀት
የሚገልጽ ጽዋ አጠጣው::
ጥቅስ፡ ሐዋ8÷26-40 ሐዋ10÷1-8
ራዕ 10÷8-11

መዝሙር
ኡራኤል ለሔኖክ
ኡራኤል ለሔኖክ ዘአራዩ ትዕምርተ አምላልኪ
ቤተነድ(2)
ዘመብረቅ ጠፈረ ወሕብረ በረድ ለደብረ ጽጌ(2)
ትርጉም፡ የደብረ ጽጌ ጠፈሯ የመብረቅ ሕብር
የበረድ የአሣት ነበልባል የሚሆን
የምላሴ ምልክት ኡራኤል ለሔኖክ
ያሣየው ነው::

ጥቅስ፡ ዳን 7÷9-14

መዝሙር
ኡራኤል ወሩፋኤል
ዑራኤል ወሩፋኤል(4)
አስተምሩ ለነ በስኢል ወበ ትህትና
ሀበ ውእቱ ነበልባል(2)
ትርጉም- ዑራኤል ሩፋኤል ሆይ በትህትና በፀሎት ወደ
እግዚአብሔር ለምኑልን::
ጥቅስ፤-ዘካ 1÷12-13 ሉቃ 13÷6-9

መዝሙር
ቀዋምያን ለነፍሣት
ቀዋምያን ለነፍሣት(2) እሙንቱ ሊቃናት ዑራኤል
ወሩፋኤል(2)
ይተፈነዋ ለሣህል(2) እም ሀበ ልዑል(2) እግዚአብሔር(2)
ትርጉም፡ ለፍጥረት/ለነፍሳት/ የቆሙ የመላእክት አለቆች
ዑራኤልና ሩፋኤል ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ
ለረድኤት ይላካሉ::
ጥቅስ፡

መዝሙር
ሰፊሁ ክነፊሁ
ሰፊሁ ክነፊሁ(2)
ክነፊሁ ይዒለል ዲቤነ(2)
ትርጉም፡ ክንፋን ዘርግቶ ወደ እኛ ይላክ::
ጥቅስ፡ ማቴ 18÷10-14

መዝሙር
ያከብርዋ ለሰንበት
ያከብርዋ ለሰንበት መላእክት በሠማያት ፃድቃን በውስተ
ገነት(2)
ወኮሉ ፍጥረት አሳት ወአናብርት አለ ውስተ ደደን
ያረፋ ባቲ እስመ ባቲ አእረፈ እምኩሉ ግብሩ(2)
ያከብሯታል ሰንበትን መላእክት በሰማያት ፃድቃንም
በገነት(2)
ፍጥረታት በሙሉ አሳዎች እና አንበሪዎች በመቃብር ያሉ
ያከብሯታል አምላክ በእርሷ እንዳረፈ ከሥራው ሁሉ(2)

መዝሙር
ግሩማን መላዕክት
ግሩማን መላዕክት(2) ዑራኤል ወሩፋኤል እለ አክነፊሆሙ
ነበልባል(2)
ወረዱ ዮም ይትቀበሉከ በብሂል አማን ገብረ መንፈስ
ቅዱስ ገባሬ ኃይል(2)
ትርጉም፤ የግሩማን መለአክት ዑራኤል ሩፋኤል መንፈሳዊ
ኃይል የምታደርግ ገብረ መንፈስ ቅዱስ
ክንፎቻቸው የነበልባል የሆኑ ዑራኤልና ሩፋኤል
ይቀበሉህ ዘንድ ወረዱ::
ጥቅስ፤ ራዕ 8÷1-13

መዝሙር
መላእክትኒ
መላእክትኒ ተጋብኦሙ ሰፊሁ ክነፊሆሙ (2)
ላእለ ማርያም ወፀለሉ ላእለ ማርያም (4)
ትርጉም፡ መላእክት ክንፋቸውን ዘርግተው የእመቤታችንን
አራስ ጋረዱት::
ጥቅስ፡

መዝሙር
ኮከብ ብሩህ
ኮከብ ብሩህ ቅዱስ ማርቆስ ዘሠረቀ
አምአስክንድርያ ቤተክርስቲያን ዘንሰመያ(2)
ኩኖሙ አበ ስሰበአ ግብጽ ወኢትዮጵያ በከመ
ጳውሎስ ሐዋርያ(2)
ትርጉም፡ ቤተክርስቲያን ብለን ከምንጠራት
ከአስክንድርያ የመጣ የሚያበራ ኮከብ
ቅድስ ማርቆስ አንደ ቅዱስ ጳውሎስ
ለኢትዮጵያና ለግብጽ አባት ሆናቸው።።
ጥቅስ፡ ሉቃ11÷36

መዝሙር
ማርቆስ አስተማረ
ማርቆስ አስተማረ ቃለ ክርስቶስ(2)
ፈጽሞ ሳይፈራ ነገሥታተ ምድር(2)
ጥቅስ፡ 1ጴጥ 5÷13

መዝሙር
ማርቆስ ሐዋርያ
ማርቆስ ሐዋርያ ወንጌላዊው ሠማዕት(2)
ሰበከ በግብፅ በመላዋ ግብፅ
ሰበከ በአስክንድርያ በመላው ግብፅ(2)
ትርጉም፡ ሐዋርያው ማርቆስ በአስክንድርያና
በመላዋ ግብጽ ሰበከ።።
ጥቅስ፤- ገድስ ማርቆስ

መዝሙር
ማርቆስ ተሠጠወኒ
ማርቆስ ተሠጠወኒ ተሠጠወኒ አምራማ(2)
ወተናገረኒ ማርቆስ በጥዑመ ዜማ(2)
ትርጉም፤- ማርቆስ ከራማ መስሠልኝ
በአማረ ቅኝትህ ማርቆስ ተናገረኝ
ጥቅስ፤- ገድስ ማርቆስ

መዝሙር
በበግማድ
በበግማድ ሥጋሁ መተሮ(2)
ቅዱስ(3)ጊዮርጊስ ምኦሙ ስፀሮ(2)
ትርጉም፡ በጥቂት በጥቂቱ ሥጋውን ቆረጡ።።
ቅዱስ ጊዮርጊስ ጠላቶቹን አሸነፈ።።
ጥቅስ፡

መዝሙር
ከመፀበል ዘነፋስ
ከመፀበል ዘነፋስ ወዘርውዎ በደብረ ደድራስ(2)
ወዘርውዎ(6)ስጊዮርጊስ(2)
ትርጉም፡ ትቢያ በነፋስ እንደሚበን የጊዮርጊስን
ሰውነት ፈጭተው ይድራስ በተባለው
ተራራ ላይ በተኑት አቦነኑት።።
ጥቅስ፡ ገድስ ጊዮርጊስ

መዝሙር
ጊዮርጊስ በዚያች ቀን
ጊዮርጊስ በዚያች ቀን ከፈተናው እንባር
ስለሃይማኖቱ የታየው ምን ነበር
ያመነውን አምላክ አላውቀውም እንዲል
በሥልጣን በገንዘብ አርሱን በመሸንገል
ነገር ሲሰሩበት የዳክዮስ ጭፍሮች
ስመሥዋዕት ሲቀርብ መንፈሱ ምን አለች
ጊዮርስ በዚያች ቀን.....
ስገድ ባሉት ጊዜ ሰው ስሰራው ምስል
ትዝ አለው ጊዮርጊስ የአምላኩ ሕያው ቃል
ከሠለስቱ ደቂቅ ከዳንኤል ጋራ
በእሳት ነበልባል ውስጥ ተአዓምር ሲሰራ
ጊዮርጊስ በዚያች ቀን.....
ቂርቆስ አየሱጣን ከመቃጠል ዋጅቶ
ያቀዘቀዘውን ፍሱን ውኃ አጥፍቶ
አስታውሷል ጊዮርጊስ ያንን ኃያል ጌታ
መስቀል መሸከሙን በዚያ በጎልጎታ
ጊዮርጊስ በዚያች ቀን.....
ጴጥሮስና ጳውሎስ አባቶቹን መስሎ
ሞትን አሸነፈ በአምነቱ ተጋድሎ
አንድንጸና በአምነት ይችን ዓለም ንቀን
በሰማእቱ ምልጃ አምላክ ይጠብቀን
ጊዮርጊስ በዚያች ቀን.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ደም ወማይ
ደም ወማይ ወሐሊብ እምነ ክሣደ ፈልፈለ(2)
ሶበ ተከለለ(3)ቅዱስ ጊዮርጊስ(2)
ትርጉም፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ አንገቱን በተሠየፈ ጊዜ
ወተትና ውኃ ደምም ከአንገቱ ፈሠሠ(መነጨ)
ጥቅስ፡

መዝሙር
ጋሻውን ይዞ በፈረስ
ጋሻውን ይዞ በፈረስ አቤት ማማሩ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ብሩታይትን ያዳናት ዘንዶ አንዳይበላት ደራጐን(2)
በወጣትነቱ ጽድቅን ለይቶ አውቆ
ስዘመቻ ወጣ ጋሻ ጦሩን ታጥቆ
ጋሻውን.....
በሕፃንነቱ በአምላኩ ተጠርቶ
ድል ነሳው ጠላቱን ጥበብን ተሞልቶ
ጋሻውን.....
ኃያሉ ጊዮርጊስ የጽድቅ ወታደር
በተጋድሎው ጸና በአምላኩ ሳያፍር
ጋሻውን.....
ሞትን ሞተ ስሥጋው ሳይሰሳ
ስለአምላኩ ክብር ተቀበለ አቦሳ
የልዳው ንጉሥ ቅዱሱ አንበሣ
ጋሻውን.....
ጥቅስ፡ ገድስ ጊዮርጊስ

መዝሙር
ኦ ፍጡነ ረድኤት
ኦ ፍጡነ ረድኤት(2)
የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅዱስ ሰማእት
ሠላም ላንተ ይሁን ፍጡነ ረድኤት
የልዳው ፀሐይ "

በጨካኝ ንጉስ ፊት ቆምክ አደባባይ
ታማኝ አገልጋይ ነህ ፍጡነ ረድኤት
ስቃይ ያልበገረህ "
አክሊልን አገኘህ መከራን ታግሰህ
ኦ ፍጡነ ረድኤት.....
የፈጣሪውን ስም ፍጡነ ረድኤት
ስለመሰከረ "
ጊዮርጊስ ሰማእት በሰይፍ ተመተረ
የስቃይ መሣሪያ ፍጡነ ረድኤት
ያሳዘናጋህ "
መንፈሳዊ አርበኛ ጊዮርጊስ አንተ ነህ
ኦ ፍጡነ ረድኤት.....
ስጌታ ተጋዳይ ፍጡነ ረድኤት
ታማኝ ወታደር "
ቢነገር አያልቅም የተሰጠህ ክብር
ስቃይ ቢያደርሱብህ ፍጡነ ረድኤት
በመታገስህ "
ሲወሳ ይኖራል ዘለዓለም ክብርህ
ኦ ፍጡነ ረድኤት.....
ስሰማው ይደንቃል ፍጡነ ረድኤት
ያንተ ሰማእትነት "
ምሳሌ ይሆናል ስሁሉ ፍጥረት
ገድልህ ይናገራል ፍጡነ ረድኤት
ክብር አንደተሰጠህ "
ጊዜ የማይሽረው ምግባር ሃይማኖት
ኦ ፍጡነ ረድኤት.....
ጥቅስ፡ ገድለ ጊዮርጊስ

መዝሙር
አንደ ኮከብ
አንደ ኮከብ (2) ብሩህ
አንደ አጣንም ንፁህ
አልሰግድም ቢል ለጣኦት
በፈላ ውኃ ቀቀሉ
የጋለ ብረት ጫማ ሰፋለት
ንጉስ ዲዳያኖስ ፈረደበት (2)
አንደ ኮከብ.....
ተፈተነ በአሳት ተዘጋጀ ለስለት
ተቆራረጠ ለክብቶች ተሰጠ(2)
አንደ ኮከብ.....
የዘንዶ አራት የግፍ መስዋዕት
ተዘገጅታ ብሩታይት
ደርሶ በአምነት ቤዛ ሆናት (2)
አንደ ኮከብ.....
ሰባት ጊዘ አንደሞተ
ሰባት አክሊል ተበረከተ
አንደሞተ አንደተነሳ
በሰማዕትነት ጠላት ድል ነሣ(2)
አንደ ኮከብ.....
ጥቅስ፡ ገድለ ጊዮርጊስ

መዝሙር
ሶበ ተከለለ
ሶበ ተከለለ(6)
ጊዮርጊስ(2) ሶበ ተከለለ ኸኸ(2)
ጥቅስ፤-ገድለ ጊዮርጊስ

መዝሙር
ጊዮርጊስ ኃይል
ጊዮርጊስ ኃያል(2) መስተጋድል(2)
ገባሬ ተዓምር(2) መስተጋድል(2)
ትርጉም፤- ጊዮርጊስ አርበኛው ኃይለኛ
ተጋዳይ ነው አስደናቂ ተአምረን ያደርጋል።
ጥቅስ፤- ሰዓታት

መዝሙር
አማን በአማነ ፀሐየ ልዳ
አማን በአማን(2)
ፀሐየ ልዳ ኮከበ ፋርስ(2)እኸ
ትርጉም፤- እውነት ነው የልዳ ፀሐይ የፋርስ ኮከብ ነህ።
ጥቅስ፤-

መዝሙር
በብዙ አሕጉር
በብዙ አህጉር የዞርክ የጌታን ወንጌል ያስተማርክ(2)
የዲቁናን ሥርዓት በክብር የፈፀምክ <u>ብፁ ነህ</u> (2)
አስጢፋኖስ ብፁ ነህ(2)
ጥቅስ፡ ዮሐ6÷3-7

መዝሙር
ቅዱስ እስጢፋኖስ
ቅዱስ እስጢፋኖስ ቀዳሚ ሰማእት
ተመረጥክ በዛሬዋ ዕለት
ቅዱስ እስጢፋኖስ አምደ ሃይማኖት
ተመረጥክ በዛሬዋ ዕለት
ቅዱስ እስጢፋኖስ ቀዳሚ ሰማእት
ተመረጥክ በዛሬዋ ዕለት
ጥቅስ፡ የሐ6÷8-15

መዝሙር
አስጢፋኖስ ሰማዕት
አስጢፋኖስ ሰማዕት ሊዋ ዲያቆናት በሐዋርያት
የተሾምክ(2)
የአምላክህን ትዕዛዝ በሥራ የፈፀምክ(2)
ጥቅስ፡ የሐዋ6÷8-15

መዝሙር
ጊዜው አረፍቱ
ጊዜው አረፍቱ ለአስጢፋኖስ(2)
በልአልና ወረደ አግዚአብሔር(2)
ትርጉም፡

ጥቅስ፡ የሐዋ 6÷1

መዝሙር
ተክለሃይማኖተ ተወለዱ
ተክለሃይማኖት ተወለዱ አሠይ(2)
የዓለም ብርሃን(2) የፅድቅ ፀሐይ(2)
ባለሟሉ የአምላክ አገልጋይ(2)
ጥቅስ፤-

መዝሙር
አባ አቡነ
አባ አቡነ(2) መምሕርነ አባ ተክለ ሃይማኖት(2)
አም አዕላፍ ሕሩይ(2) አባ(4) አቡነ
ተክለሃይማኖት(2)
ትርጉም፦-አባታችን መምህራችን ተክለሃይማኖት
ከብዙዎች የተመረጥክ ነህ።
ጥቅስ፦-ገድለ ተክለሃይማኖት

መዝሙር
አበ ኩልነ
አበ ኩልነ(2) ተክለሃይማኖት(2)
አስተጋብአነ(5) ለስብሐተ አግዚአብሔር(2)
ትርጉም፡ የሁላችን አባት ተክለሃይማኖት
ለእግዚአብሔር ምስጋና ሰበሰበ
(አዘጋጀ)
ጥቅስ፡ ገድለ ተክለሃይማኖት

መዝሙር
ትዌድሶ ደብረሲባኖስ
ትዌድሶ (3)
ለተክለሃይማኖት ደብረ ሲባኖስ(2)
ትርጉም፡

ጥቅስ፡

መዝሙር
ተክለሃይማኖት ተክለ አብ
ተክለሃይማኖት ተክለ አብ ተክለ ወልድ ተክለ
መንፈስቅዱስ(2)
አባታችን አማልደን አስታርቀን ከፈጣሪ ጋር
ከአምላካችን
በሦስት ቀን ስላሴን ያመሰገንክ
ከጭንጫ ድንጋይ ውሃን ያፈለቅክ
አባታችን ተክለሃይማኖት
አማልደን በሀጢአት እንዳንሞት
ተክለ ሃይማኖት.....
እንደ መላእክት ክንፍ የተሰጠህ
ሠማእት ነቢይ አንድም ካህን ነህ
መምህራችን አዲስ ሐዋርያ
አስተምረን የፍቅር ባለሙያ
ተክለ ሃይማኖት.....
እንደ ሱራፌል በሰማይ ሲያጥን
በምድር ላይ ረድአ ሆኖ ማገልገሉን
በተሰጠው ሥልጣን ሲያስነሳ ሙታን
ክህነቱ ካንተው ዘንድ ናት
አባታችን ፈታን ከሀጢአት
ተክለ ሃይማኖት.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ተክለሃይማኖት የአምላክ ባለሟል
ተክለሃይማኖት የአምላክ ባለሟል ፍፁም
ናቸው(2)
ይኸው ለዘለዓለም ያበራል ሥራቸው ያበራል ይኸው(2)
ጥቅስ፡ ማቴ5÷14-16

መዝሙር
ሐዋርያው መነኩሴ
ሐዋርያው መነኩሴ የመረጠህ ሥላሴ
ዋስ ጠበቃ ሁናት ፃድቁ ለነፍሴ
ዳሞት ትናገረው የአንተን ሐዋርያነት
የወንጌል ገበረ የጣኦታት ጠላት
ፀሎተኛው ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት
ክንፍን የተሸለምክ እንደ ሰማይ መላክ(2)
ሐዋርያው መነኩሴ.....
ብራናው ሲገለጥ ገድለ ተክለሃይማኖት
ከሰው ልጅ ልብና ደወጣል አጋንንት
የቅደሴው አጣን ሲወጣ ከዋሻው
ምድርን ይባርካል ፀሎተ ምሕላው(2)
ሐዋርያው መነኩሴ.....
የኢትዮጵያን ምድር አረስከው በመስቀል
ጭንጫው ፈራረሰ ተዘራበት ወንጌል
ትናንት የዘራህው ዛሬም ለእኛ ሆኗል
አምላክ ተክልዬ ብለን ተምረናል (2)
ሐዋርያው መነኩሴ.....
ከሱራፌል ተርታ ቆመህ ስታጥን
ቅዱስ አምላክ ብለህ ስታመሰግን
ፀሎት ቱሩፋትህ ትህትና ስግደትህ
ፃምህ ከፍ አድርጎ ሠማይ አደረሰህ(2)
ሐዋርያው መነኩሴ.....
ዛፋ ሲመነገል አምላክ የተባለው
ሞቶሎሚ አፍሮ ታላቅ ሰው ነኝ እያለ
የተክልዬ ፀሎት ብዙ ነው ምስጢሩ
ስድስት ክንፍ አወጣ ቢቆረጥ አንድ እግሩ(2)
ሐዋርያው መነኩሴ.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ኮኮብ ብሩህ
ኮኮብ ብሩህ ተክለሃይማኖት ዘስረቀ አም
ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ዘንሰመያ(2)
ኰሎሙ አበ ስሰብአ ዓለም ወኢትዮጵያ
በከመ ማርቆስ ሐዋርያ(2)
ትርጉም፦-ከኢትዮጵያ የወጣ ተክለሃይማኖት
አንደ አጥቢያ ኮከብ የበራ ነው
ቤተክርስቲያንም የምንጠራት ስዓለምም
ለኢትዮጵያ ሰዎችም አባት ሆኖአቸዋልና አንደ
ሐዋርያው ማርቆስ አናት ሆኖቸዋል።

መዝሙር
ሀበ ተሰበረ
ሀበ ተሰብረ አግረከ ወሀበ ተከብረ ተዝካረ ሞትከ
ህየ ይኩን ሣህል ወምህረት ህየ ይኩን ተክለሃይማኖት
ትርጉም፦-አግረህ በተሠበረበትና መተሰቢያህ
ከሚደረግበት ከዚያ ይቀሪታ ይሁን
ጥቅስ፦- ገድለ ተክለሃይማኖት

መዝሙር
ስምዐፅድቅ ኮነከ
ስምዐ ፅድቅ ኮንከ(3)
ውበአንተዝ <u>ተሠመደከ</u>(2) ተክለሃይማኖት(2)
<u>ትርጉም</u>፡- ተክለሃይማኖት የእውነት ምሥክር ሆነ ስለዚህ ተክለሃይማኖት ተባልክ
ጥቅስ፡- ገድለ ተ/ሐይማኖት

መዝሙር
ትክበር ነፍስየ
ትክበር ነፍስየ በቅድሜከ ዮም(2)
ባርከኒ አባ(2) ባርከኒ አባ (2) ብዕሴ መምህር(2)
ትርጉም፡- የሰው ሁሉ መምሕር የሆንክ አባቴ ሆይ ባርከኝ ነፍሴም በፊትህ ክብር ሞገስ ታግኝ።
ጥቅስ፡- ገድለ ተክለሐይማኖት

መዝሙር
ዜና ውዳሴከ
ዜና ውዳሴከ ፈጸምኩ(2) ተክለሃይማኖት(2)
በስኒ አባ ወልድየ(2) ወልድየ ተክለሃይማኖት(2)
ትርጉም፡-ተክለሃይማኖት የምሥጋና ዜናህን ፈጽሜአለሁ አባቴ ተክለሃይማኖት ልጄ ነህ በለኝ።
ጥቅስ፡- ገድለ ተክለሃማይኖት

መዝሙር
በእንተ ሰላም
በእንተ ሠላማ ለቅድስት ቤተክርስቲያን (2)
ባርከኒ አባ (4) ባርከኒ ተክለሃይማኖት (2)
ትርጉም: ስለ ቤተክርስቲያን ሠላምና አንድነት አባታችን ተክለሃይማኖት ባርክልን።
ጥቅስ:

መዝሙር
ኦ አባ ቅዱስ እቀቦሙ
ኦ አባ ቅዱስ እቀቦሙ(2)
በሥምከ ወበኃይልከ እቅቦሙ(2)
ከመይኩኑ አሐደ ብነ ከማነ(2) ከመ ይኩን(2)
ትርጉም፡- አባቴ ሆይ በፅድቅህ መልሳቸው። በኃይልህ ጠብቃቸው። በስምህ አፅናቸው። ያመኑት ከአኛ ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ።
ጥቅስ፡- ዮሐ 17÷21-26

መዝሙር
በጣና ሐይቅ የኖርሽ
በጣና ሐይቅ የኖርሽ የጌታን ወንጌል ያስተማርሽ
ምንኩስናሽንም በግብር የፈፀምሽ(2)
ብፅዕት ነሽ (2) ክርስቶስ ሰምራ ብፅዕት ነሽ(2)
ጥቅስ:

መዝሙር
ገብረ መንፈስ ቅዱስ
ገብረ መንፈስ ቅዱስ የዓለም ብርሃን ናቸው
ተክለ ሃይማኖትም የዓለም ብርሃን ናቸው
ይኸው ለዘለዓለም ያበራል ሥራቸው(2)
ጥቅስ ማቴ 5÷13-15

መዝሙር
ጼና አልባሲሁ
ጼና አልባሲሁ(2)ስገብረ መንፈስ ቅዱስ ከመፄና ስሂን(2)
አልባሲሁ ዘሜሳት(2) ዘወረደ ውስተ ገነት(2)
ትርጉም: የገብረ መንፈስ ቅዱስ ልብሳቸው እንደ ሸቱ ያማረ ነው ደግሞም ልብሳቸው እንደ ነጭ ሃር ነው እርሱም ወደ ገነት የወረደው ነው።
ጥቅስ: ገድለ ገብረ መንፈሰ ቅዱስ

መዝሙር
እፁብ ነው ድንቅ ነው
እፁብ ነው ድንቅ ነው የአምላክ ስራ
የራሱን ሙሽራ ከጫጉላው ሲጠራ(2)
ገብረ ክርስቶስም በአምላኩ ተመርጦ በመንፈስ ተመልቶ
አበቱ ቤት ሔደ አካሉን ለውጦ (2)
ጥቅስ:

መዝሙር
ይቤላ ህፃን
ይቤላ ህፃን ለእሙ ኢትፍርሒ እም(2) ነበልባለ አሳት
ወአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል ዘአድህኖሙ ውእቱ ያድህነነ(2)
ትርጉም፡- አናቱን ህፃኑ ቂርቆስ እንዲህ አሳት የአሣቱን ነበልባል አትፍሪ አናንያን አዛርያን ሚሳኤልን ያዳን አምላክ ያድነናል።
ጥቅስ፡- ማር 4÷39-41

መዝሙር
ወአናንያ ወአዛርያ
ወአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል (2)
ወአድህኖሙ ውእቱ ያድህነነ(2)
ትርጉም: አናንያን አዛርያን ያዳነ አምላክ ያድነናል።
ጥቅስ: መዝ 56÷ ዳን3÷1-30

መዝሙር
በእንተ ኪዳኑ
በእንተ ኪዳኑ ለሕፃን እንተ አቀረቦ ለነድ(2)
መሀከነ(2)አዘዜ መብረቅ(2)
መሀከነ(2)አዘዜ መብረቅ ወነጐድጓድ(2)
ትርጉም: ነጉድጓድን መብረቅን የምታዝ አምላካችን አሳትን ለአቀዘቀዙ ለስ ሕፃኑ ቂርቆስ ብለህ አዘንልን።
ጥቅስ: ዘፍ18÷22 23 ዘፀ 2÷23-25
ማር9÷33-37

መዝሙር
ሃሌ ሉያ ይቤላ ሕፃን
ሃሌ ሃሌ ሉያ (2) ይቤላ ሕፃን(2)
ኢትፍርሒ እም(2)ነበልባለ አሳት ንፍጸም ገድለነ(2)

ትርጉም፡ ሕፃኑ ቁርቆ እንዲህ አሳት የአሳቱን
ነበልባል አትፍሪ ገድሳችንን እንፈጽም
እንጂ::
ጥቅስ፡ ማቴ10÷34-39 ሉቃ20÷23

መዝሙር
ጳውሎስ ሲመራን
ጳውሎስ ሲመራን ጴጥሮስ ሲከፍትልን
ወደ ጽድቅ አዳራሽ እንግባ ሁሳችን
ስዘለዓለም በጌታችን እንሞትም ሕያው ነን(2)
ሠይፍና መከራ ሞትም ቢሆን ሕማም
ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን የለም
ስዘለዓለም በጌታችን.....
ፍቅራችንም ይሁን ያለግብዝነት
ፀንተው እንዲኖሩ ተስፋ ፍቅር እምነት
ስዘለዓለም በጌታችን.....
ጥቅስ፡ ሮሜ 8÷35-39

መዝሙር
መዝሙር ለሣዓል ወኬፋ
ለሣዓል ወኬፋ(4)
አክሊሎሙ(2) ይኩነነ ተስፋ(2)
ትርጉም፤-የሣዓልና የኬፋ/የጳውሎስና የጴጥሮስና
የሰማዕትነት አክሊሳቸው ለኛ ተስፋችን
ይሁን::
ጥቅስ፤-1ኛ ቆሮ 15÷3 ጢሞ 4÷7

መዝሙር
አመ አመ አመ እዎ
አመ አመ አመ እዎ(2)
ቅዱሳን ሐዋርያት
ሁለት ፀሐይ አሉ ሐዋርያት
ስማቸው ብርሃን ነው ሐዋርያት
መጀመሪያው ጴጥሮስ "
ሌላው ጳውሎስ ነው "
እኸ አመ.....
ብርሃናተ ዓለም ሐዋርያት
ጴጥሮስ ወጳውሎስ "
በእውነት ተሰየ፮ "
ስለክርስቶስ "
እኸ አመ.....
የዘለዓለም ሕይወት ሐዋርያት
ማግኘት ያማራችሁ "
የሐዋርያት ሥራ "
ይሁን አላማችሁ "
እኸ አመ.....
ሐዋርያት ዘርተው ሐዋርያት
ሲስቅሙ በሻማ "
ስዎች አትለዩ "
ከወንጌል ሉውድማ "
እኸ አመ.....
ውሆች ቀለም ሆነው ሐዋርያት
እንጨቶች ብዕር "
ቢፅ፮ት አያልቅም "
የሐዋርያት ክብር "
እኸ አመ.....

ጥቅስ፤- የሐዋ 1÷27 ማቴ 5÷14-16
ማቴ 16÷18-19

መዝሙር
ኤልያስሰ
ኤልያስሰ ሊወሀበነ ዝናመ(2)
እምነ አሃዱ ገራህት ሪአራዊ ትልመ(2)
ትርጉም፡

ጥቅስ፡ ያዕአ÷16

መዝሙር
መሠረተ ዜማ ወጠነ
መሠረተ ዜማ ወጠነ(2) ያሬድ ካህን(2)
ያሬድ(4) ካህን ጥዑመ ልሣን(2)
ትርጉም፤- እንደበቱ ያማረ የቤተክርስቲያን አገልጋይ
የሆነ ያሬድ የዜማን መሠረት ጀመረ
ጥቅስ፤-

መዘሙር
አሠርጐካ
አስርጐካ ለሲትዮጵያ
በስብሐት ወበ ሃሌ ሉያ(2
ያሬድ ካህን ፀሐየ ስቤተክርስቲያን(2)
ትርጉም፡

ጥቅስ፤ እንቀፀ ብርሃን (ድጓ)

መዝሙር
ያሬድ ፈልፈል
ያሬድ ፈልፈስ ማኅሌት ወቅኔያት ወባሕረ ጥበባት
አስመ ከነ መርሐ መዝሙሩ ለሲትዮጵያ
ያሬድ ካህን ጥዑም ልሣን(2)
ጥቅስ፤-

መዝሙር
ፃድቃን ብሩካን
ፃድቃን ብሩካን ዓለምን ንቃችሁ
የክርስቶስን ፈለግ የተከተላችሁ
በመንግሥተ ሰማይ አጽፍ ነው ዋጋችሁ
ሰአሉ ለነ አሰተምሕሩ ለነ አስመ በፀሎተ
ፃድቃን ትድኅን ሐገር
ቀዳሚ ሰማእት አስጢፋኖስ ዲያቆን
ወቅዱስ ጊዮርጊስ መክብበ አሚን
ምስለ ሲየሉጣ ወቂርቆስ ሕፃን
ሠዓሉለነ.....
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዘአምአቅሌስያ
ወተክለሃይማኖት ዘሲትዮጵያ
ወማርቆስ አብ ዘአስንድርያ
ሠዓሉለነ.....
አሥራ ወአርባእቱ ካህናተ ሰማይ
አጠንተ መንበሩ ለአምላክ አደናይ
መንበረ ፀባኦት ዘላአልአይ
ሠዓሉለነ.....

ትንቢተ ነቢያት የተፈፀመብሽ
የኢያቄም ርግብ ማርያም አንቺ ነሽ
ስምኝልን ስኚ በሃና በአናትሽ
ሰዓሊስነ አስተምሪስነ አስመ በፀሎትኪ ትድንን
ኢትዮጵያ
ኢትዮጵያ (2) ሐገርነ ነያ
ጥቅስ: ምሳ 15÷29 ማቴ 16÷24-28

መዝሙር
የፃድቃን መአዛ
የፃድቃን መአዛ ደስ ይላል አንደ ጽጌረዳ(2)
ያድነናል(2) ከኃጢአት ፍዳ(2)
ጥቅስ:

መዝሙር
የፃድቃን ከተማ
የፃድቃን ከተማ ሆነች መንግሥትህ
አምላክ የፈጠርካት <u>ስመገኖቸህ</u> (2)
ያራዊቱን ድምጽ የሌሊቱን ግርማ
በትዕግሥት አስፋት <u>ያን ሁሉ ጨለማ</u>(2)
ሀብትና ንብረትን ተድሳን ሁሉ ናቁ
መንግሥትህን ብቻ <u>ስማየት ናፈቁ</u>(2)
ቅዱሳን አፆችህ ሰውን የፈጠሩ
ስሰው ሕይወት ሲሉ <u>በምስማር ታሰሩ</u>(2)
ይህንን ሁሉ ግፍ ቅዱሳንም አይተው
በሀዘን አስፈ <u>መሳ ሕይወታቸው</u>(2)
ምሕረትና የበዛ ቸር አምላካችን
በምሕረትህ ጐብኛት <u>ኢትዮጵያን</u>(2)

ጥቅስ: ማቴ 19÷16-30 ማት15÷21 2ኛ
ተሰሎ1÷5-7

መዝሙር
ቅዱሳን
ቅዱሳን ሰማአታት ፃድቃን
ስምኑልን ስኚ ምሕረን
ግሩማን መላእክት ስዓይን
ሚካኤል ገብርኤል ሱራፊል ኪሩቤል
ካህናተ ሰማይ ዑራኤል ሩፋኤል
ሱራኤል ፋኑኤል አፍኒን ራጉኤል
ብርናኤል አቅናኤል ሱባኤል ፍናኤል
ቅዱሳን_____
የእስራኤል ነቢያት ሕዝቅኤል ዳንኤል
ዳዊት ሰሎሞን ኤርምያስ ሳሙኤል
ኢሳይያስ አሞጽ ሐጌ ዘካርያስ
አንባቆም አብዱዩም ናሆም ሶፎንያስ
ቅዱሳን_____
ጴጥሮስ ጳውሎስ ሐዋርያት
የተሰዋችሁ ስተዋሕዶ አምነት
ቅዱሳን_____
አስጢፋኖስ ዲያቆን ቅዱስ ጊዮርጊስ
መጥምቁ ዮሐንስ መርቆርዮስ
ተክለ ሃይማኖት ዜና ማርቆስ
ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ
ቅዱሳን_____
ፃድቃን ሰማአታት ቅዱሳን መላእክት
ምሕረት ስምኑላት ሆናችሁ በአንድነት
አምላክ ተስመናት ኢትዮጵያን
አጆቿን ዘርግታ ስትማፀን
ቅዱሳን_____
ቅዱሳት ፃድቃን ሰማዕታት
ስምኑላት ይሰጣት ምሕረት
ግሩማን መላእክት ስዓይን
ጥቅስ:

መዝሙር
ፃድድቃን ኢሞቱ
ፃድቃድሰ ኢሞቱ ሀበ አግዚኦሙ ነገደ (2)
በመንግሥተ ሰማይ አንበሮሙ በመንግስተ ሰማይ (2)
ትርጉም: ፃድቃን አልሞቱም ነገር ግን ወደ ጌታቸው
ሔድ አርሱም በሰማያዊ ክብር አክበራቸው
አስቀመጣቸው::
ጥቅስ: መዝ 115÷6

መዝሙር
ይትፌስሁ ፃድቃን
ይትፌስሁ ፃድቃን (2) በአግዚአብሔር (2)
ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ በጥዑመ ልሳን (2)
ትርጉም: ፃድቃን በአግዚአብሔር ደስ ይላቸዋል ደስ
በሚል ዜማ ሃሌ ሉያ አያሉ ያመሰግናሉ::
ጥቅስ: መዝ 32÷በሙሉ

መዝሙር
መዓዛሆሙ
መዓዛሆሙ ለቅዱሳን ከመፅጌ ደንጐላት ዘውስተ
ቁላት(2)
ፀገዩ ቀንሞስ መስለ ናርዶስ(2)
ትርጉም: የቅዱሳን ሽታቸው ሥነ-ምግባራቸው አንደ ቆላ
ሱፍና አበባ ነው:: ናርዶስ የሚባለው ዛፍና
ቀንሞስ የተባለው ዛፍ አብረው አበቡ::
ጥቅስ

መዝሙር
ሰላም ስዝክረ ስመከ
ሠላም(3)ስዝክረ ስምከ(2)
ጥዑመ ዜና(4) መድኃኔዓለም ጥዑመ ዜና(2)
ትርጉም: ዜናህ ያማረ የዓለም መድኃኒት
ጌታ ሆይ ስስም አጠራርህ ምስጋና
ይገባል::
ጥቅስ: መዝ112÷1-4 መዝ 137(138)1-8

መዝሙር
አሳተ ጽርሁ
አሳተ ጽረሁ ማየ ጠፈሩ(2)
ደመና መንኮራኩሩ ስመድኃኔዓለም(2)
ትርጉም: የመድኃኔዓለም አዳራሹ አሳት ነው
ጣራው ውኃ ነው:: የመድኃኔዓለም
መውጫ መውረጃው ደመና ነው::
ጥቅስ: ዘፍ33÷1-3 ማቴ14÷22-36

መዝሙር
ንጉስ ውእቱ ክርስቶስ
ንጉስ ውእቱ ክርስቶስ(4)
አምላክነ(2) መድኃኔዓለም(2)
ትርጉም: ክርስቶስ አምላካችን መድኃኒታችን
የዓለም ንጉስ ነው::
ጥቅስ: ጢሞ 6÷15-16
መዝሙር 516-522

መዝሙር
ውስቴታ ታቦት
ውስቴታ ታቦት በውስቴታ ኦሪት በውስቴታ(2)
ደኪልልዋ በወርቅ ደኪልልዋ(2)በወርቅ ደኪልልዋ(2)
ትርጉም:

ጥቅስ:

መዝሙር
ጽላት ዘሙሴ
ጽላት ዘሙሴ ጽላት(2)
ጽላት ዘሙሴ ጽላት(2) ሕግ ወሥርዓት(2)
ሙሴ ከፈጣሪ የተቀበላት አስርቱ ትዕዛዛት
የተፃፋባት ጽላት ዘሙሴ ጽላት(2)
ደስቲ አፀ መድኃኒት(2)
ደስቲ አፀ መድኃኒት (2)ማርያም ቅድስት(2)
ጥቅስ: ዘፀ31÷

መዝሙር
ተቀደሲ
ተቀደሲ ወንስዒ ኃይለ ኦ ምስካየኃዙናን(2)
አስመ ናሁ ንጉሥኪ መጽአ ዘያበርህ ለኪ
አግዚአብሔር(2)
ትርጉም: ያዘኑት መጠጊያ ቤተክርስቲያን ሆይ
ከኃጢአት ከበደል ተለይ ንጉስሽ
መጥቷልና::
ጥቅስ: ሐዋ20÷28

መዝሙር
አመ ትትሐነጽ
አመ ትትሐነጽ ምስካየ ኀዙናን በእንቆ ሰንፔር
ወበከድከዴን በእንቆ ሰንፔር(2)
አረፋቲ ሀኒ ለቤተክርስቲያን ወማይፈዲ ሀኒ በወርቅ
ንፁሕ ወመርህባስ ለኢየሩሳሌም(2)
ትርጉም: ከርከዴ ሰንፔር የሚባል የእንቁ አይነት
ለቤተክርስቲያን ምሳሌ የሆነች ኢየሩሳሌም
በምትታነጽ ጊዜ ደረጃዋና አዳራሽዋ በንፁህ
ወርቅ ሜዳዋ ግን የከርቤ መልክ ያለው
ነበር::
ጥቅስ: መዝ77÷69

መዝሙር
ሐነጽዋ
ሐነጽዋ ለቤተክርስቲያን ወሣረርዋ ለመንፈስ ቅዱስ
እንተ ተሀንፀት በአዳ ካህናት(2)
ወተቀደሰት በአፈ ጳጳሳት ወተአትበት በማይ ዘህውዘ
<u>አምገቦሁ</u>(2) አመ ሕማማቲሁ(2)
ትርጉም: በካሕናት እጅ የታነፀች በጳጳሳት ፀሎት
ከበደል ከመርገም ከኃጢአት የተለየችውን
መድኃቸችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ አርብ
መከራችንን በተቀበለ ጊዜ በጐኑ በፈሰሰው
ውኃ የተባረከችዋን
ጥቅስ: ሐዋ20÷28

መዝሙር
ኃይለ ጽለመት ተሰደ
ኃይለ ጽለመት ተሰደ (2)
በሰንበት ሀይለ ጽለመት ተሰደ(2)
ትርጉም:

ጥቅስ:

መዝሙር
መንበረ ጽላቱ
መንበረ ጽላቱ(4) ተከበረ ቤቱ
ቅድሰተ ቅዱሳን መቅደስ ማሕሌቱ
የመድኃኔዓለም ተከበረ ቤቱ(2)
ሁስተኛይቱ ኢየሩሳሌም
ምስካየኃዙናን ኑሪ ዘላለም(2)
መንበረ ጽላቱ.....
ከተቀደሰብሽ ከፀና ቤትሽ
ተከበረ ዛሬ ክብረ በዓልሽ(2)
በደሙ የዋጀሽ እየተንገላታ
አንቺን ሊቀድሰ ነው በጥፊ የተመታ(2)
መንበረ ጽላቱ.....
የኀዙናን እናት አንባ መጠጊያቸው
ክርስቲያን ልጆችሽ ሆድ አንዳይብሳቸው(2)
ጠብቂ ምዕመናን ተኩላ አንዳይነጥቃቸው
ደጅ ይፁኑ ቤትሽ መጽናኛ ሁኖቸው(2)
መንበረ ጽላቱ.....
ጥቅስ: ጢሞ 3÷15

መዝሙር
ወወጽአ በሰላም
ወወፃ በሠላም ወፃ በሠላም(2) መድኃኔዓለም
ወጣ በሠላም (2) መድኃኔዓለም
የሕዙናን አባት የዓለም መድኃኒት
መድኃኔዓለም ወጣ ተቀበሉት
ወወጽአ.....
መጠጊያ ለፍጥረት የዓለም መድኃኒት
መድኃኔዓለም ወጣ ተቀበሉት
ወወጽአ.....
ሳዘኑት መጠጊያ ለደካሞች ብርታት
መድኃኔዓለም ወጣ ተቀበሉት
ማኅደረ መለኮት የዓለም ሁሉ እናት
ድንግል ማርያም መጣች ተቀበሏት
ወወጽአ.....
የሰው ሁሉ እናት የመላእክት እህት
ድንግል መጣች ኑ እንቀበላት
ምስጋና አናቅርብ ሆነን በመንፈስ
የአምላክ ወዳጅ መጣ ዮሐንስ
ወወጽአ.....
ፍቁረ እግዚእ መጣ እቀበለው
ሳመንበት አማላጃችን ነው
ገባ በሰላም መድኃኔዓለም
ጥቅስ:

መዝሙር
አበው ፀልዩ
አበው ፀልዩ በእንቲአነ
ፀሎትክሙ ትባርከነ
የቅዱሳን ፀሎት የአባቶች ልመና
ከኃጢአት በሽታ ይፈውሳልና (2)
አበው ፀልዩ.....
የሕግ መሠረት ስላደረጋችሁ
የቤተክርስቲያን አእማደች ናችሁ(2)
አበው ፀልዩ.....
ወደ እኛ ስትመጡ እናንተ ጻድሳት
የክርስቲያን ደሴት ኢትዮጵያም ደስ አሰኘት (2)
አበው ፀልዩ.....
ጥቅስ:

መዝሙር
ባርከኒ አባ
ባርከኒ አባ ለወልድከ ዝኬ(2)
አስመ ልማዱ ውእቱ ለመምሕር ቡራኬ(2)
ትርጉም:

ጥቅስ:

መዝሙር
አሰርጐካ
አሰርጐካ ለኢትዮጵያ በስብሐት በሃሌ ሉያ(2)
ጳውሎስ ፀሐያ ለቤተ ክርስቲያን
" " ለኢትዮጵያ(2)
ትርጉም: የኢትዮጵያና የቤተክርስቲያን ፀሐይ ጳውሎስ ኢትዮጵያን በምስጋና ጌጥ አስጌጥካት::
ጥቅስ:

መዝሙር
ብፁአን ጻድሳት
ብፁአን ጻድሳት ብፁአን ሊቃነ ጻድሳተ(2)
አስተምሩ ለነ በስሒን ወበትሕትና ሃበ ንጉሥ ስብሐት(2)
ትርጉም:

መዝሙር
ቅዱስ አባታችን
እንኳን ደህና መጡ (3) ቅዱስ አባታችን(2)
የተዋህዶ ልጆች እጅ እንነሳስን (4)

መዝሙር
ሠላም ለክሙ
ሠላም ለክሙ ኦ ማኅበራኒሁ ለክርስቶስ እስ ተጋባይክሙ
ውስተ ዛቲ መካን(2)
ጻድሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ሕዝበ ክርስቲያን ፅኑአን
በተዋህዶ ሃይማኖት ርትዕይት(2)
ትርጉም: በዚህች የተሰበሰባችሁ (የተገኛችሁ) የክርስቶስ ማኅበር የምትሆኑ ቀጥተኛ በሆነች በተዋህዶ ሃይማኖት ወይም እምነት የፀናችሁ ጻድሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት እንዲሁም ክርስቲያኖች በሙሉ ሠላም ለእናንተ ይሁን::

መዝሙር
ባርከኒ አባ
ባርከኒ አባ መፍቀሬ ምዕመናን _____
አስመ አንተ(2) ሰባኬ ወንጌል ሐዲስ ሰባኬ ወንጌል _____
ትርጉም: ምዕመናን የምትወድ (ሕፃናትን)
የምትወድ_____ ሆይ
ባርከን የሐዲስ ወንጌል መምሕር
አንተ ነህና::

መዝሙር
እኁ ወአንተሰ
እኁ ወአንተሰ እኁ_____
እኁ ወአንተሰ እኁ ፖትርያርክ
እኁ ቀዊመከ ፀሊ ለኢትዮጵያ
እኁ ቀዊመከ ፀሊ ለቤተክርስተያን
ትርጉም: አንተ

መዝሙር
ትክበር ነፍስየ
ትክበር ነፍስየ በቅድሜከ ዮም(2)
ባርከኒ አባ(5) ብዕሴ መምሕር
ትርጉም:

መዝሙር
ጳጳሳት
ጳጳሳት(2) ወኤጲስቆጶሳት(2)
ቤተክርስቲያናችን ልትጐበኝት
ወደርሷ ስትመጡ ለባርኮት
በአናንተ ተመካች በጣም ደስ አላት
ጳጳሳት.....
አንዲት ተዋሕዶ ኦርቶዶክሰዊት
አደራ አለባችሁ ልትጠብቋት
የክርስቶስ ወንጌል ሐዋርያት
የአምነት መስዋዕት ሰማዕታት
ጳጳሳት.....
የኢትዮጵያ አባቶች ገፀ በረከት
የተወሰናችሁ በፃም በፀሎት
አገርን ጠብቁ አኛን ከጥፋት
ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይዛችሁ መብራት
አንድትመሩን አኛን ኋላ ከገነት
ጳጳሳት.....
አንስገድሳቸው የአክብሮት ስግደት
አንቀበላቸው ሆነን በአንድነት
አንዘምርላቸው መዝሙረ ዳዊት
ሥልጣንን ያገኙ ማሰርን መፍታት
ጳጳሳት.....

መዝሙር
ብፁዕ አባታችን

መዝሙር
በከመ ደቤ
በከመ ደቤ ጳውሎስ ንግድፍ አምላአሌነ ኩሉ
ምግባረ ጽሰመት(2)
ወልበስ ወልታ ጽድቅ ንልበስ ወልታ ጽድቅ(2)
ትርጉም: ጳውሎስ አንደተናገረ የጨለማን ትተን
የጽድቅን ጋሻ አንያዝ::

መዝሙር
አባ አቡነ ቅዱስ
አባ ኡቡነ (4) መምሕር አባ_____
አም አዕላፍ ሕሩይ (2) አባ(6) አቡነ
ትርጉም: አባታችን መምሕራችን ሆይ
ከብዙዎች የተመረጥክ ነህ::

መዝሙር
ሃሌ ሉያ ግሩም
ሃሌ ሉያ _____ግሩም በመንፈስ ቅዱስ ህቱም
መአዛ ቅዳሴከ ጥዑም(2 ከመ ጽጌረዳ(2)
ንአ ንአ ማዕከሌነ ቆመ በመስቀልከ ባርከነ ዮም
_____ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት አኽ
ዘኢትዮጵያ
ትርጉም: የቅዳሴህ መዓዛ እንደ ጽጌረዳ ደስ
የሚያሰኝ በመንፈስ የተቀባህ ____
ግሩም ነህ:: የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ
የሊቀጳጳሳት አለቃ ፓትርያርክ ____
በመካከላችው ሆነህ በመስቀልህ
ትባርካቸው ዘንድ ና::

መዝሙር
ሃገሩሰ
ሃገሩሰ ለቅዱስ _____ትመስል ደብረሲና(2)
ወሀደረ ላእሌሀ ሀፁረ የአውዳ ወጽጌረዳ በትምዕርተ
መስቀል(2)
ትርጉም:

መዝሙር
እንኳን ደህና መጣችሁ
እንኳን ደህና መጣችሁ(2)
ወደኔ ወደ እናታችሁ
እጄን ዘርግቼ ስጠብቃችሁ
ወላጆቻችሁን እንድታከብሩ
አምላካችን መናገሩ
እንኳን ደህና መጣችሁ.....
እንድትፈፅሙ እንጂ ትዕዛዙን
እንቢተኞች ባለመሆን
በከንቱ አይደለም የሰጠን ሕጉን
እንኳን ደህና መጣችሁ.....
የእውቀት ገበያተኞች እንደመሆናችሁ
ምንም ጊዜ ባይኖራችሁ(2)
እንኳን ደህና መጣችሁ.....
እንደዚህ እኮ የምላችሁ
ቤተ ክርስቲያን ነኝ እናታችሁ(2)
እንኳን ደህና መጣችሁ.....
ስለመጣችሁ እናት ልጆቼ
ታዩኛላችሁ ተደስቼ(2)
እንኳን ደህና መጣችሁ.....
ከሰኞ እስከ ዓርብ አየሠራን
እንጠያየቅ በሰብንበት ቀን(2)
እንኳን ደህና መጣችሁ.....

መዝሙር
በሰላም ላመጣ
በሠላም ላመጣ እንግዶቻችንን(2)
እኽ እናቅርብ(2) ምስጋና ስፈጣሪያችን(2)

መዝሙር
እግዚአብሔር ይመስገን
እግዚአብሔር ይመስገን(4)
ስዚህ ያደረሰን(4) እግዚአብሔር ይመሰገን(2)

መዝሙር
እንኳን ደስ አላችሁ
እንኳን ደስ አላችሁ(3)
መልክተ ዮሐንስ ሀ ሁ ብላችሁ
ፊደል ቆጥራችሁ
ከነ የኔታ ጠዋትና ማታ
ተመላልሰችሁ ስዚህ በቃችሁ
እንኳን ደስ.....
የአምላክ ቸርነት አረቂቅነት
ይህነው ቸሮታው ከሕፃንነት እስከ አዋቂነት
ዓመታት ቆጥሮ ስዲግሪ መብቃት
" " ስዲፕሎም መብቃት
እንኳን ደስ.....
አደራ እንዳትረሷት ቤተክርስቲያንን
እናታችንን እንዲት ተዋህዶን አደራችሁን
እንኳን ደስ.....
የተዋህዳ ልጆች እናንተ ሁላችሁ
የእውቀት ካባ ጃኖ ስብሳችሁ
ደስ ማስታችሁ
እንኳን ደስ.....

ጥቅስ: መዝ 25÷12

መዝሙር
ስዚህ ቀን ሳበቃ
ስዚህ ቀን ሳበቃ ወንድሞታችንን
ስዚህ ቀን ሳበቃ እህቶቻችንን
እኽ እናቀርብ(2) መስጋና ስፈጣሪያችን(2)

መዝሙር
ማርያም በሰላም አድርሽው
ማርያም(2) ድንግል ማርያም(2)
በሠላም አድርሰሽ መልሽው(ሾት)
ወንድማችንን(አህታችንን) (2)

መዝሙር
የማይሳነው አምላክ
የማይሳነው አምላክ ወልደ አብ መድኃን(2)
አንተን(ችን) መልሶ አኛን አቆይቶ በሠላም በቸር
ይግጠመን(2)

መዝሙር
መድኃኔዓለም የሁላችንም አለኝታ
መድኃኔዓለም የሁላችንም አለኝታ(2)
ልጅሽህን አድርሰው(ሳት) ሆነህው(ሀት) መከታ
ማርያም (2)ድንግል ማርያም
በሠላም አድርሽ መልሽው ወንድማችንን
መሪ ሆነሽ በሚሔድበት ቦታ
ድንግል ሆይ አትራቂው ከጎኑ ቀንም ሆነ ማታ(2)
አማላጆች ተራድአያን መላእክት
(ክርስትና ስም) ጠብቀት(ቂት) አንዲፀና(ድትፀና) በአምነት
እናመሰግን ስዚህ አድል ሳበቃቸው(2)
ችሩ መድኃኔዓለም በእውነት(2) ሁሉን ፈጣሚ ነው(2)

መዝሙር
እናታችን ድንግል ማርያም
እናታችን ድንግል ማርያም ትቀበልህ በሠላም(2)
በመድኃነዓለም ቤት ብዙ ቆይተሀል
ትምሕርተ ወንጌልን ሁሉ ተምረሀል
እናተችን ድንግል.....
አራቅክም ነበረ ከፈጣሪ ደጅ
መዳኛ ለማግኘት ደግሞም አማላጅ
እናተችን ድንግል.....
እናታችን ማርያም ድንግል ትቀበልህ
ከልጇ አማልዳ ከጉኗ ታስቀምጥህ
እናተችን ድንግል.....
ከቶ ብትለየን ከሥጋ ከዓለም
አንገናገናኛለን በመንግሥተ ሠማይ
እናተችን ድንግል.....
እንዳገለገልካህ ማህበርህን
በመንግሥተ ሰማይ ያብዛልህ ተድላን
እናተችን ድንግል.....
በቤተክርስተያን ደጅ እንደፀናህው
ዋጋህን በሰማይ ይከፈልህ በሰፊው
እናተችን ድንግል.....
መንግሥተ ሰማያት ፈጣሪ ያውርስህ
በፃድቃን ከተማ በደስታ ያኑሩህ

አናተችን ድንግል.....
እጅህን ዘርግተህ ስሙን እንደጠራህ
አጾቹን ዘርግቶ አምላክ ደቀበልህ
አናተችን ድንግል.....
ከቶ አንረሳህም ወንድማችን በእውነት
ዳግም ያገናኝን በሳይኛው መንግሥት
አናተችን ድንግል.....
ከሠለስቱ ደቂቅ በክበር ተቀምጠህ
ውዳሴ አምላክን ለማቅረብ ያብቃህ
አናተችን ድንግል.....
ከአብርሃም ከይስሐቅ ደግሞም ከያዕቆብ
በምስጋና ኑር ደምቀህ እንደ ኮከብ
አናተችን ድንግል.....

መዝሙር
ሞቼ ስለማልቀር
ሞቼ ስለማልቀር ትንሣኤ ስላለኝ
በተስፋ ቤታችን ስለምንገናኝ
ወዳጅ ዘመዶቼ ታልቅሱ በቃኝ(4)
አገኛለሁና ገና አዲሱን ኑሮ
አምላክ አስቡት ይብቃችሁ እሮሮ
ይልቅ ፀልዮላት ለነፍሴ አርፍት
በቀኝ እንዲያኖራት የፃድቃን አባት
ዓለም ኪራይ ቤት ናት ዘላቂ አይደለችም
ለሥጋ ነው እንጂ ለነፍስ አትመችም
ግን በእርሷ ስንኖር ትዕዛዙን ከፈፀምን
ለተዘጋጀው ቤት ወራሾች እኛው ነን(2)
ጥቅስ፡-1ኛ ተሰ 4÷13-18 1ኛ ቆሮ 15÷13
በሙሉ ማቴ 25 በሙሉ

መዝሙር
አዝናለሁ አለቅሳለሁ
አዝናለሁ አለቅሳለሁ ስለ በደሌ ሁል ጊዜ
አለቅሳለሁ
ነገር ግን መሀሪ ነህና እንደምታድነኝ
አምናለሁ(2)
ሥጋዬ ስራሱ አየታለለኝ(2)
ሁሉን በመፈስግ ወሰደና ስጥፋት ሰጠኝ(2)
አዝናለሁ.....
ከመሬት ተገኝታ እመሬት ስትገባ
በከንቱ አስቀረችኝ እያሳሳች ሥጋ ሰገብጋባ(2)
አዝናለሁ.....
ትቻት መሔዴ ነው አፈር ሥጋዬን(2)
እንድትቀበላት አምላኬ ሆይ አደራ ነፍሴን(2)
አዝናለሁ.....
ትተናት ስንሔድ አፈር ሰጋችንን(2)
እንድትቀበላት አምላካችን አደራ ነፍሳችን(2)
አዝናለሁ.....
ጥቅስ: ሮሜ 7÷13-20

መዝሙር
ላይቀር መሞት
ላይቀር መሞት አፈር መልበስ መግባት ከመቃብር
መስሎኝ ቂሚ ይህ ሥጋዬ ለእርሱ ብቻ ስጥር
ግን ለነፍሴ ቀረ ማስታወሴ(2)
ዘመን መቁጠር ዕለት ወራት ክረምትና በጋ
ሌትና ቀን ሲፈራረቅ ሲጨልም ሲነጋ
በማየቴ ይሁን መደሰቴ(2)
ኧረ ወዲያ ወዲያልኝ ዋ ይብላኝ ለነፍሴ
አድርጉኛል የኃጢአት ምንጭ ደካማው መንፈሴ
ላልኖር በዓለም ቆሜ ለዘለዓለም(2)
መሀሪ አምላክ ለጋስ ጌታ ቸሩ ፈጣሪዬ
አንተ እኮ ነህ ለዘለዓለም ለኔ መመኪያዬ
ይቅር በለኝ ምሕረትህ አደራቀኝ(2)
ጥቅስ: ኤፌ2÷1-5

መዝሙር
ሞት አልተወደድክም
ሞት አልተወደድክም በጣም ተጠልተሀል
ትንሹም ትልቁም ያርቀው ይሁሀል
ይኛ ሀሳብማ መቼ በአጭር ያልቃል
ዋ ! ሞት አለና ታዲያ ምን ይሆናል
ከሞት አንደማይቀር ሲያስብ ልቦናዬ
አንደ ክረምት ውሃ ይወርዳል አንባዬ
ከሞት እንደማይቀር ሲያውቀው ልቦናችን
አንደ ክረምት ውኃ ይወርዳል አንባችን

መዝሙር
መፃ ዘመፃ እምላእሉ
መፃ ዘመፃ እምላእሉ(2)
መርአዊ መጽአ(2) ተቀበሉ መጽአ ተቀበሉ(2)
ትርጉም፡ ከወደ ሰማይ የወረደ ሙሽራ መጥቷልና ውጡና ተቀበሉ::
ጥቅስ፡ ማቴ 25 ÷ 1-13

መዝሙር
መርአዊ ስቡሕ
መርአዊ ስቡሕ ካህን ውእቱ
ወእስከ ለዓለም(2) ካህን ውእቱ(2)
በገሊላ አውራጃ ከሠርግ ቤት ገብቶ(2)
ጋብቻን ባርኮታል ቀድሶ አዘጋጅቶ(2)
አዳምን ብቻህን አትኑር ሲለው(2)
ሔዋንን ከጐኑ በመፍጠር ሰጠው(2)
በግላዊ ኑሮ የትም ከመኮብለል(2)
በአንድ አካል በአንድ አምሳል ጋብቻ ይሻላል(2)
ጥቅስ፡ ዮሐ2 ÷ 1 ዘፍ2 ÷ 18-25

መዝሙር
ህገ ሰብአናሁ አቀበ
ህገ ሰብአናሁ አቀበ በተደንግሎ(2)
ወፈፀመ በወንጌለ ዘሀሎ(5)
የወንጌልን ትዕዛዝ ፈፀመ(2) በድንግልና(2)
ሙሽራው በአምነት(2) የፀና ነውና ሃይማኖቱ መሠረት ናትና(2)
ጥቅስ፡ 1ኛቆሮ7 ÷ 2-7 ኤፌ5 ÷ 3-14

መዝሙር
ይደሰት ሙሽራው
ይደሰት ሙሽራው በሥርዓተ ተክሊል ሲያገባ(2)
አሸበረቀ ደመቀ አጌጠ በሙሽሪት አበባ(2)
በሥጋው ወደሙ ፍፁም አንዳዘዘው ወንጌሉ አኽ (2)
በሙሽሪት ነው ሙሽራው ያማረው ሥርዓተ ተክሊሉ(2)
ጥቅስ፡ ዕብ13 ÷ 4

መዝሙር
የኛማ ሙሽራ
የኛማ ሙሽራ (2) የኛ ሙሽራ
የኛማ ሙሽራ(2) አፁብ ድንቅ ሥራ
እንዲህ ነው ሥርዓት እንዲህ ነው ጋብቻ
በአምነት በምግባር ሲሆኑ አቻ ላቻ
የኛ ሙሽራ.....
የአብርሀም የሣራ ይሁን ጋብቻችሁ
መልካም ዘርን አፍሩ አምላክ ይባርካችሁ
የኛ ሙሽራ.....
ሙሽሪት ሙሽራው እንኳን ደስ አላችሁ
ተከበረ ዛሬ መልካም ጋብቻችሁ
የኛ ሙሽራ.....
የመድኃኔዓለም ልጅ የተዋህዶ ፍሬ
አምሮ ደምቆ ታየ ወንድማችን ዛሬ
የኛ ሙሽራ.....
የመድኃኔዓለም ልጅ የተወሐዶ ፍሬ
አምራ ደምቃ ታየች አህታችን ዛሬ
የኛ ሙሽራ.....
ጥቅስ፡ ዘፍ11 ÷ 29 ዘፍ 21 ÷ 1-8

መዝሙር
መጽአ መርአዊ
መጽአ መርአዊ ፍስሀ ለኩሉ እኽ (2)
በሠላም ፃዉ ተቀበሉ(2)
ሙሽሪት ሙሽራው የሃይማኖት ፍሬ
በቅዱስ ጋብቻ አንድ ሆኑ ዛሬ(2)
አንድ ያደረገውን ጌታችን በቃሉ እኽ (2)
ሊለየው አይችልም የሰው ልጅ በኃይሉ(2)
የወንጌልን ትዕዛዝ በመፈፀማው እኽ (2)
የብርሀን አክሊልን ደፍተው አየናቸው(2)
አህቶች ወንድሞች ክርስቲያኖች ሁሉ እኽ (2)
ሙሽሪትንና ሙሽራን ምሰሉ(2)
በመንፈሳዊ ፍቅር በመተባበር እኽ (2)
አንግዲህ ጀምሩት መልካሙን ትዳር(2)
ጥቅስ፡ ማቴ 19 ÷ 3-12 ዘፍ1 ÷ 27-28

መዝሙር
መርአዊ ሰማያዊ
መርአዊ ሰማያዊ(2)
ለእመ ገብረ በአለ(2) እኽ እኽ እኽ
ይኑሩ በሠላም(4) ፀንተው ዘለዓለም
ደናግል ተነሱ ያዙ መብራቱን
ሙሽራው ደረሰ አጉል እንዳንሆን
መርአዊ.....
ወንጌልን ይዘራል ጐዳቸው ያምራል
ዓላማው መልካም ነው እነርሱን እንምሰል
መርአዊ.....
የድካም ዋጋቸው(2)
ብርሃንን ያበራል በማህበራቸው(2)
መርአዊ.....
ጥቅስ፡ ማቴ 25 ÷ 1-13

መዝሙር
ዘኢዮር መንበሩ
ዘኢዮር መንበሩ ሐረግ ሙሽራው ማማሩ(2)
ማማሩ(2) ማማሩ ማማሩ(2)ማማሩ
እንዲህ ነው ጋብቻ ማማሩ እንዲህ ነው ስርዓቱ
ቃል ኪዳን አክብሮ " ለትዳር መብቃቱ
ቃል ኪዳን ሰይፍ ነው " መልሶ ይበላል
ክደትን አይወድም " አምነትን ያፈቅራል
ዘኢዮር.....
ትዳር እንዲፀና ማማሩ ሕይወት እንዲሰፋ
ፍቅር ነች ዋናዋ " የሰው ልጆች ተስፋ
ቂም በቀል ተረስቶ " እንዲሆን ደስታ
ፍቅር ነች ማሰሪያ " የምታበረታ
ዘኢዮር.....
ጌታችን እንዳለው ማማሩ ደግሞም በሠማይ
ምንም ስሜት የለም " ከፍቅር በላይ
ዘኢዮር.....
ጥቅስ፡ መዝ18 ÷ 5

መዝሙር
የማኑ ተሐቅፈኒ
የማኑ ተሐቅፈኒ ወፀጋሙ ታተርስየ(2)
ትብሎ መርዐት ትብሎ(2) መርዐት ለመራዊሀ(2)
ትርጉም፡ ሙሽሪት ሙሽራውን ቀኝ እጁ
ታቅፈኛለች ግራ እጁ ትራስ ትሆነኛለች
ትለዋለች::
ጥቅስ፡ መኃ2÷6 መኃ8÷3

መዝሙር
ትብሎ መርዐት
ትብሎ መርዐት መራት ለመራዊሃ(2)
አፈቅሮ(4) አስከ አመ ፈቀደ(2)
ትርጉም፡ ሙሽሪት ሙሽራውን እሱ አሰከ ፈቀደ
ድረስ እወድሃለሁ ትለዋለች
ጥቅስ፡ 1ኛ ቆሮ7÷34-35

መዝሙር
ሙሽራው ከሁሉ
ሙሽራው ከሁሉ አማረ ተክሊሉ(2)
አማረ(4) ከሁሉ አማረ(3) ተክሊሉ(2)
እድገቱ ከገዳም ምግቡ ሕብስተ መና
መጠጡ አስካለ ወደን ኑሮው በምስጋና
ሙሽራው ከሁሉ.....
ጥንትም በተዋሕዶ ያማረ ነውና
ተሞሽሮ መጣ መላአክ መሰለና
ሙሽራው ከሁሉ.....
ጥቅስ፡ መዝ18÷5

መዝሙር
ካህናት ተንስኡ
ካህናት ተንስኡ(2) ለተናብቦ(2)
እንዘ ደበሉ ንሴብሆ(2)
ትርጉም፡ ካህናት ተነሱ....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ሐመልማለ ሐመልማል
ሐመልማለ ሐመልማል ሐመልማለ ወርቅ
ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ
ለቁርባን ለተክሊል በቅቶ መገኘት
ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ
የወንጌል ትዕዛዝ ነው የእምነት መሠረት
ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ
ሐመልማለ ሐመልማል.....
ድንግልናቸውን ጠብቀው ሳይስቱ
ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ
እኒህን አበቦች አሰቲ ተመልከቱ
ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ
ሐመልማለ ሐመልማል.....
አንድ ሰው ለአንድ ነው መጽሐፍ ያዘዘው
ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ
ካንድ በላይማ አመነዘረ ነው
ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ
ሐመልማለ ሐመልማል.....
እልል በሉላቸው ዛሬ ነው ደስታቸው
ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ
የተመረጡበት መልካም ጋብቻቸው
ልብሱ ዘመብረቅ ሐመልማለ ወርቅ
ሐመልማለ ሐመልማል.....
ጥቅስ ፡ 1ቆሮ7÷በሙሉ

መዝሙር
ከመቀናንሞ
ከመቀናንሞ(4) የሰራህ ቀምሞ
ከመቀናንሞ(4) የሰራሽ ቀምሞ
ቀናንሞ እኸ ቀናንሞ እኸ
የሙሽራው እኸ ቄሚ ቤቱ እኸ
የፀና ነው እኸ መሰረቱ እኸ
ከመቀናንሞ.....
ጉልላቱ እኸ ወርቅ ፈርጡ እኸ
ሙሽሪት ናት እኸ የሙሽራው እኸ
አምደ ጌጡ
ከመቀናንሞ.....
የወደን ሐረግ እኸ የወደን ዛላ እኸ
ሙሽሪት ናት እኸ የሙሽራው ጫማ ጥላ
ከመቀናንሞ.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ዳዊት ይቤብሕ
ዳዊት ይሴብሕ (2) ወይዜምር አዝራ(2)
እንዘ ደበሉ ሙሽራ ሙሽራ(2)
ትርጉም፡ ዳዊት ያመሰግን አዝራም ይዘምር ሙሽራ
ሙሽራ አያሉ
ጥቅስ መዝ18÷5

መዝሙር
ወረደ ወረደ
ወረደ (6) መና ዘካረያስ ወረደ(2)
እንዲህ ነው ጋብቻ ወረደ
ሲሆን በሥርዓቱ "
በቁርባን በተክሊል "
መወሰን መጽናቱ "
ወረደ.....
እፁብ ነው ድንቅ ነው ወረደ
እንደዚህ መጣመር "
በሀሳብ ተግባብቶ "
በፍቅር መታሰር "
ወረደ.....
ጥቅስ፡ ዕብ13÷4

መዝሙር
ሶበ ሰማዕነ
ሶበ ሰማዕነ ዜናከ መፃዕነ ሀቤከ(2)
መፃዕነ (4)
እንደ ሰባ ሰገል እንደ ሩቅ ምሥራቅ
ዝናህን በመስማት መጣን ልንጠይቅ
ሶበ ሰማዕነ.....
ብቻህን ስላየህ ፈጣሪ ቢወድህ
ከጉንህ አንስቶ ሔዋን ፈጠረልህ
ሶበ ሰማዕነ.....

አንቺ ቤተልሔም ቤተክርስቲያን/ተምሮ ማስተማር/
ያፈራሽው ፍሬ ልደቱ ደከበር
ሶበ ሰማዕነ.....
ውብ አሸከር አበባ
ሙሽራው አበባ
ውበቱ አበባ
ፈሰሰ አበባ
በአንገቱ አበባ
ሙሽሪት አበባ
ውበቷ አበባ
ፈሰሰ አበባ
በአንገቷ አበባ
ጥቅስ: ዘፍ2÷18

መዝሙር
አልቦም ጽምጽ
አልቦሙ ድምጽ ዘኢይሰማዕ(2)ድምፀ ክነፈሆሙ
አልቦሙ ድምጽ(2)
ዲበ ምድር(4) ሶበሰ ደወርዱ መላእክት(2)
ትርጉም: መላእክት ክንፋቸውን ዘርግተው
ደወርዳሉ ድምፃቸውን ግን አይሰማም
ጥቅስ: ኢሳ6÷3

መዝሙር
አስመለዓለም
አስመ ለዓለም አኽ አስመለዓለም(2)
ለዓለም ለዓለም አስመ ለዓለም ለዓለም
በሉላቸው(2)
ሙሽራው መልካም አኽ ሙሽሪት መልካም አኽ
ለዓለም(2) አስመ ለዓለም በሉላቸው
አስመ ለዓለም.....
ደስ ይበለን በጣም አኽ አይግባን ፈሪቻ አኽ
ጌታ ባርኮልናል አኽ ቅዱሱን ጋብቻ አኽ
ቃና ዘገሊላ አኽ ከእናቱ ጋር ገብቶ አኽ
ውኃውን ለወጠ አኽ ወደ ወይን አስታክቶ አኽ
ለዓለም(2) አስመ ለዓለም በሉላቸው
አስመ ለዓለም.....
ሙሽራው መልካም አኽ ሙሽሪት መልካም አኽ
ለዓለም(2) አስመ ለዓለም በሉላቸው
አስመ ለዓለም.....
ጋብቻችሁ ደመር አኽ በዓለም ይዳረስ አኽ
ይነገር ስብከቱ አኽ ጽፎታል ጳውሎስ አኽ
ዳዊትም ይጠራ አኽ በገና ይደርድር አኽ
በመዝሙር ይፈክር አኽ ትንቢትም ይናገር አኽ
ለዓለም(2) አስመ ለዓለም በሉላቸው
አስመ ለዓለም.....
ሙሽራው መልካም አኽ ሙሽሪት መልካም አኽ
ለዓለም(2) አስመ ለዓለም በሉላቸው
መድኃኔዓለም ይምጣ አኽ ይስራ ጥበቡን አኽ
በግብዣችሁ ጥሪት አኽ ድንግል ማርያም አኽ
ሐዋርያት ይምጡ አኽ ፃድቃንም ይጠሩ አኽ
ጋብቻችሁ ደመር አኽ መልካም ዘርን አፍሩ አኽ
ለዓለም(2) አስመ ለዓለም በሉላቸው
አስመ ለዓለም.....
ሙሽራው መልካም አኽ ሙሽሪት መልካም አኽ
ለዓለም(2) አስመ ለዓለም በሉላቸው
ጥቅስ: ዮሐ2÷1-11 ዕብ 13÷4

መዝሙር
ንሴብሐ ለአምላከ አዝራ
ንሴብሐ ለአምላከ አዝራ(2)
እሱን ለፈጠረ አሷንም ለሰራ(2)
ንሴብሐ ለአምላከ አዝራ(2)
ጥቅስ:

መዝሙር
ወገዳሙኒ
ወገዳምኒ ገዳምኒ አንትሙ
ለዓለም ብርሃኑ(4) አንትሙ ለዓለም ብርሃኑ
እሰቲ በስመ አብ ብለን እንጀምር ሰላምታ
ለተቀመጥንበት ለዚህ ተክሊል ቦታ
እሰቲ በስመ አብ ብለን እንጀምር ፀሎት
ውዳሴ ወግናይ ዐሥርቱ ቃላት
ወገዳምኒ.....
ሰው ብቻውን አይኑር ከንቱ ነው ዓለሙ
ጋብቻ መልካም ነው በሥጋወደሙ
ብቻውን እንዳይሆን ሰው እንዳይጐዳ
ሔዋን ተፈጠረች አዳምን ልትረዳ
ወገዳምኒ.....
ጋብቻ ክቡር ነው መኝታው ንፁህ
ሙሽራው ተደሰት ይመር ዘመንህ
ወገዳምኒ.....
የቤተ ክርስቲያን ተዋህዶ ጋብቻ
በሥጋ ወደሙ ያውም አቻ ለአቻ
ሙሽራው አልል በል ደስታ ይብዛልህ
ትዕዛዙን አክበረህ በድንግልናህ
በወንጌል ያለውን አንብበህ ሰምተህ
ለቅዱስ ጋብቻ ለዚህ ተመረጥክ
ወገዳምኒ.....
ሙሽሪት ሙሽራው አምሮአል ጋብቻችሁ
ግሩም ነው ድንቅ ነው ለዚህ መብቃታችሁ
ወገዳምኒ.....
ውግዝ ነው ኃጢአት ነው ከአንድ ሰው ማስፍ
አንድ አካል እንዲሆን አዛል መጽሐፍ
አንድ እንሆናስን ከቀደሙት ጋራ
ከአብርሃምና እንዲሁም ከሣራ
ወገዳምኒ.....
ሙሽው መልካም ነው ሙሽሪት ብርክት
እንመኝላቸው ጤናና ሕይወት
መልካም ዘር ከነርሱ ፍሬ በረከት
እንዲያገኙ ይሀን በፍፁም ስብሐት
ወገዳምኒ.....
ጥቅስ:

መዝሙር
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ልጆች
ናቸው እንቀበላቸው
ሙሽሮች ናቸው እንቀበላቸው
ያውና በድንግልና
ፈፀሙ ስጋ ወደሙ
ለዚህ ዕድል ተዘጋጁ

የሕይወት አክሊል ተቀዳጁ
የኢትዮጵያ.....
እንዘምር በከበሮ
ፍሬ ናቸው የተምሮ
አልል በሉ ሚዜዎች
አብሮ አደጐች ጓደኞቼ
አልል በሉ ሚዜዎቿ
አብሯ አደጐች ጓደኞቿ
የኢትዮጵያ.....
ጥቅስ፡ ማቴ 19÷1-6

መዝሙር
ሕላዌ ዘአብ
ሕላዊ ዘአብ ወሕላዌ ዘወልድ ዘመንፈስ ቅዱስ(2)
ንትቀበል መራአዊ ሰማያዌ (2) አዶናይ ወቢይ ኖላዊ
ትርጉም፡ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በባሕሪ
በሕልውና አንድ የሚሆን ትልቁ
ጠባቂያችን አዶናይ የሚባል ሰማያዊ
ሙሽራ ወልድን እንቀበለው።
ጥቅስ፡ ማቴ 25÷1-6

መዝሙር
ትዌድሶ መራት
ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ(2)
ወልድ አሁየ ቃልከ አዳም(2)
ትርጉም፡ ሙሽሪት ሙሽራውን ወንድሜ ድምጽህ
ያማረ ነው ትለዋለች።
ጥቅስ፡ መሐልየ 5÷6

መዝሙር
የሀብ ከዮም
የሀብ ከዮም የሀብከ መድኃኔዓለም(2)
ዕድሜ ማቱሳላ ወአብርሃም(2)
ይስጣችሁ ዛሬ ይስጣችሁ መድኃኔዓለም(2)
ዕድሜ ማቱሳላ የአብርሃም(2)
በቅዱስ ጋብቻ ሙሽሮች የተወሰናችሁ
ክርስቶስ ተገኝቷል በመካከላችሁ(2)
የድንገሮቹን ጋን ወይኑን (2) ሊሞላበት
ከድንግል ማርያም ጋር ተገኝቷል ሠርግ ቤት(2)
የሀብ ከዮም.....
ደስታውን አይቶ አምላክ ፍፁም ተደስቷል(2)
ሊባርካችሁም እጆቹን ዘርግቷል
ሕይወታችሁም <u>ፍቅር</u>(2) በመሆኑ
ትሕትናን ይስጣችሁ እግዚአብሔር በቶሎ(2)
የሀብ ከዮም.....
ሠርጋችሁ እንዲሆን ደስታ ፍቅር የተመላበት
በሕይወታችሁ ውስጥ ክርስቶስ ይግባበት
" " አምላክ ይኑርበት
የሀብ ከዮም.....
የበረከት ፍሬ በፀጋ እንዲበዛላችሁ
ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ(2)
አራስን በመግዛት <u>አሙቀት</u>(2) ተመልታችሁ
ዛሬ ተደሰቱ አምላክን ይዛችሁ(2)
በሥጋወ ደሙ እግዚአብሔር ስለመረጣችሁ
የመንፈስ ቅዱስ ሕፃናቶች ናችሁ(2)
የሃብ ከዮም.....

መዝሙር
በሠርጋችን እለት
በሠረጋችን ዕለት እንድትባርከን
ጌታ ጠርተንሃል በአምነት ሆነን
ከአናትህ ጋራ ከአመቤታችን
ከመላአክት ጋር ና በሠርጋችን
ከሐዋርያት ጋር ና በሠረጋችን
ከወዳጆችህ ጋር ና በሠርጋችን
በሠርጋችን.....
በገሊላ መንደር እንደተገኘህ
ና በኛ ድንኳን ውስጥ ጌታ ስንጠራህ
ስለ አናትህ ብለህ ጌታችን እንዳትቀር
አንተ ነህ ክብራችን የቤታችን ፍቅር
በሠርጋችን.....
ነይ ከልጅሽ ጋራ አመቤታችን
እንድታሟይልን የጐደለውን
ንገሪው ለልጅሽ ባዶው እንዲሞላ
በረከት የአርሱ ነው ቤታችንን ይሙላ
በሠርጋችን.....
በጎደው ሁሉ አየጨመርሽልን
ቤታችን ሙይው ድንግል አናታችን
ለአገልጋዮቹ ድንግል ንገሪያቸው
ጠርተን እንዳናፍር ጋኖቹን ይሙሳቸው
በሠርጋችን.....

መዝሙር
ሙሽራዬ
ሙሽራዬ(3) አበባዬ (2)
ከገንህ የምትሆን አህት አገኝህ
የኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለህ
የእግዚአብሔር ፈቃዱ ለዚህ ካበቃችሁ
ቤታችሁ ይመረቅ በፍቅር ያጽናችሁ
ሙሽራዬ.....
ወንድም አግኝተሻል የማያስብልሽ
የኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለሽ
እግዚአብሔር ይመስገን አኛም ደስ ብሎናል
በቤተክርስቲያን ሠርጋችሁ ውብ ሆኗል
ሙሽራዬ.....
እንደ ነፍስህ አርገህ እንድትወዳት
አደራ ሰጠንህ በጌታችን ፊት
እንድታስቢለት አንቺም ለአካልሽ
አደራ ትላለች ወንጌል አናትሽ
ሙሽራዬ.....
በስጋ ወደሙ ሕይወት አግኝታችሁ
ፍሬአችሁም ይብዛ ይባረክ ጓዳችሁ
አምላክ ያለበት ነው ይሔ ጋብቻችሁ
አስከ መጨረሻው ኑሩ ደስ ብሏችሁ
ሙሽራዬ.....
ጥቅስ፡ ዘፍ 2÷18

መዝሙር
ደስ አላት
ደስ አላት ቤተክርስቲያን በጣም ደስ አላት(2)
ሙሽራት ሙሽራው ልጆቿ(2) በተክሊል በቁርባን
ተዋሀዱላት(2)
ጥቅስ፡ ማቴ 19÷6

መዝሙር
ንጽሕይት ድንግል
ንጽሕይት ድንግል ብርክት
የአምላክ እናት እመቤት
ልጆችሽ ሙሽሮች ሁስቱም አንድ ሆኑ
ተዋሀዱ ተጣመሩ በቅዱስ ቁርባኑ(2)
ፍፁም መንፈሳዊ ልዩ ፍቅር
አንቺ ያስሸበት መልካም ትዳር
መሠረቱ ዛሬ ልጆችሽ
ቅድስት ሆይ ባርኪያቸው ተገኝተሽ
ንጽሕት.....
ድንግል ጎጆአቸውን ቀድሰሽ
እውነትኛ ፍቅር መስርተሽ
በመካከላቸው ተገኝተሽ
ሁሱን አሰጫቸው አማልደሽ
ንጽሕት.....
ሙሽሮቹ አምነው በምልጃሽ
እናታችን ባርኪን ነይ ሲሱሽ
ፈጥነሽ ድረሽና በሠርጋቸው
ነይ ተመላለሽ መሀላቸው
ንጽሕት.....
አንቺን ለሚወዱሽ ለሚያምኑሽ
የሕይወት አጣፋጭ ቅመም ነሽ
ሙሽሮቹም አምነው ይጠሩሻል
የገጆአችን ፋና ነሽ ይሱሻል
ንጽሕት.....
ቃና ዘገሊላ ተገኝተሽ
መልካሙን ጋብቻ የስባረክሽ
ዛሬም ከልጀሽ ጋር በሠርጋቸው
ነይ ተመላለሽ መሀላቸው
ንጽሕት.....

መዝሙር
ሥላሴ ይባርኳችሁ
ሥላሴ ይባርኳችሁ(2)
በሥጋዉ ደሙ ዛሬ ከበራችሁ ሥላሴ ይባርኳችሁ
እመ አምላክ ትከተለልህ(4)
ፈተና እንዳይገጥምህ ድንግል ትከተልህ
እመ አምላክ ድንግል ትከተልና

ቍ ሚካኤል በኑሮአችሁ(4)
ቍ አርምሞ ማስተዋል ትዕግሥቱን ይስጥችሁ
ቍ ሚካኤል ይባርካችሁ

ቍ ገብርኤል ከሳይ ወርዶ(4)
ቍ አርሱ ይራዳችሁ በክንፎቹ ጋርዶ
ቍ ገብርኤል ከሳይ ወርዶ

ቍ ዑራኤል በምልጃው(4
ቍ የዕውቀትን ጥበብ ይስጥህ በምልጃው
ቍ ዑራኤል በምልጃው

ቍ ጊዮርጊስ አይለያችሁ(4)
ቍ በመከራ ጊዜ ጽናት ያሳያችሁ
ቍ ጊዮርጊስ አይለያችሁ
ቍ ተክለ ሃይማኖት በፀሎት(2)
ቍ ያግዟችሁ ዘውትር ሆነው አረዳት
ቍ ተክልዩ በፀሎት
ሥላሴ ይባርኳችሁ(4)
በስጋዉ ደሙ ዛሬ ከበራችሁ
ሥላሴ ይባርኳችሁ

መዝሙር
ሰናይ በዜና
ሰናይ በዜና(6)
ሰናይ በዜና አምሮ ደምቆ መጣ ሰናይ በዜና
" አየገሰገሰ "
" አልል በሉ ሰዎች "
" ሙሽራው ደረሰ "
ሰናይ በዜና.....
ሰናይ በዜና ቃና ዘገሊላ ሰናይ በዜና
" ስሠርግ የታደመ "
" ጌታችን ክርስቶስ "
" አዚህም ደገመ "
ሰናይ በዜና.....
ሰናይ በዜና ተነሱ እናመስግን ሰናይ በዜና
" አንዘምር ዘምሩ "
" የአምላክነቱን "
" መልካም ዜና አብስሩ "
ሰናይ በዜና.....

መዝሙር
በከመ ይቤ
በከመ ይቤ ዳዊት በመዝሙር(2)
አንተ ካህኑ ስዓስም(2)
በሥጋ ወደሙ ቀደሱ ቅዱሱን ጋብቻ
ሆነዋልና አቻ ሳቻ(2)
አኽ በከመ ይቤ.....
ፅድሜና ጤና ይስጣችሁ በቸርነቱ(2)
አንዳይነሳችሁ ከበረከቱ(2)
አኽ በከመ ይቤ.....
ቤተ ክርስቲያን ቅድስት ያገለገሏት
ይኸው ቆማለች ፊት ለፊት(2)
አኽ በከመ ይቤ.....
መልካሙን ፈሬ አንዲያዩ አንዲሰጣቸው(2)
ይበል ይበል(2) በሉላቸው(2)
አኽ በከመ ይቤ.....

መዝሙር
ነውና እና ልጃችን
ነውና እና ልጃችን ስሙ የተጠራ2)
አንበል ሁሳችን ሙሽራ ሙሽራ(2)
አሱ አመሮበታል አዎ
ፀጋ አድሮባታል አዎ
ሁሱን አውቆበታል አዎ
አሸብርቆ ደምቂል አዎ
ተይ ደምቂል(2) አዎ
አሳየንም አንደ አርሱ አሳየንም(3)
ነውና ለጃችን.....
ሙሽሪት አህት አዎ
የአርሱ ባለቤት አዎ
ውበት ውበት ሆነች በውበት(2)
ያው አምራለች ከፀሐይ ደምቃለች

ያው አምሯል ከፀሐይ ደምቋል
ነውና ልጃን.....
ለሠው ሙሽርነት አዎ
በጣም ደስ የሚለው አዎ
የሚለው(2)
በተክሊሉ በቁርባን ሲሆን ነው(2)
ነውና ልጃን.....

መዝሙር
ሙሽራው አሸበረቀ
ሙሽራው አሸበረቀ (2)
በሙሽሪት ይህው ደመቀ
ሁለቱም ተስማሙ በስጋ ደሙ
ሁለቱም አንድ ሆኑ በስጋ ደሙ
ሙሽራው.....
በቅዱስ ቁርባን ቀደሱት ሠርጉን
አንድ አካል አንድ ሀምሳል ሆነው በተክሊል
ሙሽራው.....
ከመኖር ለብቻ በቅዱስ ጋብቻ
ከመኖር ለብቻ መጋባት ለአቻ
ሙሽራው.....
ፍቅር ሰራ ቤቱን በተክሊል ሥርዓት
አልል በሉሳቸው የተዋህዶ ናቸው
ሙሽራው.....
አምላክ የባረከው ጋብቻ ይኼ ነው
መጡ የምሥራች የተዋህዶ አበቦች
መጡ የምሥራች የወንጌል ፍሬዎች
ሙሽራው.....

መዝሙር
አንዘምር በአልልታ
አንዘም በአልልታ አንዘምር በከበሮ(2)
ሥርዓት ፈጽሞ ሕግን አክብሮ መጣ (ሔደ)
ሙሽራው አምሮ(2)

መዝሙር
ወይቤሳ መርአዊ
ወይቤሳ መርአዊ ለመርአት(2)
እኅ ንዒ ንሁር ሀበ ደብረ ከርቤ ወደብር(2)
በደብረ ስሂን ቅድስት(2)
ትርጉም፡ ሙሽራው ሙሽሪትን ...

መዝሙር
በቃና ዘገሊላ
በቃና ዘገሊላ(2) በዚያ በሠርግ ቤት
ተገኝተሻል ድንግል ክልጅሽ ጋራ
ተገኝተሀል ጌታ ከናትህ ጋራ
እድምተኞች ሞልተው በተጋበዙበት
ሲበሉ ሲጠጡ ወይኑ አልቆበት
ድንግል እናታችን ቤዛዊት ዓለም
በመከራ ደራሽ እንደ አንቺ የለም
በቃና .....
አንተ እያለህስ ማፈር የለባቸው
ሁሉ ይቻልሀል ወይኑን ሙሳላቸው
ማድጋው ባዶ ነው ብለሽ የተናገርሽ
ጌታን ያሳሰብሽው አመቤታችን ነሽ
በቃና .....
የጌታ አምላክነት የተገለጠበት
ምንኛ ታደለ የነ ደኪማስ ቤት
ዛሬም ይህው በዚህ በሠርገኞች ቤት
በረከት ፈሰሰ በአምላክ ቸርነት
በቃና .....
ውሀው ተለውጦ የወይን ጠጅ ሲሆን
በቃና ገሊላ ሁላችን አየን
እግዚአብሔር ከኛር በመካከላችን
ሁሌም ይሠጠናል ይህን መሠል ወይን
በቃና .....

መዝሙር
ሙሽሮች እንኳን ደስ
ሙሽሮች እንኳን ደስ አላችሁ
ለዚህ ቀን ይኸው ደረሳችሁ
በአምላክ ፊት እጅግ ከበራችሁ
በእግዚአብሔር ቸርነት በመልካም ፈቃዱ
በቅዱስ ቁርባኑ ዛሬ ተዋሀዱ(2)
በሥርዓተ ተክሊል በሥጋ ወደሙ
በመድኃኒዓለም ፊት ጋብቻ ፈፀሙ(2)
ሙሽሮች.....
በቤተክርስቲያን በፈጣሪያቸው ፊት
ሁለቱም አንድ ሆኑ በዚህ ቅዱስ ዕለት(2)
አንድ የሚያደርጋቸው ተነቦ ወንጌሉ
በካህኑ መስቀል በረከት ታደሉ(2)
ሙሽሮች.....
በወንጌሉ ትእዛዝ በሐዋርያት ቃል
በአመብርሃን ፊት ቃብቻችሁ ፀድቋል(2)
በአምላክ ሥጋና ደም ሁለቱም ታተሙ
የህብረት ቃል ኪዳን በአንድነት አሰሙ(2)
ሙሽሮች.....
አፀንቶ የሚያኖር የማይለያያቸው
ክቡር ቃል ስላለ በመካከላቸው(2)
እስከ መጨረሻው አንድ አካል ሆነዋል
የአማኑኤል ሥጋ አስተሳሰሯቸዋል(2)
ሙሽሮች.....

መዘሙር
የምስራች ደስ ይበላችሁ
የምስራች ደስ ይበላችሁ(2)
አሸብርቆ ዋለ ሙሽሮች ሠርጋችሁ(2)
ሕይወታችሁ ሠላማዊ ፍፁም ፍቅር(2)
እንደ ፅጌረዳ እንዳደይ ፈክቶ የሚኖር
አማኑኤል ያድርገው መልካም ትስስር
የምሥራች.....
መተሳሰብ መከባበር ይሁን ግብራችሁ(2)
ሠርጎ አንዳዳይገባ ዲያብሎስ በትዳራችሁ
በፃም ፀሎት ይታጠር ሙሽሮች ጎጆአችሁ
የምሥራች.....
አይኖቻችሁ የገረቤት አይመልከቱ
ለወሬ ለሐሜት ጆሮቻችሁ አይከፈቱ
በሐዘን በደስታ በፃም ፀሎት በርቱ
የምሥራች.....
እግሮቻችሁ ይገስግሱ ወደ እውነት(2)
አማናዊ ማእድ ክርስቶስ ወዳለበት

በልባችሁ አኑሩት ታላቁን አባት
የምሥራች.....
ድንግል ማርያም ቅድስት እናት ለምኝላቸው(2)
የሚፈልጉትን ሁሉ አንቺ አሰጫቸው
በሠማይ በምድር ምልጃሽ አይራቃቸው
የምሥራች.....

መዝሙር
አጅቡት በልልታ
አጅቡት በልልታ ሲመጣ ሙሽራው
ፍፁም የማያስደስት የሠርጉ ዕለት ነው
ዘመዶቹ ሁሉ ተቀበሉት ውጡ
የሙሽራው መምጫ አሁን ነው ሰዓቱ
እልል(2) እንበል እንዘምር በደስታ
ይህን ላደረገ ለሠራዊት ጌታ
ሁሉንም በጊዜው ደፈፅማልና
ይኸው አበቃቸው ለዚህ መልካም
ዜና(2)
ሙሽሪት ተደሰች ዝምታው ምንድን ነው
የዳግም ልደትሽ የሠርግሽ ዕለት ነው
አዳም ጎንሽ ቆሞ ሔዋን ሆይ ሲልሽ
መንፈሳዊ ሐሴት ይሙላ በልብሽ
እልል(2) እንበል.....
እህት ወንድሞቿ አናትና አባቷ
ተነሱ ዘምሩ ለልጃችሁ ደስታ
መግባቷ ነውና ወደ ቤቷ ዛሬ
ወደ አዲስ ጎጆዋ ሸኟት በዝማሬ
እልል(2) እንበል.....
ቤተሰቦችሽን ሁሉንም ትተሽ
መሄድሽ ነውና ወደ መኖሪያሽ
ከአማኑኤል ጋራ ባልሽን ይዘሽ
ተነሽ አህቴ ሆይ ደረሷል ሠዓትሽ
ከድንግልም ጋራ ሚስትህን ይዘህ
ተነስ ወንድሜ ሆይ ደርሷል ሠዓትህ
እልል(2) እንበል.....

መዝሙር
ደመቀ አበራልን
ደመቀ አበራልን የአማኑኤል ሥራ(2)
ሙሽሮቹ ሆኑ አብርሃም ወሣራ(2)
ቤተክርስቲያን ጥሳ ተከልስው
ተክሊል አድርገዋል ሙሽሪተ ሙሽራው
ፀጋ መንፈስ ቅዱስ ስለተሰጣቸው
ሙሽሪት ሙሽራው አበራ ገፃቸው
ደመቀ አበራልን.....
የተራራቀ አካል አንድ ሆነ በተክሊል
እግዚአብሔር ይመስገን እልል እልል እንበል
አጥንትሽ ከአጥንቴ ሥጋሽ ከሥጋዬ
አዳም የሰበከው ይኸው ዛሬ ታዬ
ደመቀ አበራልን.....
የተክሊል ብርሃኗ በኛ መሐል በርቶ
ረቂቅ አንድነት ታየ በሷ ጕልት
ይህን ድንቀ ነገር ለማየት ያበቃን
ምሥጢሩን የሚገልፅ እግዚአብሔር ይመስገን
ደመቀ አበራልን.....
ነጭ መጎናፀፊያ በአንድ ተጎናጽፈው
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አረ፤ በጥላው
ሙሽሪት ሙሽራው ስፍቅር ተሸነ፤
ለቀርባን መቀረቢያ ነጭ ነልስ አሰ፤
ደመቀ አበራልን.....

መዝሙር
አቤቱ ምሕረትህን
አቤቱ ምሕረትሕን ከኔ አታርቅብኝ
ቸርነትህና ይቅርታህ ይጐብኙኝ
ኃጢአቶቼም ያዙኝ ማየትም ተሳነኝ
አንደ ራሴ ፀጉር በላዬ ከበቡኝ
አንዳልቀር ወድቄ በደሌ ጨልሞኝ
የድኀነቴ ፋና አምላኬ አንተ ሁነኝ
ጥቅስ፡ መዝ50÷1

መዝሙር
አንደ ቸርነትህ
አንደ ቸርነትህ አቤቱ ማረኝ(2)
አንደ ምህረትህም ይቅርታን ስጠኝ(2)
ከኃጢአቴም አንፃኝ ከብዙ በደሌ(2)
ስዚያች ክፋ ኃጢአት አንዳልሆናት ሎሌ(2)
አኔስ አመፃዬን በደሌን ሳውቀው(2)
ከቶ የሚያድነኝ ቸርነትህ ነው(2)
አንተን ብቻ በደልኩ ክፋም አደረግሁ(2)
አሁን ይቅር በለኝ ከፊትህ ወደቅሁ(2)
ከፊትህ ወድቄ ስለምን አንተን(2)
መውደቄን ተመልከት አምላክ ብርሃን(2)
ጥቅስ፡ መዝ50÷1

መዝሙር
አባቴ ሆይ
አባቴ ሆይ መጥቻለሁ ይቅር በለኝ በድያለሁ(2)
አባቴ ሲቆጣኝ አልመለስ ብዬ
አልሰማሽም አያልኩ ስትመክረኝ አምዬ
ከወንድሜ ጋራ ሐብቴን ተካፍዬ
ከሰው አገር ሔድኩኝ ከአባቴ ኮብለዬ
አባቴ ሆይ.....
የአናት የአባቴን ሀብት በገፍ ተሸክሜ
ከጋለሞቶች ጋር ስጨፍር ከርሜ
ሀብቴ ተጨርሶ ንብረቴ ሲጠፋ
ጓደኞቼም ጠሉኝ መውደቂያዬም ከፋ(2)
አባቴ ሆይ.....
የማይጐዳኝ መስሎኝ የሲኦል መከራ
ኮብልዬ ነበር ወደ ኃጢአት ጐራ
አሁን ግን ተመለስኩ ጥፋቴን አውቄ
የሰማይ አባቴን ይቅርታ ጠይቄ
አባቴ ሆይ.....
አባቴ ሆይ ማረኝ በቸርነትህ
ቂም አንዳትይዝብኝ በደሌን ቆጠረህ
ስለማይገባኝ ስመባል ልጅህ
ቁጠረኝ አንደ አንዱ ከአገልጋዬችህ
አባቴ ሆይ.....
ይቅር ባይ ነህና የበደሉህን
ከሞት ወደ ሕይወት መልሰህ አኔን
አባት ሆይ ጥራቸው መላአክትህን
ስለ አኔ በሰማይ ደስታ ይሁን(2)
አባቴ ሆይ.....
ጥቅስ፡ ሉቃ 15÷11-24

መዝሙር
ጊዜዬ እስኪደርስ
ጊዜዬ እስኪደርስ ወደ አንተ መምጫዬ
ለንስሃ አብቃኝ አቤቱ ጌታዬ(2)
ብርሃኔና መድኃኒቴ ተስፋህ ይመልሰኝ
ክፋቴን ደምስሰህ ይቅርታ አድርግልኝ
ተስፋዬ አረዳቴ አንተ አትጣለኝ
አምላኬ አታጥፋኝ ከሲዓል አድነኝ
ጊዜዬ.....
መሀሪ ይቀር ባይ ምሕረትህ ይጐብኘኝ
ከሀጢአት ፈላፃ ኃይልህ ይታደገኝ
አዳኜ መድኃኒቴ ሰላምን ላክልኝ
የድህነት ደጆችህን በፍቅር ክፈትልኝ
ጊዜዬ.....
አቤቱ ምሕረትህ በአኔ ላይ ይሁን
ተጨነቅሁ _____አስከ ዘለዓለም
ከክፋ አንድሸሽ አርቀኝ አኔን
በጐ አንድሰራም ምራኝ መንገድን
ጊዜዬ.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
መቼ ነው ጌታ
መቼ ነው ጌታ አረ መቼ ነው (2)ጌታዬ
አንደ ቃልህ የሚሆን ጉዞዬ
አልተማርኩም አልል አስተምረህኛል(2)
ቃልህን አንደ ወተት አጠጥተህኛል(2
መቼ ነው.....
የታስ አኗኗሬ አንተን የሚመስለው (2)
በልማድ ሕይወት ነው የምመሳሰሰው(2)
መቼ ነው.....
ይህ አንደበቴማ በቃልህ ሰልጥኗል(2)
ልቦናዬ ካንተ ከፊትህ ኮብልሏል(2
መቼ ነው.....
አንተን አንደማውቅህ አብዝቼ ባወራ(2)
የተዘራ ሁሉ ፍሬን አሳፈራ(2)
መቼ ነው.....
አዘንልኝና መንገዴን አቅናልኝ(2)
የአመጽ ሥራዬን በደሌን ተውልኝ(2)
መቼ ነው.....
- ቃልህ አንዳይሰደብ በአኔ ድካም
-

መቼ ነው.....

መዝሙር
አንደ በደሌማ
አንደ በደሌማ ከሆነ ቅጣቴ
አያልቅም ተነግሮ ብዙ ነው ጥፋቴ
አንጃልኝ ፈራሁኝ አዬ ሰውነቴ
አመለሳለሁኝ አያልኩኝ ጠዋት ማታ
ዘመኔን ጨረስኩኝ ሳስብ ሳመነታ
ምን አመልስ ይሆን የተጠራሁ ስታ
በላዬ ሲያንዣብብ ሞት አጁን ዘርግቶ
ሥጋዬን ሲውጠው መቃብር ተከፍቶ

የነፍሴ ማረፊያ ወዴት ይሆን ከቶ
ይቅር ባይ ነህና የበደሉህን
አቤቱ ጌታ ሆይ አኔን ባሪያህን
ይቅር በለኝ አና ልየው ፊትህን (2)

መዝሙር
ከአገልግሎት በፊት
አደባባይ ቆሜ ስምህን ከመስበክ
መጀመሪያ ልቤ ከፊትህ ይነበርከክ
ከአገልግሎት በፊት አንተን ልወቅህ
መስዋዕት ከማቅረብ ልታዘዝልህ
አሐዱ አብ ብዬ ስምህን ብቀድስ
ለድሆችም ብሰጥ ቤትህ ብገሰግስ
በመላዕክት ልዛን ብዘምር በአልልታ (2)
ከበሮ ብመታ
ምን እጠቅምሀለሁ ካልፈራሁህ ጌታ
ከአገልርሎት በፊት.....
ተራራ አስካፈልስ አምነት ከሌለኝ
ሥርዓት ከሌለበት ምንም አደጠቅመኝ
ልቤን ስትመረምር ከኮሆንኩኝ ቀላል
ክርስቲያን መባሉ ምን ይጠቅመኛል
ከአገልርሎት በፊት.....
ሰው አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል
ከውጭ ተጥሎ በእግር ይረገጣል
አንተን ለሚከተል አንዳልሆን አንቅፋት
አምልኮቴ ይሁን በፍቅር በፍርሀት
ከአገልርሎት በፊት.....

ጥቅስ:

መዝሙር
አዕቀድም
አዕቀድም አኩቶቶ ለእግዚአብሔር(2)
በአንተ አግዚአነ ኢየሱስ ክርስቶስ(2)
ትርጉም፤-ለስ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ
ክርስቶስ ምሥጋና ለእግዚአብሔር
አስቀድማለሁ
ጥቅስ፤- መዝ 103/104/÷8-22
1ኛ ቆሮ 1÷4 ራዕ 7÷9-17

መዝሙር
እግዚአብሔር የሃበነ
እግዚአብሔር የሀበነ ልሳነ ጥበብ(2)
ከመ ናአምር ሕጋ(2) ለቤተክርስቲያን(2)
ትርጉም፤-እግዚአብሔር የጥበብ እንደበትን
ይስጠን የቤ/ክ ህግ አናውቅ ዘንድ
ጥቅስ፤- ሮሜ 2÷12-16 ያዕ 1÷22-25

መዝሙር
ሃበነ እግዚኦ
ሃበነ እግዚኦ አአምሮ እይአንተ አአምሮ
ወትረ ኪያከ ይርአ(2)
ወአህዛን ነሂ ቃለ ዘባህቲትከ ይስምአ(2)
ትርጉም፤- አቤቱ ጌታ ሆይ የአውቀት አይኖችን
ስጠን አንተን ብቻ ያዩ ዘንዴ
ጆሮአችንንም ያንተን ቃል ብቻ ይሰሙ
ዘንድ::
ጥቅስ፤- 1ኛ ጴጥ 3÷10-12

መዝሙር
እግዚአብሔር ዓቢይ
እግዚአብሔር ዓቢይ (2)ወዓቢይ ኃይሉ (2)
ወአልቦ ሙልቁ(4) ሙልቁ ለጥበቢሁ(2)
ትርጉም:

ጥቅስ:

መዝሙር
ከጌታዬ ፍቅር
ከጌታዬ ፍቅር የሚለየኝ ማን ነው(2)
መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው(2)
አንፈራም አንሠጋም አንጣራጠርም(2)
እግዚአብሔር ከእኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም(2)
የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሠራው(2)
ግንቡ ንፁህ ውኃ መሠረቱ ደም ነው (2)
ሳይነጋ ተራምደን እንግባ በጧት(2)
በደሙ መስርቶ ከሰረልን ቤት(2)
ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት(2)
የውኃ ግድገዳ የደም መሠረት(2)
የውኃ ግድገዳ የደም መሠረት(2)
ይህው እዚህ አለ የአማኑኤል ቤት(2)
ጥቅስ፤- ሮሜ 8÷36

መዝሙር
የኃያላን ኃያል
የኃያላን ኃያል(3) ልዑል እግዚአብሔር
ተአምራተ ብዙ በሰማይ(2)በምድር(2)
ለአብና ለወልድ(3) ለመንፈስ ቅዱስ
መስገድ ይገባናል በሥጋ በሥጋ በነፍስ(2)
ለእግዝእትነ ማርያም(3) ለአምላክ እናት(2)
መስገድ ይገባናል የጸጋ ስግደት(2)
ለፃድቁ አባት(3) ለተክለሃይማኖት(2)
መስገድ ይገባናል የአክብሮት(2) ስግደት(2)
ለቀዳሚ ሰማእት(2) ለእስጢፋኖስ
መስገድ ይገባናል የአክብሮት (2)ስግደት
ጥቅስ: ዮሐ 4÷19-26 ሉቃ1÷44

መዝሙር
አንስገድስት
አንስገድስት የአምልኮት ለመድኃኔዓለም(2)
ብርሃን ስለሆነ መድኃኒት ለመላው ዓለም(2)
አንስገድሳት የፀጋ ለእምላክ እናት(2)
አክብሯት ነውና ፈጣሪ ከሴቶች መርጧት(2)
አንስገድስት የአክብሮት ለቅዱስ ጊዮርጊስ(2)
የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅዱስ ዘልዳው ንጉስ(2)
ጥቅስ: ሮሜ 13÷7

መዝሙር
አትልፊ በከንቱ
አትልፊ በከንቱ አትድከሚ ዓለም(2)

ቆርጫለሁ እኔ ከጌታ አልለይም(2)
እኔ አልጠበብም አልደለልም
ልቤ እያወቀ አምላኬን አልክድም
ዓለምን ለመምሰል አምነት አለውጥም
በከንቱ ማባበል ከመንገዱ አልወጣም
አትልፌ.....
ሥጋዊ ፈላጐት አያታልለኝም
ዓለማዊ አውቀት አያስታብየኝም
እነዚህ በአንድነት ይጠፋሉ ሁሉም
የእግዚአብሔር ጽድቅ ግን ይኖራል ዘለዓለም
አትልፌ.....
ሰውን ለማስደሰት ትዕዛዙን አልጥስም
በከንቱ ማባበል ከመንገዱ አልወጣም
ለዲያብሎስ እጄን በፍፁም አልሰጥም
ጌታ አግዚአብሔርን አሳሳዝነውም
አትልፌ.....
ከቅዱስ አግዚአብሔር እኔ አልለይም
በምድር በሰማይ ያለርሱ አልኖርም
መመኪያዬ እርሱ ነው ባዝንም ብተክዝም
ሕይወቴ ጌታዬ ያለርሱ አልኖርም
አትልፌ.....
ጥቅስ፡ 1ዮሐ 2÷15-17

መዝሙር
ለሞተለት አምላክ
ለሞተለት አምላክ የማይገዛለት(2)
ጨለማን መረጠ(2) ብርሃን አያለለት
ማን ይሰቅለው ነበር በገዛ ሥልጣኑ(2)
ለኛ ሲል ነው እንጂ(2) እንደዚህ መሆኑ
ፈጣሪስ አያጣም እርሱን የሚያመልከው(2)
ይልቅ ባያመልኩት(2) እራስን መጉዳት ነው
ለሞተለት.....
ጥቅስ፡ ዮሐ3÷35-36

መዝሙር
ዝናምን ለሚሰጥ
ዝናምን ለሚሰጥ ውኃን ከለከሉት(2)
ጠማኝ ሲል ቢናገር አጠጡት ሀሞትና ከርቤ
በደለኞች አይሁድ በአምስቱ ችንካሮች
ቸንክረውት በሰቀሉት ጊዜ
ጠማኝ ሲል .....
ጥቅስ፡ ማቴ27÷45-49

መዝሙር
አውረደ ሎቱ
አውረደ ሎቱ ለይለሀቅ ግዑዝ አቅረንቲሁ(2)
ቤዛሁ በግዓ በዕፀ ሳቤቅ(2)
ትርጉም፤- በእርሱ ፈንታ ለይለሐቀ ቀንዶቹ በዕፀ
ሳቤቅ የታሠረ በግ አወረደለት::
ጥቅስ፤- ዘፍ 22÷9-13

መዝሙር
ከአስርቱ ቃላት
ከአስርቱ ቃላት የመጨረሻው ቃል(2)
አትጣሉ ተፋቀሩ ይላል(2)
ጥቅስ፡ ዘሌ 19÷17-18 ማቴ22÷39-40
ዮሐ15÷12

መዝሙር
የሰው ልጆች ሁሳችን
የሰው ልጆቸ ሁሳችን እንማር
አስተባብረን ሃይማኖት ከምግባር
የሰው ልጆች ሁሳችን እንማር
መልካም ሥራ በመስራት እንኑር
የሰይጣን ድል መንሻ የክብር መውረሻ
ሃይማኖት ናትና አውነተኛ ጋሻ
የሰው ለጆች ሁሳችን.....
አምነታችን ሁሉ ይሁን በፈጣሪ
ይቅር ባይ ነውና ሲቻለው መሃሪ
የሰው ለጆች ሁሳችን.....
ፍዳ ዓለምን አልፈን እንሂድ ሁሳችን
ፀንተን መገኘት ነው በሃይማኖታችን
የሰው ለጆች ሁሳችን.....
ለአውነተኛ ሥራ ሁሳችን እንበርታ
ፃድቃን ሰማአታትን አድርገን መከታ
የሰው ለጆች ሁሳችን.....
ጥቅስ፡ ያዕ 2÷14-17

መዝሙር
የሰው ልጅ ሁልጊዜ
የሰው ልጅ ሁል ጊዜ በጣም ደስ ቢለው(2)
ደግሞም የጭንቁን ቀን ማሰብ ተገቢ ነው(2)
ምንም ቢደሰቱ ቢበዛ ም©ት(2)
አይቀርም በኋላ መወሰድ በሞት(2)
ችግር ቢደራረብ ሃዘን ቢከበን(2)
ከክርስቶስ ፍቅር ማንም አይለየን(2)
ሳናውቀው ዲያብሎስ እንዳይነጥሰን(2)
ነቅተን እንጠብቀው የአምነትን ሰይፍ ይዘን(2)
ጥቅስ፡ ሉቃ 12÷13

መዝሙር
ወደ ሕይወት መንገድ
ወደ ሕይወት መንገድ ይመራኛል ጌታ
በጨለማው መንገድ እንዳልገላታ
ፈጣሪ ብቻ ነው ሕይወቴና ክብሬ
በርሱ ደስ ይለኛል ሳቀርብ ዝማሬ
ጉልበት ሁሉ ለአንተ በፍርሃት ይሰግዳል
ምህረትን አድስን ፈጣሪ ችል አትበል
የምህረትን ውኃ የተጠሙ ሁሉ
ከኃያሉ ጌታ ካንተ ይረካሉ
በምህረትህ ማረን አቤቱ ፈጣሪ
ለፍጥረትህ ሁሉ ነህና መሀሪ
ሠላምን አድሳት ለሺትዮጵያ
አጆቿን ዘርግታ ስትል ሃሌ ሉያ
ጥቅስ፡ መዝ22/23/÷በሙሉ

መዝሙር
በሕይወቴ በዘመኔ
በሕይወቴ በዘመኔ ደስ የሚለኝ ለኔ በወንጌል ማመኔ(2)
ወደ ሰማይ አገር አሁን ለምትሔዱ
አምሯል ተደላድሏል ተሰርቷል መንገዱ
በሕይወቴ.....

ሔዳችሁ ሔዳችሁ አንዳትሳሳቱ
ከመንታው መንገድ ሳይ አስ ምልክቱ
በሕይወቴ.....
ቀኙን ስትሔዱ ግራውን ትታችሁ
ኢየሱስ የሚለው ጽሑፍ አስላችሁ
በሕይወቴ.....
እኔም ወደዚያ አገር አሔዳለሁና
አንገናኛለን ከደረስን በደህና
በሕይወቴ.....
ጥቅስ፡ ሮሜ 1÷15-16

መዝሙር
ተነሱ አንዘምር
ተነሱ አንዘምር(3) ለአምላክ በአንድ ቃል
ሁላችንም አንጂ ወንድ ሴት አንበል
ተነሱ አንዘምር ለአምላክ በአንድ ቃል
የአምላክ ምስጋና ምን ያሳፈረናል
አንኳንስ አርሱ አና ሰው ይመሰገናል
ተነሱ አንዘምር.....
ለሚያወርድልን ዝናመ ምሕረት
ደግሞም ለሚሰጠን አክለ በረከት
ተነሱ አንዘምር.....
ሁሉንም በጊዜው ለሚሰጠን ጌታ
መዘመር አለብን ሁላችን በአልልታ
ተነሱ አንዘምር.....
ጥቅስ፡ መዝ44/45/÷1-2 መዝ94÷1-11

መዝሙር
የድሆች መጠጊያ
የድሆች መጠጊያ ቤተ ክርስቲያን
አነሆ ተደሰች ልጆችሽ መጣን(2)
ሰላም ሰላም የዘለዓለም ቤቴ(2)
ካንቺ አልለይም እስከ አለተ ሞቴ
ሰላም ላንቺ ይሁን ቤተ ክርስቲያን(2)
በደሙ ያፀናሽ ኢየሱስ መድኃን
ሰላም.....
ቤተክርስቲያን ሆይ የአማንያን እናት(2)
ወዳንቺ ቀርበናል አንድናገኝ ሕይወት(2)
ሰላም.....
ቅረቡ ወጣቶች በአንድነት ሆናችሁ
አጆቿን ዘርግታ ልትቀበላችሁ
ተነስታለች እና ቅድስት እናታችሁ
ሰላም.....
ጥቅስ፡ ማዝ121÷1 ማቴ16÷18

መዝሙር
ሰው ሆይ
ሰው ሆይ(2) አስብ ለነፍስህ
ዛሬ ቆመህ ብትሔድ ነገ አፈር ነህ
ጌታችን አዞታል አዳምን እንዲህ ሲል
አንተ መሬት ነህ የአፈርም ክፍል
ሰው ሆይ.....
ሰው አፈር መሆን ፈጽሞ አይካድም
ሲወርድ የመጣ ነው ከአባታችን ከአዳም
ሰው ሆይ.....
ሁሉም አላፊ ነው ታይቶ የሚጠፋ
የሰው ልጅ ይከተል የማይጠፋ ተስፋ
ሰው ሆይ.....
ክርስቲያን ነኝ ማለት በስም ብቻ አይደለም
በሥራ ነው እንጂ ሁሉም መፈፀም
ሰው ሆይ.....
አቤት አቤት ቢሉት ከልብ ይዞ ተንኮል
ጌታ አይቀበልም ቀድሞ አስጠንቅቆናል
ሰው ሆይ.....
ጥቅስ፡ ዘፍ2÷7 ዘፍ3÷17-19 ኢዮ14÷ በሙሉ
ማቴ7÷21-23

መዝሙር
አባትህን እናትህን
አባትህን እኽ አናትህን አክብር(2)
አትስረቅ አትግደል አታመንዝር(2)
ይሳል የእግዚአብሔር ቃል(2)
ጥቅስ፡ ዘፀ20÷1-7 ኤፌ6÷14

መዝሙር
በእጅ ያልተሰራች
በእጅ ያልተሰራች(2) የሰማይ ድንኳን(2)
እኛ ክርስቲያኖች በሳይ ቤት አለን(2)
ለጥቂት ጊዜ ነው(2) በዚህ ዓለም የምንኖር(2)
ጥለን እስክንሔድ እኑር በፍቅር(2)
ጥቅስ፡ 2ኛጴጥ2÷በሙሉ

መዝሙር
በጐቼን አውቃለሁ
በጐቼን አውቃለሁ እነርሱም ያውቁኛል
ድምጼን እየሰሙ ይከታተሉኛል
ወደ በጐች ስፍራ ያልገባ በደጅ
ፃድቅ አይባልም ቀማኛ ነው እንጅ
በኔ የገባ ግን በቀጥተኛው በር
ሕይወት ይካፈላል በሳይኛው አገር
ቸር ጠባቂ እኔ ነኝ ምንደኛ ያየደለሁ
ለበጐቼ ቤዛ ራሴን የለወጥሁ
ጥቅስ፡ ዮሐ10÷1-6

መዝሙር
ልባችሁ አይደነግጥ
ልባችሁ አይደንግጥ እኔንም አመኑ
ብዙ ቦታ ሞልቷል አብን ብትለምኑ
ብዙ ቦታ ባይኖር በሳይኛው አገር
ከብዙ ቀን በፊት የለም ባልኩኝ ነበር
አሰጣችኋለሁ ሠላሜን በብዙ
በደሜ ታጥባችሁ ጽድቅን እንድትገዙ
ናፍቃችሁ እንደሆን ወደ አብ ለመሔድ
እኔ አለሁላችሁ ቀጥተኛው መንገድ
ተመስገን ጌታችን ለዚህ ያደረስከን
ቀንበር ባርነትን ሰባብረህ ጣልክልን
ጥቅስ፡ ዮሐ14÷1-7

መዝሙር
ዘሰማየ ገብረ
ዘሰማየ ገብረ ሰማየ ገብረ ወምድር ሣረረ(2)
አልቦ ዘየአብዮስ አምላክነ(2)

ሰማይን የዘረጋ መሬትን ያፀና(2)
ኃያል ጌታ ሕያው አምላክ ያለአንተ ማን አለና(2)
ጥቅስ፡ ዘፍ1÷1

መዝሙር
የሐሰት መስካሪ
የሐሰት መስካሪ ካልጠፋ ከሀገር(2)
አይመሰረቱም ሠላምና ፍቅር(2)
አገኛለሁ የሚል ተስፋ ያደረበት(2)
ሲለውጥ ደኖራል እውነትን በሐሰት(2)
በሐሰት መስክሮ የተገኘ ገንዘብ(2)
ቢቀርም አይጐዳ ቢመጣም አያጠግብ(2)
ምንም ቢችግርህ ለገንዘብ ብትሣሣ(2)
የፈጣሪህን ስም በከንቱ አታንሣ(2)
በሐሰት አትመስክር ይቅርብህ ወንድሜ(2)
የሐሰት መስካሪ አያገኝም ዕድሜ(2)
ጥቅስ፤- ያዕ 3÷13-14
ዘፀ 28÷1-3

መዝሙር
ሰው ሆይ ለነፍስህ ዋል
ሰው ሆይ(2) ለነፍስህ ዋል ለፅድቅም ተነሣ
ጊዜህ እንደ ሣር መሆኑን አትርሳ
በሥላሴ አርአያ ሰው ሆይ
የተፈጠረው ሰው " "
በዳግም ትንሣኤ " "
ይነሣል ሕያው ነው " "
ሰው ሆይ(2) _____
አቤቱ ፈጣሪ ሰው ሆይ
በቸር አስበን " "
ዛሬ ህያው ብንሆን " "
ነገ መሬት ነን " "
ሰው ሆይ(2)_____
ቃላሪ ችል አትበል ሰው ሆይ
የእጆችህን ሥራ " "
ከጠላትም ወጥመድ " "
ጠብቀን አደራ " "
ሰው ሆይ(2)_____
የምድርን በረከት ሰው ሆይ
አምላክ ባርክልን " "
የበረከት ፈሬ " "
እንዲሆንልን " "
ሰው ሆይ(2)_____
የሠላም ባለቤት ሰው ሆይ
አምላክ አንት ነህ " "
ሠላምን አድለን " "
ለኛ ባሮችህ " "
ሰው ሆይ(2)_____
ጥቅስ፤-ኢሳ 40÷6-8

መዝሙር
በሞት ጥላ ወድቀን
በሞት ጥላ ወድቀን ስንከራተት(2)
በረቀቀው ፍቅሩ ዋጀን ከጥፋት(2)
በገልገታ የታየው ፍፁም መድኃኒት::
ሃሌ ሃሌ ሉያ ለአንተ ለኃያሉ ጌታ(2)
ስለኛ ተዋረድክ በጐልጐታ
የሞት ሸክም ከብዶን በጣር ስንባዝን(2)
ወረደ ከሰማይ መጣ ሊያግዘን(2)
ከባርነት ሸክም ሊገላግለን::
ሃሌ ሃሌ ሉያ_____
ምንም ባልበደለው ምንም ባላጠፋው(2)
ሁሉን ማድረግ ሲችል ደካማ የሆነው (2)
ሕይወትን ሊያድለን ሰለወደደ ነው
ሃሌ ሃሌ ሉያ_____
አስቲ አስተውሉ የፍቅሩን ብዛት(2)
ለመስቀል ሞት ታዞ አኛን ያዳነበት(2)
ምንም አቻ የለው የጌታ ቸርነት
ሃሌ ሃሌ ሉያ_____
ጥቅስ፤- ሲሳ 53÷1-12 ማቴ 27÷1-7

መዝሙር
ወንጌል ነጋሪዎች
ወንጌል ነጋሪዎች ቀሳውስት በመሉ(2
ከአምላክ ማፈግፈጉን ከቶ አይሆንም በሉ(2)
ልዑካን ዲያቆናት ፀልዩ እያሳችሁ(2)
ህፃናት ወጣቱን ምከሩ ባካችሁ(2)
እንዲሁም መምህራን ሰባክያን ሁሉ(2)
ወንጌል አስተምሩ ዓለምን በሙሉ(2)
ወንጌል ነጋሪዎች.....
ትምህርተ ወንጌሉን የምትሣተ⌋
ኧረ ዝም አትበሉ ህፃናት ሲጠ⌋
" " " ወጣቶች "
ህግና ሥርዓቱን የተስተማራችሁ(2)
ክፋትና ተንኮል ይራቅ ከልባችሁ(2)
ወንጌል ነጋሪዎች.....
የወንጌል ማደሪያ ሆኖ ልቦናችሁ(2)
ለሠላም ለፍቅር ይሆን ፀሎታችሁ(2)
የአዳም ዘር በሙሉ ያገኛችሁ ጥቅም(2)
ተዋህዶ አምነትን እንዳትለውጧት(2)
ጥቅስ ያዕ 5÷14 ሐዋ 20÷28

መዝሙር
ሀበ ቅራንዮ
ሃበ ቀራንዮ ደብረ መድኃኒት(2)
ቀራንዮ(2) ሀበ ቀራንዮ
የመስቀሉ ቃል ለኛ የእግዚአብሔር ኃይል ነው (2)
ለማያምኑት ሞኝነት ነው ለኛ ግን ህይወትነው (2)
እንመሠክራለን ፈጣሪያችን አለ
" አማኑኤል አለ
እንመነው እንካደው ፈጣሪያችን ቸር ነው(2)
እንመሠክራለን ድንግል አማላጅ ናት
" ማርያም " "
እንመናት እንካዳት የአምላክ እናት ናት(2)
ሀበ ጥበባት ሀበ ልሳናት (2)
ዮሐንስ (2) ወንጌሉ ስብከት(2)
ጥቅስ፤- 1ኛ ቆሮ 1÷18-31

መዝሙር
የአምላክነቱን
የአምላክነቱን ሲገልጽልን ፍቅሩን
ወደ ዓለም ላከው አንድ ልጁን

አምላክነቱን የካዳችሁ
ተመለሱ ልምከራችሁ
የሥሙን ክብር ለአምላክ አምጡ
ምስጋናውን ለእርሱ ስጡ
ኃላ መንግስቱን አንዳታጡ(2)
የአምላክነቱን.....
ወደ መቅደሱ ሁላችሁ ሒዱ
ለባአድ አምላክ አንዳትሰግዱ
በአንዲት አምነት ከፀናችሁ
ከአቶን አሳት ትወጣለችሁ
በአንዲት አምነት ከፀናችሁ
ከነደደ አሣት ትወጣላችሁ
የአምላክነቱን.....
አይጠቅመንም መዋተት
ከተዋህዶ በቀር ሌላ አምነት
አምነን ሳንሰራ በአውነት
ሞት ይመጣል በድንገት (2)
የአምላክነቱን.....
አምላክ መሀሪ ከሀሊ ነው
መስጠት መንሣትም ሥልጣኑ ነው
እሱን የሚያክል ሌላ ማን ነው (2)
የአምላክነቱን.....
ለማይረባ ለማይጠቅም
ሁሉም ኑሮ ለማይል ቅም
አንደው በከንቱ አምላክ መካዱ
ከቶ አይሆንም ሰዎች ተረዱ
ከቶ አይረባም ሰዎች ተረዱ
የአምላክነቱን.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ጌታ ያለው
ጌታ ያለው ሁሉም አለው
የዘለዓለም ሕይወት ባለቤት ነው
አመኑ በጌታ ይህ ብቻ ይበቃል
የቀረውን እርሱ በፍቅሩ ይሰጣል
ጌታ ያለው.....
ሠላም ላጡ ሰላም ፍቅርን ላጡ ፍቅርን
ለታረዙት ልብስን ለተራቡት እንጀራ
ለተጠሙት ውኃ ለታመሙት ፈውስን
ተስፋ ላጡት ተስፋ ለደካሞች ኃይልን
ጌታ ያለው.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ተናገሩ ድንቅ ሥራጢን
ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መስክሩ(2)
ተአምሩን ለዓለም ንገሩ(2) ድንቅ ሥራውን መስክሩ(2)
ጥቅስ፡ መዝ104÷1-2

መዝሙር
ሠርዓለነ ሰንበት
ሠርዐለነ ሰንበት ለአረፍተ ዚአነ (2)
ሠርዐ ለነ ሰንበት ለዕረፍተ ወለ መድኃኒተ(4)
ትርጉም፡ ለረፍተ ሥጋ ለረፍተ ነፍስ ለመድኃኒተ
ሥጋ ለመድኃኒተ ነፍስ ሰንበትን
ሠራልን::
ጥቅስ፡

መዝሙር
አለምን ዞረ አየኋት
አለምን ዞረ አየኋት
ሁሉን በተራ ቀመስኩት
ፈጽሞ የለም(2) ሰላም እንደ ልጅሽ ቤት
ሀብት ንብረቴን ጨረስኩና
ጉልበቴም ሁሉ ደከመና
ጐስቋላ ሆንኩኝ(2) ደካማ የሌለው ጤና
ስቃ አሣለቃ ተቀብላ
መልኳን አስውባ ተኳሉላ
ዛሬ ጣለችኝ(2) ይች ዓለም አትረባም ብላ
የትናትና ወዳጆቼ
ዛሬ ሲሆኑኝ ጠላቶቼ
ባክኜ ቀረሁ(2) በዓለም ላይ ተንከራትቼ
የአባቴ ቤት ሲናፍቀኝ
ፍቅሩ ምሕረቱ ትዝ ሲለኝ
ሁሉንም ትቼ(2) ድንግል ሆይ ዛሬ መጣሁኝ
ልጁም አባል ዘንድ ባይገባኝ
ባሪያው እሆን ዘንድ ቢፈቅድልኝ
ጐስቋላው ልጅሽ ደካማው ልጅሽ ድንግል ሆይ ዛሬ መጣሁኝ
አናቴን አንቺን ንቄ ትቼ
የአባቴን ቤት አረስቼ
ተሰቃየሁኝ ተንከራተትኩኝ ልደሰት በዓለም ገብቼ
አባቴ ሲያየኝ ተደሰቶ
ጐረቤቶቹን ሁሉ ጠርቶ
ሠርጉን ደገሰ(2) የበደልኩትን አረስቶ
አስከ አሁን ድረስ በድያለሁ
ዓለም ደህና ሁኝ አብቅቻለሁ
ወደ አባቴ ቤት ወደ ድንግል ቤት ዳግመኛ ተደስቻለሁ
ጥቅስ፡ ሉቃ15÷12-24

መዝሙር
እንግዶች ነንና
እንግዶች ነንና በዚህ ዓለም ስንኖር
ተባብረን ባንድነት እንኑር በፍቅር(2)
የዓለም ባንሆንም ስለምንኖር በዓለም
በሥጋም በነፍስም አናብብ እንለምልም(2)
አንገዛምና ለጨለማው ዳኛ
መሸፈት ካልቀረ እንፈልግ መዳኛ(2)
በጨለማ ሳለን ብርሃን ስለሚያሻን
በእንዲህ ያለ ጊዜ አናብራ ወንጌልን(2)
የወንጌልም ብርሃን ፍቅር ስለሆነች
ይህው በሃይማኖት እንደወንጌል በራች(2)
አብበው ቅዱሳን በገነት ሲኖሩ
ጣፋጭ አምነቸው ያ ፍሬው ማማሩ
መርቶ እንዲወስደው መንገዱን ተማሩ(2)
ጥቅስ፡ ቆሮ 9÷8-15 ዕብ 11÷13

መዝሙር
ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ጥበባት
ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ጥበባት(2)
አትመረመርም(2) አጅግ ጥልቅ ናት

በሥጋዊ ጥበብ ስማወቅ ቢቃጣ
እምነት መነጽሩን ይዞ ስሳልመጣ
ሰው ሁሉ በክደት(2) ፈጣሪውን አጣ(2)
የመስቀሉ ቃል ስኛ የእግዚአብሔር ኃይል ነው(2)
ስማያምኑት ሞኝነት ነው ለእኛ ግን ሕይወት ነው(2)
እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ
እንመሰክራለን አማኑኤል አለ
እንዳንዱ ቢክደው(2) እየተታለለ (2)
እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት
እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት
ወላዲተ አምላክ(2) መሰረተ ሕይወት(2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
እግዚአብሔር ብርሃኔና
እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው(2)
የሚያስደነግጠኝ የሚያስፈራኝ ማን ነው(2)
አምላኬ መመኪያዬ ነው(2)
ጥቅስ፡ መዝ26/27/÷1 1ኛዮሐ4÷17
ሉቃ10÷1-20

መዝሙር
ሰው ሆይ አትታለል
ሰው ሆይ አትታለል ስጊዜው ቢደላህ
የዛሬ ሰው ብትሆን(3) የነገ አፈር ነህ
ለዚች ለሥጋዬ ስብከነከንሳት(3)
ያብከነክነኛል(3) ይመጣና ያ ሞት
አምላኩን የሚያስብ ከጧት አስከ ማታ(2)
ንዑድ ነው ክቡር ነው(3) በሳይኛው ቦታ
ለዚች ለስጋዬ.....
ሰው አፈር መሆኑ መበስበሱ ላይቀር(2)
ምነው አንዱ ለአንዱ(3) መቃብር ባይቆፍር
ለዚች ለስጋዬ.....
ሰው ሆይ አትጨነቅ አትጠበብ በጣም(2)
ለዚህ ለማይሞላው(3) ስጐደሎው ዓለም
ለዚች ለሥጋዬ.....
ጥቅስ፡ ዘፍ3÷19

መዝሙር
እያስፈ ነው ዘመኔ
እያስፈ ነው ዘመኔ ትአዛዙን ሳልፈጽም ወየው ለእኔ
በጠራኝ ጊዜ ምን አሳስሁ ና ብሎ ወደ እኔ
" " " " ነይ " "
በወጣትነቴ ሳልሰራ እያየሁ አስፈኝ ብዙ አዝመራ
ከአንግዲህ በመስራት ጌታ ሆይ ልኑር ከአንተ ጋራ(2)
የማስብበት በየአለቱ ንፁሕ ልብን ስጠኝ አቤቱ(2)
ከትአዛዝህ ውጭ በመሆን እንዳልቀር በከንቱ(2)
እንደየስራው ለመክፈል በግርማ መንግስቱ ሲመጣ
ማን ይሆን የሚቆም ከፊቱ ፈተናን የወጣ(2)
እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ የተማራችሁ ከቃሉ(2)
ይመጣሉና በአርሱ ስም አምላክ ነን የሚሉ(2)
ትዕግስቱን በመያዝ ሁላችሁ እስከ መጨረሻው ጠንክሩ
ያን ጊዜ ይሆናል በአርሱ ዘንድ የማዳን ተግባሩ(2)
ጥቅስ፡ ማቴ 24÷23-28

መዝሙር
ሁላችን አንፀልይ
ሁላችን አንፀልይ የሃይማኖት ፀሎት (2)
አንድናውቅ ምስጢሩን(2) የተህዶን አምነት
የአንድነት ሦስትነት ምስጢሩ ከገባን(2)
ከቶ ምንም አይኖር (2) የሚያይናግረን
የአምላክ ሰው መሆን ምስጢረ ስጋዌ(2)
ያስረዳናል በእውነት(2) የአንድነት ሕላዌ
የአንድነት ሦስትነት ምስጢሩ ይረቃል(2)
በሃይማኖት ትምሕርት (2) ጐልቶ ይታወቃል
ሁላችን አንፀልይ.....

መዝሙር
መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም ያነበዋል
መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም ያነበዋል
ምዕራፍና ቁጥሩን ሁሉም የጠቅሰዋል

መዝሙር
ሕገ እግዚአብሔር ቅን ናት
ሕገ እግዚአብሔር ቅን ናት
መንገዷም ሕይወት
ታድነናለች ከዘለዓለም ሞት
በአንግድነት ሀገር ሥርዓት የምትሆን
ሰላምን የምትሰጥ የራቀች ከሀዘን
የመንገዴ ብርሃን የአግሬ <u>መብራት ?</u>
ሕግህ ለዘለዓለም ይሁነኝ <u>መብራት ?</u>
ሕገ እግዚአብሔር ቅን ናት.....
ወንበዴ የነበርን ሽክም የከበደን
ሕግህን አፍርሰን ሀዘን የከበበን
ሕይወት እንዲሆነን ላንተ ልንገዛ
መጣን ተቀበለን የዓለም ሁሉ ቤዛ
ሕገ እግዚአብሔር ቅን ናት.....
ከጠላቶቼ ድል ህግህ ጠቀመኝ
ራሴን ገዛሁኝ አስተዋይ አረገኝ
እንዲሆን አምኜ ሕግህ መድኃኒቴ
ንስሐ ገባሁኝ ቆምኩኝ በሕይወቴ
ሕገ እግዚአብሔር ቅን ናት.....
ክርስቲያኖች ሁሉ እንመሰክራለን
ሕግህ ብርሃን ነው በእንተ እንመራለን
ሥጋችን ደካማ ሆነና ረገን
ለእግራችን ብርሃን የት እናገኝ ይሆን
ሕገ እግዚአብሔር ቅን ናት.....
ጥቅስ

መዝሙር
አቤቱ ጌታ ሆይ
አቤቱ ጌታ ሆይ ምስጋናህ አያልቅም(2)
ሥራህ ሁሉ (2) አይመረመርም(2)
ጥቅስ፡ መዝ96÷1 ጀምሮ ኢሳ 10÷1-23
ማቴ 8÷በሙሉ

መዝሙር
ስብሐት ለአምላክነ
ስብሐት ለአምላክነ ወመድኃኒነ(2
ወአድኃንከ ሕሊናነ(2)
ትርጉም፡ ስመድኃኒታችን ስፈጣሪያችን ምሥጋና
ይገባዋል።። ሀሳባችንን ከክፋ ነገር
ስለመለሰልን(ስላዳነን)
ጥቅስ፡ ኤፌ2÷በሙሉ ኢሳ9÷1-12 ሮማ8÷1-8

መዝሙር
አማን በአማን
አማን በአማን(4)
አማኑኤል ተመስገን(2)
አማን በአማን(4) አማኑኤል ተመስገን
ድብቁን ኃጢአት አንተ ብትገልፀው
ይቅር ብለህኝ ባትሸፋፍነው
አንደ ሰው በቀል ቢኖርህ ጌታ
ለኔ ኃጢአትስ የስውም ቦታ
አማን.....
በየደቂቃው ኃጢአት ስሰራ
ስሰርቅ ስበድል አንተን ሳልፈራ
አንተ ግን ፊትሕ ምንም ቢቀየም
በቁጣህ በትር አልገረፍከኝም
አማን.....
ምሕረትን ልከህ አድነኝ ዛሬ
ታክቶኛል አና በኃጢአት መኖሬ
ዓለም በኃጢአት እየሳበችኝ
በፍፁም ደስታ መኖር አቃተኝ
አማን.....
የኃጢአት ጉዞ ጣፋጭ ቢመስልም
ውጤቱ መሮ ፍፁም አይጥምም
አንደበይሌ ስላልከፈልከኝ
ተመስገን አንጂ ሌላ ምን አለኝ
አማን.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
ልዑል አግዚአብሔር
ልዑል አግዚአብሔር(2) ምሥጋና ይገባሀል(2)
ስዚች ሰዓት (2) በሰላም በጤና አደረስከን(2)

መዝሙር
በእውነት አምልኮአችን
በእውነት አምልኮአችን እንዲሆን የቀና
ስእመቤታችን እናቅርብ ምስጋና
የአምላካችን እናት ናትና እናቅርብ ምስጋና
የፈጣሪያችን እናት ናትና " "
የአዳኛችን እናት ናትና " "
በእውነት አምልኮአችን.....
የመጠጊያችን እናት ናትና እናቅርብ ምስጋና
የታዳጊያችን " " "
የመመኪያችን " " "
በእውነት አምልኮአችን.....
የአምላካችን እናት ናትና እናቅርብ ምስጋና
የቅዱሣችን " " "
የንጉሣችን " " "
የምስጉናችን " " "
በእውነት አምልኮአችን.....

መዝሙር
ግሩም ነው ጌታ አምላክ
ግሩም ነው ጌታ አምላክ ስመ ጥርን አለታ
እፁብ ነው ጌታ አምላክ ስመ ጥርን አለታ
ድንቅ ነው
ሥሉስ
ቅዱስ
ንጉሥ
ኃያል
ልዑል
አጽናኝ
አዳኝ
ምሐሪ
አፍቃሪ
ወዳጅ
ታጋሽ
ፈራጅ
የፍጥረታት ጌታ ግሩም ነው
የአዳም አለኝታ
የኪሩቤል ንጉሥ
ዮሱራፌል ቅዱስ
የሚካኤል ኃይል
የገርብኤል ልዑል
ግሩም ነው.....
የሰራዊት ጌታ ግሩም ነው
የነቢያት አለኝታ
የዳድቃን አለኝታ
ግሩም ነው.....
የቤተልሔም ሕፃን ግሩም ነው
የታቦር ብርሃን
የናዝሬቱ ኢየሱስ
የአይሁድ ንጉስ
የቀራንዮ ቅዱስ
ግሩም ነው.....
የገሊላው መምሕር ግሩም ነው
የሐዋርያት ፍቅር
የዮርዳኖስ ትሑት
የመጥምቁ ትሑት
አረ የሲናው አሳት
ግሩም ነው.....
የቆሮንሶስ ባሕታዊ ግሩም ነው
የቆሬብ ግርማዊ
የቀራንዮው መሥዋዕት
የዓለም መድኃኒት
የፍጥረታት ሕይወት
ግሩም ነው.....

መዝሙር
ግሩም ነው እፁብ ነው
ግሩም ነው እፁብ ነው ድንቅ ነው ጥበበኛው ፈጣሪ
የፍጥረታት ጌታ የሰው ልጅን አፍቃሪ
የኪሩቤል ጌታ የሰው ልጅን አፍቃሪ
የሱራፌል ጌታ " " "
የሚካኤል ጌታ " " "

የገብርኤል ጌታ " " "
ግሩም ነው.....
የቤትልሔም ጌታ የሰው ልጅን አፍቃሪ
የዮርዳኖስ ጌታ " " "
የቆሮንቶስ ጌታ " " "
የገሊላው ጌታ " " "
ግሩም ነው.....
የነቢያት ጌታ የሰው ልጅን አፍቃሪ
የሐዋርያት ጌታ " " "
የነአብርሃም ጌታ " " "
የነሙሴ ጌታ " " "
የነኤልያስ ጌታ " " "
የነጴጥሮስ ጌታ " " "
የነዮሐንስ ጌታ " " "
ግሩም ነው.....
የናዝሬቱ ጌታ የሰው ልጅን አፍቃሪ
የታቦሩ ጌታ " " "
የቀራንዮ ጌታ " " "
የንልንታ ጌታ " " "
ግሩም ነው.....

መዝሙር
ዝንቱ ኩሉ ኮነ
ዝንቱ ኩሉ ኮነ(2) በተምሮ ማስተማር
በፈቃደ(4) እግዚአብሔር(2)
ደህ ሁሉ የሆነው (2) በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው(2)
ማንበሩን በቸርነት(2) በእውነት ጠባቂ ነው(2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
በአምሳሉ ፈጥሮናል
በአምሳሉ ፈጥሮናል አናመስግነው
በአርአያው ፈጥሮናል ሁሉ በእርሱ ነው
ከኛ የሚፈለገው ማመን
ከኛ የሚፈለገው መታመን
አፍም ይፁም ከማውራት ይከልከል
ጆሮም ይፁም ከማስማት ይጠበቅ
አይን ይከልከል ከማየት ይቆጠብ
በአምሉ.....
ልሳን ይፁም ከመናገር በእርምሞ
እጅ እግር ይፁም ከመዳፈር በተደሞ
በአምሉ.....
ምምጫው ደርሷል ቀርቦል ቀኑ
እንመለሳለስ በብርሃኑ
በአምሉ.....
ጥቅስ፡ ኢሳ40÷3 ማቴ3÷2

መዝሙር
አባታችን ሆይ የሁላችን ጌታ
አባታችን ሆይ የሁላችን ጌታ
ቅዱስ መንፈህን ስጠነ በተርታ
ወደ አንተ መልሰው የሰውን ልቦና
ባስወቀው መንገድ እርሱ ሔዷልና
እዝነ ልቦናህን ወደ እኛ አዘንብል
ይቅርታን ልንጠይቅ በፊትህ ቆመናል
ይቅርታን ልንጠይቅ ከፊትህ የቆምነው
መሀሪ መሆንክን ስለምናውቅ ነው
አይቶ እንዳላየ ታልፈዋስህ ሁሉን
መአቱ ምሕረቱ ሁሉም የአንተው ሲሆን
አይመረመርም ሥልጣንህ ረቂቅ ነው
ዘመንና ወራት ሊሸሩህ አይችሉም
አንማልድሀለን በስቅሶ በሀዘን
የይቅርታህ ብዛት ከእኛ ጋር እንዲሆን
የምድር ሰራዊት የሰማይ መላእክት
ያመሰግኑህል ቀንና ሌሊት ????

ጥቅስ፡ መዝ50÷9-10

መዝሙር
መአትህን አርቅ
መአትህን አርቅ(2) ከኛ(2)
ምሕረትህንም አውርድ(2) ሠማያዊው ዳኛ(2)
ኢየሱስ ክርስቶስ(2) ንጉሠ ራማ(2)
በጨነቀን ጊዜ በችገረን ጊዜ በፈተና ጊዜ ፀሎታችንን ስማ(2)
ጥቅስ፡ መዝ 85÷4

መዝሙር
አልተወኝም ጌታ
አልተወኝም ጌታ ስካስ ይወደኛል(2)
ዛሬም ስበድሰው ልጂ ነህ ይስኛል
ዛሬም ስበድሰው ልጂ ነሽ ይስኛል
በበደል ጉራንጉር በኃጢአት ጫካ
ስጠፋበት እንኳ አልተወኝም ስካ
ዛሬም ልጂ ብሉ ዳግም ይጠራኛል
ስካስ አልጠላኝም ጌታ ይወደኛል(2)
አልተወኝም.....
ለሥልጣን ስክብሬ ብዩ ስክደው
ስገንዘብ አድልቼ እኔ ስረሳው
ስኔ ያለው ፍቅር አልቀነሰብኝም
ዛሬም ይወደኛል ጌታ አልጠላኝም
አልተወኝም.....
ታዲያ ለዚህ ፍቅሩ ለሌለው ወሰን
ከጭንጫ መቃብር ሳወጣኝ እኔን
በሕይወቴ ሁሉ ፍፁም ለመራኝ
ክብርና ምስጋና አቀርባለሁኝ
አልተወኝም.....
ጥቅስ፡ ሉቃ10÷29-37 ሮሜ5÷10

መዝሙር
እግዚአብሔር አረኛዬ ነው
እግዚአብሔር አረኛዬ ነው ይጠብቀኛል(2)
በአረፍት ውኃ በለምለም መስክ(2) እኔን ይመራኛል(2)
ነፍሴን ጠብቆ በጽድቅ መንገድ መራኝ(2)
ስለ ስሙ (2) ከጥፋት እርሱ አዳነኝ
እግዚአብሔር አረኛዬ.....
በሞት ጥላ ውስጥ እንኳን ባልፍ አልፈራም
ያድነኛል (3) በምሕረቱ መድኃኒዓለም
እግዚአብሔር አረኛዬ.....
ቸርነቱና ደግሞም ምህረቱ ይከተለኛል

ስዘለዓለም በቤቱ ውስጥ (2) ስዘለዓለም(2)
እርሱ ያኖረናል
አግዚአብሔር አረኛዬ.....
ጥቅስ፡ መዝ22÷1

መዝሙር
የአመሰግዬ ብዛት
የአመሰግዬ ብዛት ከልሎኝ ያንተን ክብር
ነበርኩ የምዋትት በባቢሎን ምድር
ወጥመዱ ተሰብሮ ባሪያህ እንድፈታ
ይቅርታህን አፍስስ እንዳልቀር በዋይታ
አስንጋህን ይዘህ መቅደስህን አጽዳ
ማራገፊያ ሆኗን የሀጥያት በረዳ
ቅጥሩም ተንዶ በአንተ እንዲመሰረት
በይቅርታህ ብዛት አንፃት የኔን ሕይወት
የአመሰግዬ.....
የዘመመው ጐጆ ሳይርፈርስ ድረልኝ
የቆሰው ቁስሌን በዘይትህ ቀባልኝ
አሳዛር ሆይ ተነስ ብለህም አናግረኝ
ሬሳዬን ቀስቅሰህ ሕያው ልጅህ አርገኝ
የአመሰግዬ.....
በዓለም ሳይ ስኖር በጣም ተደስቼ
አምላኬን በመርሳት መግቢያ መውጫ አጥቼ
በጨለማ ኑሮ ስንከራተት ኖሬ
በኃጢያት ማአበል ስዋዠቅ አድሬ
አምላኬን ሳስበው በጣም ስንገላታ
አንባዬ ምግብ ሆነኝ ጠዋትና ማታ
የአመሰግዬ.....
በቤቱ ስመኖር ስፈልግ በጣሙን
አምላኬ አረሳኝም የአጁ ፍጥረቱን
የችግሬን ቀንበር ከላዬ አውደ
አምላኬ ታደገኝ ከሰማያት ወርዶ
የአመሰግዬ.....
ልጂ ሆይ ስትለኝ ኃጢአቴን ሳታይ
አንተኑ ሸሸቼ ሆንኩኝ አታላይ
አሳውቅም ጌታ ሆይ ወዴት አንደምሔድ
አባክህ አሳየኝ የሕይወትን መንገድ
የአመሰግዬ.....
የምህረት አጅህ ተዘርግቶ አያየሁ
ከአቅፍህ ስመግባት በጣም ተሰቃየሁ
የኃጥያቴ ብዛት በዓለም ሁሉ በዝቷል
ክፋቴን ሳስበው አንባዬ ይፈሳል
የአመሰግዬ.....
ስኃጢያቴ አጥበት ይሁነኝ ጌታዬ
በፍቅርህ አድሰኝ ጥሳ ከለሳዬ
በአንድነትህ ፀንተህ ስምትኖር ዘለዓለም
በባሕሪህ ህልፈት በአውነት የሰብህም
የአመሰግዬ.....
ጥቅስ፡ መዝ122÷5 ዮሐ2÷15

መዝሙር
አቤቱ አንተን አጠራለሁ
አቤቱ አንተን አጠራለሁ
ነፍሴን ወደ አንተ አነሳለሁ
ዝም አትበለኝ አጨሀለሁ(2)
የኃጢአት ሸክምም ከብዶኛል
የሥጋ ወጥመድ አስሮኛል
የሰይጣን ፍላፃ አጥቅቶኛል
አቤቱ.....
ደካማ ነኝ በጣም ችግረኛ
ምስኪን ተስፋ ቢስ አነስተኛ
ከመጋው የራቅኩኝ ብቸኛ(2)
አቤቱ.....
ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በለኝ
የንስሐን በር ክፈትለኝ
መጣሁኝ ጌታ ተቀበለኝ
አቤቱ.....
የቤትህ ናፍቆት አቃጣለኝ
የቃልህ በረከት አራበኝ
አባክህ ጌታ ይቅር በለኝ(2)
አቤቱ.....
ከአንተ ኮብልዬ ተንከራተትኩ
ምንም ሳይረባኝ ከንቱ ባከንኩ
ስበስባሽ ሥጋዬ ተረታሁ(2)
አቤቱ.....

መዝሙር
በሥራዬ የት ይሆን መግቢዬ
በሥራዬ የት ይሆን መግቢዬ (4)
ጨነቀኝ ጠበበኝ ነፍሴ ወዲያልኝ (2)
ተሸክሜ የኃጢአት ክምር (2)
ይመሻል ይነጋል በከንቱ ስዞር (2)
ገሰገሰ ቀኑ ጨለመብኝ (2)
ዋ ለነፍሴ ምንም ስንቅ አልያዝኩም(2)
በሥራዬ .....
በድያለሁ ወደ አንተ አጨሀለሁ (2)
ይቅር በለኝ አማፀንህለሁ (2)
ችላ አትበለኝ ከፊትህ ቆሜአለሁ(2)
በሥራዬ .....
አለፈብኝ በከንቱ ጊዜዬ(2)
አየንዓሁ ለዚች ለሥጋዬ (2)
በንስሐ ሳሳጥበው አድፌን (2)
ልትደርስ ነው ያች መከራ ቀን (2)
በሥራዬ .....

መዝሙር
ባርከን ባርከን
ባርከን ባርከን ልጆችህን ባርከን (2)
በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሀሳብ አድርገን(2)
ባርኪን ባርኪን ልጆችሽን ባርኪን (2)
ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሀሳብ አድርጊን
ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን
ጥሪህን አንስማ ወደ አንተ አንድንመጣ
በሕግህ ልንኖር ከቤትህ ሳንወጣ
በሕይወት ስንደክም አንዳንጠፋ በዓለም
አርዳን ፈጣሪያችን ቸሩ መድኃኔዓለም
ባርከን.....
ከተፈረደብን የባርነት ሕይወት
ከመጣብን መርገም በመብል ምክንያት
ከሲኦል አስራት አኛ የዳንብሽ
ድንግል ሆይ ሁል ጊዜ አይለየን ምልጃሽ
ባርከን.....

አንድነት ሳናጣ ፍቅር ሳትመነምን
በምግባር ስንደክም ሳይጐድል እምነታችን
በሥጋችን ፈቃድ ወድቀን አንዳንጠፋ
በምሕረትህ ጐብኝን አንተ ሁነን ተስፋ
ባርከን.....
ርህርተ ህሊና ቅድስት እናታችን
አሳስቢ ሁል ጊዜ ስለ ኃጢአታችን
ሊያድነን ነውና ክርስቶስ መሞቱ
አሳስቢ እመ አምላክ ድንግል ወላዲቱ
ባርከን.....
ጥቅስ፡

መዝሙር
አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነትህ
አመሰግንሃለሁ አልል
ለዓለምመ ዓለም አማኑኤል
አገዛልሃለሁ መድኃኔዓለም
ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
አረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈፅሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ
አድርገህልኛልና ~~~

ስታሳቅ ውስታ ጌታ ስዋስልን
በአልልታ እንዘምር በአንድነት ሆነን
አናመስግነው

መዝሙር
ከጨለማው ገዥ
ከጨለማው ገዥ ከጽልመቱ ንጉስ
ከሀጢአት አርግማን ያዳነን ክርስቶስ
በመገረፉ ቁስል ፈውስን ስቸረን
ታሳቅ ምሕረቱን ሞቱ ሳደለን
ስመደኃኔዓለም ውዳሴ አለን
በአልልታ በሽብሸባ እንዘምራለን
አስር ቤቱ ደፈረስ ትናወጽ ምድሪቱ
ደኃጠአት ማሰሪያ ደረገፍ ሰንሰለቱ
ደኃጢአት አስረኞች ይውጡ በነፃነት
የአምላክን ሥራ አይናቸው ይመልክት
ስመድኃኔዓለም.....
እንዘምር ስጌታ በሩ እንዲከፈት
በመዝሙር ይናወጽ የወህኒው መሠረት
ዳብሎስ ይደንግጥ መጋረጃው ይወደቅ
በአምላካችን ኃይል በግርማው ይጨነቅ
ስመድኃኔዓለም.....
እንመሰክራለን አምላክ የአንተን ክብር
ፀንቷል በልባችን የመስቀሉ ፍቅር
በፊቱ እንወድቃለን በምስጋና ደምቀን
የከፈርን ፍሬ ተቀበልን አያልን
ስመድኃኔዓለም.....
በቅዱስ አጠራር አምላክ የጠራችሁ
አርሱ ዝቅ ብሎ ከፍ ያደረጋችሁ
ክብር ሳይገባን በቤቱ ላቆመን
ስታገን ጌታ እንዘምር ተነስተን
ስመድኃኔዓለም.....

መዝሙር
ተስፋችን ነህ አንተ
ተስፋችን ነህ አንተ አስከ ዘለዓለም(2)
የድንግል ማርያም ልጅ መድኃኔዓለም(2)
ደምህን አፍስሰህ ሥጋህን ቆርሰህ (2)
ብሉ ጠጡ ብለህ ስዓለም ሰጠህ(2)
ተስፋችን.....
የዘለዓለም ሕይወት እንድናገኝ ሆነ
በመድኃኔዓለም ሁሉ ተከወነ (2)
ተስፋችን.....
ደሙን የረጫኸት ቅዱስ ዑራኤል
ኢትዮጵያን ቀረባት ሁናት ባለሟል(2)
ተስፋችን.....
በደሙ ተባርካ በዑራኤል እጅ
ዛሬም ከእርሷ ጋር ነው ሆኗት አማላጅ(2)
ተስፋችን.....
ፀሎቱ ኢትዮጵያን አጅግ ቀደሳት
ኃያሉ ዑራኤል መቼም አይተዋት (2)
ተስፋችን.....
ከመላእክት አንዱ ምድርን ከሚባርክ
አንዱ ዑራኤል ነው ይመስገን ቸሩ አምላክ (2)
ተስፋችን.....
አሜን አሜን ይሁን አሜን ሃሴ ሱያ (2)
ሠላምን ስግሳት ስኢትዮጵያ (2)
ተስፋችን.....

መዝሙር
ደስ ይበለን
ደስ ይበለን ደስ ይበለን
አምላክ አለ መሀሳችን
ምን ይከፈል ለዚህ ሥራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
ምሕረቱን አይተናልና
አድርሶናል አምላክ በጤና
ይህችን ዕድሜ የጨመረልን
ስንስሐ ጊዜ የሰጠን
ደስ ይበለን.....
ኃጢአትህን ይታገስሀል
በምሕረት አምላክ ያየሀል
ደስታ ነው በሰማያት
በአንድ ኃጥአ የጽድቅ ሕይወት
ደስ ይበለን.....
እልል በሉ የጐበኛችሁ
በቸርነት አምላክ ያያችሁ
በችግር ቀን ያሰበን ሁሉ
አመስግኑት ዝምም አትበሉ
ደስ ይበለን.....
ድንግል ማርያም ትፀልያለች
ኃጥኡን ሰው ማረው እያለች
በድንግል ክብር አንኖራለን
በጽኑ ፍቅር አንድ አንዲያደርገን
ደስ ይበለን.....
ጥቅስ:

መዝሙር
ኢትግድፈነ
ኢትግድፈነ ወይትመንነነ(2)
አምላከ ሰላም ተራድአነ (2) አኽ
ትርጉም:

ጥቅስ:

መዝሙር
ሰላም ለኢትዮጵያ
ሰላም ለኢትዮጵያ ሰላም ለአገራችን (2)
ይሳከልን (3) ቸሩ አምላካችን (2)

ጥቅስ:

መዝሙር
ኢትዮጵያ ታበጽእ
ኢትዮጵያ ታበጽእ አደዊሀ (2) ሀበ አግዚአብሔር (2)
አንዘ ትብል አምላኪየ (2) ነጽረኒ ወአድኅነኒ አምደ
ፀሳዒ ወፀብ (2)
ትርጉም:
ጥቅስ:

መዝሙር
የአብ ፀጋ
የአብ ፀጋ የወልድ ቸርነት የመንፈስ ቅዱስም
አንድነት (2)
እኽ ፀጋ በረከቱ ደደር በሁሳችን ሕደወት(2)

መዝሙር
አባታችን ሆይ
አባታችን ሆይ የምትኖር በሰማይ
መንግሥትህ ትምጣልን ክርህን አንድናይ (2)
ፈቃድህ በሰማይ ሕደወት እንዲሆነን
አንዲሁም በምድር ሰላምን ስጠን(2)
ስጠን ለዛሬ የእስት ምግባችንን
በደላችንንም ይቅር አንድትሰን (2)
ጌታ ሆይ አታግባን ከክፋ ፈተና
አንተ ካረዳህን ኃይል የስንምና (2)
ኃይና ምስጋና መንግሥትም ያንተው ነው
አሜን ለዘለዓለም ይሁንልን አረፍት (2)
ጥቅስ፡ ሉቃ11÷2-4

መዝሙር
ፀጋውና በረከቱ

ጥቅስ፡

መዝሙር
ኖላዊ ትጉህ
ኖላዊ ትጉህ ዘይትነውም (2)
ማኅበረነ (2) እቀበሰላም (2)
የማታንቀላፋ ትጉህ አረኛችን (2)
ጠብቅልን በሰላም ማኅበራችንን (2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
የቃልን ወተት
የቃልን ወተት (2) የመትመግበን (2
መድኃኔዓለም አባታችን ተምሮ ማስተማር
አናታችን (2)

መዝሙር
ለድሆች የሚያስብ
ለድሆች የሚያስብ ምስጉን ነው ደግ ነው (2)
ከችግር ከሀዘን አርሱ ያድነዋል (2)
ጥቅስ፡ መዝ40(41) 11÷16

መዝሙር
ኰሉ ዘፈቀደ
ኰሉ ዘፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር (2)
በሰማየኒ ወበምድርኒ ወበባሕርኒ ወበኩሉ ቀላያት(4)
ትርጉም፡ እግዚአብሔር የፈቀደውን የወደደውን አደረገ በሠማይም በምድርም በባሕርም በጥልቆችም ሁሉ::
ጥቅስ፡

መዝሙር
በሚገባው እምነቴ
በሚገባው እምነቴ ሳቀርብልህ ፀሎቴ
ምንም ድካም አይሰማኝም አንተ ሕያው ናፍቆቴ
ምንም ሕማም አይሰማኝም አንተ ሕያው ናፍቆቴ
ምንም ስቃይ አይሰማኝም አንተ ሕያው ናፍቆቴ
ጥቅስ፡

መዝሙር
አዘዘሙ ሙሴ
አዘዘሙ ሙሴ ለሕዝቡ (2)
ያከብሩ ሰንበተ ለፃድቃን (2)
ትርጉም፡ ሰንበትን ያከብሩ ዘንድ በእውነት ሙሴ ሕዝቦቹነ አዘዛቸው::
ጥቅስ፡

መዝሙር
ሰሎሞን ጥቀ
ሰሎሞን ጥቀ ኢስብሰስ (2)
አሐዱ ከመ አሐዱ እምእሱ (2)
ትርጉም፡ ሰሎሞን ከነዚህ አበቦች አንደ አንዱ እንኳን አልለበሰም::
ጥቅስ፡

መዝሙር
ቀንሞስ
ቀንሞስ ናንሞስ ከርካዕ ምስለ ዕንጐታት ክርስቶስ ሠርዐ ሰንበተ (2)
ነአኩቶ ለፀገውነ ሰናይቶ(4)
ትርጉም፡ ናርዶስ የሚባል ዕፅ በገነት አትክልት ቦታ ውስጥ ቀንሞስ ቀናንሞስ ሎሚ የሚባሉ ዕፅዋት ከዕንጐታት ክርስቶስ ሰንበትን ሰራ በዕውን ነገር የሰጠን ጌታን እናመሰግናለን::
ጥቅስ

መዝሙር
ወመኑ መሀሪ
ወመኑ መሀሪ(2)
ወኩሉ ይሴፎ ኪያከ(4)
እንደአንተ ይቅር ባይ ከቶ ማን ነው (2)
ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋል (2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
አለኝታችን
አለኝታችን (2) ይሁን(2) ወደፈጣርያችን (2)
እርሱ ስለሆነ(2) የህይወት ተስፋችን(2)
ኢየሱስ(2) ተሰቅሎ(2) በቅዱስ መስቀሉ(2)
ሙሉ ተስፋ ሆነ (2) ለአዳም ልጅ ሁሉ(2)
ለምታልፈው(2) ዓለም መጨነቅ ይቅርብን(2)
ተስፋችንም ሁሉ(2) በክርስቶስ ይሁን (2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
ከተጠሩት መሀል
ከተጠሩት መሀል እንዳልሄድ ኮብልዬ
ከምርጦችህ አንዱ አድርገኝ ጌታዬ
ቃልህን ለመስማት አንተ የጠራሀቸው
ክርስቲያን ወገኖች አጅግ ብዙ ናቸው
ነገር ግን ጌታ ሆይ አንተ ተናግረሀል
የምርጦቹ ቁጥር ጥቂት ነው ብለሀል
አንተን ለመከተል ጉዞ የጀመሩ
ዳሩ ግን በመንገድ ዝለው የሚቀሩ
የሰይጣን መአበል ድል የሚነሳቸው
አሉ ብዙ ሰዎች አንተ የምታውቃቸው
ዓለምን ሰይጣንን ሥጋን አሸንፈው
ሲጓዙ የሚችሉ ጽድቅን ተቀናጅተው
የተዋህዶ አርበኞች ኃይል የመላቸው
ጌታ ሆይ ምርጦችህ አጅግ ጥቂት ናቸው
እኔንም አስታጥቀኝ ፀንቼ እንድዋጋ
ጽናትን ስጠኝ ሁል ጊዜ እንድተጋ
በጉዞዬ ምራኝ ሁነኝ አረዳት
ጥቅስ፡

መዝሙር
በድንግል እናትህ
በድንግል እናትህ አባክህ ታረቀን
በአመፃችን ብዛት አይተህ አትቅሰፈን
መሀሪ ነህክ አይጨክንም ልብህ
እንደ ቸርነትህ ማረን አባክህ
የቅዱስ ሚካኤል የገብርኤል ጌታ
አራርተህ ፈውሰን የሁሉ አለኝታ
በክለሳይማኖት በአባታችን ፀሎት
ተማጽነናልና ይጥፋልን አጋንንት
ፍታን ከሽክማችን በአፀ መስቀል
ተረግጠናልና ፍቱን መድኃኒት ነህ
በሊቀ ሰማዕት በቅዱስ ጊዮርጊስ
ኢየሱስ ክርስቶስ ቸሩ መድኃኔዓለም
ተራዳን በገድሉ በቤሩቱ ፀሐይ
በብርሃን ፈረሱ ይምጣልን ከሳይ
በገብረ ክርስቶስ በአቡዬ ፃድቁ
አብቃን ስንስሐ ኃጢአትም ይራቅ
በፃድቃን ተጋድሎ በሰማዕታት ደም
ስጠን በረከትን ፍቅርና ሠላምን
ጥቅስ፡

መዝሙር
ስብሰባችንን ባርክልን
አቤቱ አምላክ ሆይ ስብሰባችንን በዚህች ቀን ባርክልን
ልመናችንን ተቀበለን እንድንጐናፀፈው ፀጋህን
አናውቃለንና ሰፊ ችሮታናን
አቤቱ ላክልን በረከትህን
ቅዱስ ቃልህን ሰምተን ወገኖችህ እንድንሆን ምረጠን
ልቦናችንን አጠብልን ሕሊናችንንም አንፃልን
የመንፈስህም ኃይል ይውረድ በላያችን
አቤቱ ላክልን በረከትህን
በፍቅርህ ጥላ ሥር ተጠግተን እንጠራለን ቅዱስ ስምህን
ታላቁ አባታችን ሆይ አንተ ነህ ሙሉ ተስፋችን
እንጠብቃለንና የሰማይ መንግስትህን
አቤቱ ላክልን በረከትህን(2)
ጥቅስ፡

መዝሙር
እንማልድሃለን
እንማልድሃለን ጌታ ሆይ በአፀደ ቤተክርስቲያን
ተሰብስበን ሥራችን እንዲቃና ተነኝ <u>በማህከላችን</u> (2)
የነፍሳችን ቤዛ የቅዱሣን ሀብት
ለእውነተኞች ፀጋ ለአዳም ሕይወት
ፈቃድህ ሆኖልን በዛሬዋ ዕለት
ጀምረናልና በሥምህ ፀሎት
እንማልድሀለን.....
ስምህን ለመቀደስ በረቂቅ ምስጢር
አንድነት በመሆን በመተባበር
እውነትን አጉልተን እንድንናገር
አድስን ለሁሉም አምላክ የአንተን ክብር
እንማልድሀለን.....
ፈቃድህ ሆኖልን ንበር ከኛ ጋራ
የጀመርነው ጸሎት ፍሬን እንዲያፈራ
ጸሎታችንንም ስማ ጌታችን ሆይ
በሕግህ ተመርተን ክብርህን እንድናይ
እንማልድሀለን.....
ጥቅስ፡ ሐዋ 4÷23-31 ማቴ18÷19-20

መዝሙር
ይህንን ጉባኤ
ይህንን ጉባኤ ባርክልን ጌታችን (2)
ሰላም ስጠን ፍቅርን ስጠን ዛሬ ለሁላችን (2)

መዝሙር
ኑ እንቅረብ
ኑ እንቅረብ መጠራት ሳይመጣ(2
ሥጋውን እንብላ(2) ደሙንም እንጠጣ
የቀራንዮ በግ የአምላክ ሥጋው
ተሰውቶልናል እንመገበው
እድፋን ኃጢአታችን በንስሐ እንጽተን
እንቀበል አምነን በልጅነታችን
መቅረብ ወደ ጌታ በእውነት የሚገባ
በስተርጅና አይደለም በወጣትነት ነው
ኑ እንቅረብ.....
ጨረቃና ፀሐይ ደም የለበሱለት
ከዋክብተ ሰማይ የተነጠፉለት
ይኸው ተፈተተ አሳተ መለኮት
ኑ እንቅረብ.....
ቅድስት እናታችን ቤተ ክርስቲያን

ትጋብዘናለች ሥጋና ደሙን
የአማኑኤል ስጋ ደህው ተፈተተ
ከግብዟው ተጠራ አዋጁ ታወጀ
መጥቁ ተደወለ አንቅረብ በአልልታ
በኋላ አደረባንም ዋይታና ጫጫታ
ኑ አንቅረብ.....
ይኽን አድል ፈጥነን አንጠቀምባት
ዓለምን አልያዝንም ብዙ ልንቆይባት
ከአሁኑ ቅረቡ ታውጇል አዋጁ
የይለፍ ደብዳቤ ስንቅን አዘጋጁ
ይህ ዓለም ጠፊ ነው በሀብት አትመኩ
ብሏል አምላካችን ተስፋችሁን አንኩ
ኑ አንቅረብ.....
(ከቅዳሴ በፊት የሚዘመር**)**
ጥቅስ፡ መክ1÷12

መዝሙር
ይህ ቁርባን ክቡር ነው
ይህ ቁርባን ክቡር ነው ፍፁም ሰማያዊ
አንዳያመስለን ተራ አይደለም ምድራዊ(2)
ዋ ! ምን አፍ ነው የሚቀበለው
ዋ ! ምን ጥርስ ነው የሚያላምጠው
ዋ! ምን ሆድ ነው የሚሸከመው
ነበልባል ያለበት የሚያቃጥል ነው
በንጽሕና ሆኖ ላልተቀበለው
የሚያፈገመግም የሚጎዳ ነው
ይህ ቁርባን.....
አምላካችን ሆይ አንተ ይቅር ባይ
አንደ ቸርነትህ በደልን አትይ(2)
አሜን አሜን ብለን ተቀብለናል
በድፈረትም ሳይሆን በፍርሃት ቀርበናል(2)
ይህ ቁርባን.....
መቃርዮስ በልቶ ስጋህን በተስፋ
60 ዓመት ኖሯል ምራቁን ሳይተፋ(2)
ሕግህን አክሮ ለተቀበለው
ስጋውን ፈውሶ ነፍሱን አዳነው(2)
ይህ ቁርባን.....
ማክበር ይገባናል በንጽሕና ሆነን
ቀለን አናቅለው አንዳያቃጥሰን(2)
አንደምታዩት ይህ ቁርባን ፈራጅ ነው
አንደ ሌላው ሳይሆን የተቀደሰ ነው(2)
ይህ ቁርባን.....
ሱራፌል ኪሩቤል ፀወርተ መንበር
ለመያዝ ያልቻሉት ፈርተውት በክብር(2)
አኛስ ተመገብነው አገኘን ድሕነት
በነፍስ በሥጋችን ሆነልን ሕይወት(2)
ይህ ቁርባን.....
ጥቅስ፡ ዮሐ6÷14 1ኛቆሮ14÷27-30
(ከቅዳሴ በኋላ የሚዘመር**)**